መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን !

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 15 ሐምሌ 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99



## ይፋ የሆነው ምስጢርና አሳዛኙ የኢ/ር ስመኘው አሟሟት

## የሦስቱ ፓትርያርኮች አሳፋሪ ታሪክ



## “የቂሊንጦን የእሳት ቃጠሎ ያስነሳው ፲ የታጋይ ልጅ ነው”

ካፒቴን መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ



## “የ19 ዓመት ወጣት ነኝ”

ተዋናይ መኮንን ላዕከ




## ሀገር ለዜጎች ዕድል ትስጥ!

# “መንግሥት የዜጎቹ ሐሳብ ውጤት ነው”



4



28

## ሀገር ለዜጎች ዕድል ትስጥ !
*“መንግሥት የዜጎቹ ሐሳብ ውጤት ነው”*

## ይፋ የሆነው ምስጢርና አሳዛኙ የኢ/ር ስመኘው አሟሟት

2 ሁለቱን ፓትርያርኮች በእኩል ሥልጣን ያስቀመጠ ስምምነት

9 ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ያለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ...
*ታምራት መርጊያ*

10 ኢትዮጵያና የብሔር ፖለቲካ
*ተሰፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ*

12 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትናንትና እና ዛሬ
*ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ*

14 “የ19 ዓመት ወጣት ነኝ፤ 27 ዓመቱን ኖርሁበት አልልም” ተዋናይ መኮንን ላዕከ

16 የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስን ጽናት ሳስብ የሦስቱ ፓትርያርኮች አሳፋሪ ታሪክ
*ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ*

18 “የቂሊንጦን የእሳት ቃጠሎ ያስነሳው ፤ የታጋይ ልጅ ነው” ካፒቴን መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ

21 የመስኮብ ዓለም ዋንጫ ውድድር
*ከፍቅሩ ኪዳኔ*

22 በመደመር ዘመን የመቀነስ ፖለቲካ - 2 -
*አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ*

24 የትግል አጋሮቼም ገደል ይግቡ
*ብሩክ መኮንን*

26 ዳህላክ ላይ ልሥራ ቤቴን
*መስፍን ጌታቸው*

ግዮን
ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ሐምሌ
28
ይጠብቁን!




ቁጥር 14 ዕትም

# “ግዮን” መጽሔት አስመራ ገባች!

በቅርቡ በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የተፈጠረውን ዕርቀ ሠላም ተከትሎ፤ ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ በተደረገው የመጀመሪያው ቀን በረራ “ግዮን” መጽሔት አስመራ ገብታለች::

ጠ/ሚ ዐቢይ ወደኤርትራ መጓዛቸውን ተከትሎ በሁለቱ ሀገራት አዲስ ግንኙነት ዙሪያ ልዩ ዕትም ለኅትመት ያበቃቸው “ግዮን” መጽሔት ከሃያ ዓመት በኋላ ኤርትራ የገባች የመጀመሪያዋ የነፃ ፕሬስ ውጤት ለመሆን በቅታለች::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አስመራ ያደረገውን የመጀመሪያ በረራ ተከትሎ በዕድሉ ተጠቃሚ በሆኑ ግለሰቦች ቀና ትብብርና በዝግጅት ክፍሉ ጥረት፤ አስመራ የደረሰችው ግዮን መጽሔትን ኤርትራውያን




በስጦታ መልክ ሲበረከትላቸው ደስተኛ ሆነው ተቀብለዋል፤ ለመጽሔቷ ዝግጅት ክፍል ያላቸውን ክብርና ምስጋናም በተጓዥ መልዕክተኞቹ በኩል አስተላልፈዋል::

# ጠ/ሚ ዐቢይና ፕ/ት ኢሳይያስ በአቡዳቢ የክብር ሜዳልያ ተሸለሙ!



ሰኞ ሐምሌ 15 ቀን 2010 ዓ.ም ከሃምሳ ዩኒቨርስቲ የተውጣጡ ሦስት ሺህ ያህል ምሑራንን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነጋግረዋል:: ምሑራኑን ያወያዩት ጠ/ሚኒስትሩ በጉባኤው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፣ “ሁላችንም በጋራና በፍቅር መንፈስ፤ ሀገራችንና ህዝባችንን በቅንነት ማገልገል ይኖርብናል” ብለዋል::

በውይይቱ ላይ በሰፊው ከመናገር ይልቅ ለምሑራኑ በቂ ዕድል በመስጠት ሀገሪቷ ወደ ተሻለ ለውጥና ዕድገት የምትሸጋገርበትን መንገድ እንዲያመለክቱ ሁኔታዎችን ያመቻቹት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ይህን መሰሉ ውይይት ወደ ፊት በስፋት እንደሚዘጋጅ አረጋግጠዋል::

በቅርቡ ከኤርትራ ጋር ዕርቅ የፈጠሩት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፤ የሀገራችንን ምሑራን ባነጋገሩ ማግሥት በተባበሩት አረብ ኤመሬትስ መዲና አቡዳቢ፤ ከፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈ ወርቂ ጋር ተገናኝተዋል:: መሪዎቹ፣ በአልጋ ወራሹ ልዑል ሼክ መሀመድ ቢን ዘይድ አወያይነት በቀጠናው ጉዳይ ላይ በስፋት የተወያዩ ሲሆን፤ የሁለቱ ሀገራት መሪዎች ከሃያ ዓመት በኋላ የሀገራቱ ግንኙነት እንደአዲስ እንዲጀመር ማድረጋቸውን ተከትሎ፤ ልዑሉ የሀገራቸውን ከፍተኛ ሜዳልያ በሽልማት መልክ አበርክተውላቸዋል::

በተጨማሪም፣ ለሁለቱ መሪዎች የወርቅ ሜዳልያ የሸለመው የተባበሩት አረብ ኤመሬትስ መንግሥት፤ በዚህ ዓመት ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በወርቅ ሜዳልያ ከተሸለሙት መካከል ለ50 ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል ሰጥቷል::

# በቃሊቲና በክልል ማረሚያ ቤቶች እስረኞች አመፁ!

ካለፈው ሳምንት መገባደጃ ጀምሮ በአዲስ አበባ ቃሊቲና ቂሊንጦ ማረሚያ ቤቶች እስረኞች፣ “በምህረትና ይቅርታ አዋጁ ተጠቃሚ መሆን አለብን” በሚል አመፅ ቀስቅሰው ሰንብተዋል:: በተለይም፣ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት አመፁን ተከትሎ የእሳት ቃጠሎ የተነሣ ሲሆን ግርግሩ በተፈጠረበት ወቅት ተደጋጋሚ የተኩስ ድምጽ መሰማቱ ብዙዎችን አሳስቧል::

እስከ ረቡዕ ሐምሌ 18 ቀን ምሽት ድረስ፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የማረሚያ ቤቱ ሰዎች መረጃ ለማግኘት ያደረግነው ጥረት ባይሳካም፤ ለታሳሪዎች ስንቅ ሊያደርሱ ሲመላለሱ ያገኘናቸው ግለሰቦች እንደገለፁልን፤ በተለይም፣ ማክሰኞ ዕለት አምቡላንሶች በብዛት ወደ ማረሚያ ቤቱ ሳይረን እያጮሁ ሲገቡና ሲወጡ መመልከታቸውን ገልፀውልናል:: ቤተሰብ፣ ስንቅ እንዳያቀብልና ከማንም ጋር እንዳይገናኝ መደረጉ በታሳሪዎች ላይ ስለደረሰው የጉዳት መጠን አሁንም በግልፅ ማወቅ አልተቻለም::

በተመሳሳይ ሁኔታ “ከእስር መፈታት አለብን” በሚል በተነሡ ግርግሮች ሳቢያ በደብረ ማርቆስ፣ በፍኖተ ሰላምና በወልድያ ከተሞች በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች የእሳት ቃጠሎ ተነሥቷል:: “የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ፣ የምሕረት አዋጁን ተከትሎ በሰጡት አስተያየት ውስጥ እንዴት አልተካተትንም?” በሚል ከፍተኛ ተቃውሞ ያስነሡት በተጠቀሱት ከተሞች ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ያሉ እስረኞች ከፀጥታ ኃይሎች ጋር ግጭት ውስጥ መግባታቸው ታውቋል::

# አርበኞች ግንቦት ሠባት በኤርትራውያን ተሸለመ!



በኢትዮ-ኤርትራ የሠላም ስምምነት ላደረገው አስተዋፅዖ አርበኞች ግንቦት ሠባት ፓርቲ በኤርትራውያን ፌስቲቫል ላይ ሽልማት ተበርክቶለታል::

ለ20 ዓመታት ያህል ተራርቀው የቆዩት ሁለቱ ሀገራት፤ ወደ ዕርቀ ሠላም እንዲመጡ የተለያዩ አካላት ቀደም ባሉት ጊዜያት ጥረቶች ተደርገው እንደነበር የገለፁት በዋሽንግተን የኤርትራ ፌስቲቫል አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት፤ የዚህ መልካም እንቅስቃሴ አጋር የሆነውና የሁለቱ ሀገራት ህዝቦች ለዘመናት በቆዩበት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ዳግም ወደነበረበት እንዲመለስ ካደረጉ ድርጅቶችና ተቋማት መካከል አንዱ አርበኞች ግንቦት ሠባት ንቅናቄ መሆኑን አረጋግጠዋል::

በዲሲ በተካሄደው የኤርትራውያን ፌስቲቫል ላይ፤ ንቅናቄውን በመወከል የተገኙት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣ ሽልማቱን የተቀበሉ ሲሆን፤ በኤርትራውያኑ ፌስቲቫል ላይ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጠና ስላሉ የሠላም ሂደቶች፤ የሁለቱ ሀገራት ዘለቄታዊ ግንኙነቶች ላይ ጥልቅ ውይይት ከመደረጉም ባሻገር፤ ምሑራን ጥናታዊ ጽሑፎችን በመድረኩ አቅርበዋል::

# “ጉዞ ለሰላምና ለፍቅር ችቦ” በቅርቡ ይለኮሳል!

በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች እየተከናወኑ ያሉ ግጭቶች እንዲበርዱና ህዝቦች በቀጣይነት ሙሉ ለሙሉ ከብሔር ተኮር ነውጦች ርቀው ለሠላምና ለፍቅር እንዲሠሩ መልዕክት የሚያስተላልፈው ችቦ በቅርቡ በተለያዩ ክልሎች እንደሚለኮስ ታውቋል::

ሀገራዊ ስሜት ባላቸው ግለሰቦች ተነሣሽነት የተዘረጋው ይህ የዕርቅና የሠላም ጉዞ፤ በኦሮሚያና ደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙ ከተሞችን እንደሚያካትት የገለፁት አዘጋጆች በጎንደርና በወልድያም ተመሳሳይ ሥራ እንደሚኖር አስታውቀዋል::

ጋዜጠኞችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተው የሰላም ቡድኑ ዋነኛ ዓላማ፤ ሠላምና ፍቅርን በመስበክ፣ የዴሞክራሲን ገፅታ ለህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር፤ ከዚህ በኋላ የጎጠኝነት ስሜትን ተንተርሰው የሚሠሩ አላስፈላጊ የእርስ በእርስ ግጭቶች እንዲቆሙ ተቀዳሚ ተግባሩ እንዲሆን፤ የአስተባባሪ ኮሚቴው አባል አበበ ቀስቶ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጿል::

አዋሳ፣ ወላይታ፣ ወልቂጤ፣ ወሊሶ፣ አምቦና ሌሎች የኦሮሚያ ከተሞችን መነሻ የሚያደርገው፤ በቀጣይነት ከስፖንሰሮች በቂ ድጋፍ ከተገኘ፤ እስካሁን ከተደረገው የኢትዮ-ኤርትራ ፖለቲካዊ ግንኙነት በዘለለ፤ ሁለቱን ህዝቦች በቀጥታ የሚያገናኝ የሠላም ችቦ በመለኮስ በአስመራ፣ ምፅዋና አሰብ ትልቅ ህዝባዊ ንቅናቄ እንደሚያደርጉ አዘጋጆቹ ገልጸዋል::

# ሁለቱን ፓትርያርኮች በእኩል ሥልጣን ያስቀመጠ ስምምነት

አቡነ መርቆሬዎስን ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን አራተኛ ፓትርያርክ በነበሩት አቡነ መርቆርዮስ ላይ ባሳደረው ተፅዕኖ ምክንያት ፓትርያርኩ ከሀገር ተሰደው ሲወጡ የተተኩት አቡነ ጳውሎስን ተከትሎ ቤተ ክርስቲያኗ ላለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት በሁለት ሲኖዶሶች የበላይነት ፋክክር ስትታመስ ከርማለች::

ያለፍላጎታቸው በመንግሥት ጫና ወደ አሜሪካ የተጓዙትና በወቅቱ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ቀጥተኛ ተጽዕኖ በተካሄደው የሲኖዶሱ ምርጫ፤ አዲስ የተተኩትን ፓትርያርክ ሹመት በመቃወም አንዳንድ ጳጳሳት አቡነ መርቆርዮስን በመከተል ወደ አሜሪካ አቅንተዋል:: ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ፣ "የሀገር ውስጥ ሲኖዶስ" እና "ስደተኛ ሲኖዶስ" በሚል ስያሜ በሁለት ጎራ ተከፍለው ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ ሲወነጃጀሉ የቆዩበት ጉዳይ ሠሞኑን ወደ ስምምነት ደርሷል::

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ቀን አንሥቶ፣ የሃይማኖት ተቋማት ከሙስናና ዘረኝነት በፀዳ መልኩ ተከታዮቻቸውን እንዲያገለግሉ ከማሳሰብ ባሻገር፤ "የሃይማኖት አባቶች ፍትሕ ሲጓደል፣ ዜጎች ሲበደሉ፣ በግልጽ ተናገሩ፤ መስክሩ" ሲሉ መልዕክት ማስተላለፋቸው ይታወሳል:: ጠ/ሚኒስትሩ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በእስልምና ሃይማኖት ዘንድ ተፈጥረው የነበሩ ክፍተቶችና ሃይማኖታዊ ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ እንዲስተናገዱ በማሰብ፤ የጉዳዩን ባለቤቶች በጋራ በመነጋገር በይቅርታና በፍቅር በመታገዝ ወደ መፍትሔ እንዲያመሩ ዕርቀ ሠላም ፈጥረዋል::

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ለበርካታ ዓመታት በፖለቲካ ሹመኞች ዘንድ ባለ ፍላጎት የተነሣ ወደ ሠላማዊ ስምምነትና አንድነት እንዳይመጡ ተደርገው የከረሙትን ሁለቱን ሲኖዶሶች፤ ዕርቅ እንዲያደርጉ አሸማጋይ የኮሚቴ አባላትን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት አሳስበው ነበር:: በዋሽንግተን ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ባፈው እሑድ ሐምሌ 15 ቀን፣ 2010 ዓ.ም የተደረገው የእርቅ ጉባኤ ሁለቱንም ወገኖች ወደ ስምምነት አምጥቷል::

ከአዲስ አበባ ወደ አሜሪካ የሄዱት ልዑካን ቡድን አባላት ሐሙስ፣ ሐምሌ 12 ቀን ሲደርሱ፤ እዚያ በሚገኙ የሲኖዶስ አባላት የተደረገላቸው መልካም አቀባበል ዕርቀ ሰላሙ በፍጥነት እውን ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነበር:: ያለሦስተኛ ወገን አነጋጋሪነት ለብቻቸው በችግሮቻቸው ላይ በቀጥታ ለመወያየት በሁለቱም ሲኖዶሶች በኩል የተወከሉት አባቶች መወሰናቸውና ተግባራዊ ማድረጋቸው በራሱ፤ ለቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነ ለምዕመናኑ ትልቅ ክብር እንደሆነ ከወዲሁ እየተነገረ ይገኛል::

የሰላምና አንድነት ኮሚቴው እንደገለጸው፣ ሁለቱም ወገኖች ለሦስት ሰዓታት ከተወያዩ በኋላ፤ በቀጣይነት ሲኖዶሱ አንድ ሆኖ በጋራ በሚሠሩበትና ሕዝበ ክርስቲያኑን በሚያገለግሉበት ጉዳዮች ላይ ተስማምተዋል:: "ቤተ ክርስቲያንን አንድ አድርገን መሞት እንደገና መፈጠር ነው" በማለት የልዑካን ኮሚቴው አባላት የሆኑ አባቶች ከወዲሁ ደስታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ::

ሁለቱም ፓትርያርኮች፣ በአንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አመራር የማዕረግ ስምና ወንበር ይፋዊ ዕውቅና ተሰጥቷቸው የሚቀመጡበት ሁኔታ ከወዲሁ እየተዘረጋ መሆኑን የደረሱን መረጃዎች ያመለክታሉ:: በዚህም መሠረት፣ 4ኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ፤ በጸሎት ተወስነው መንፈሳዊውን አገልግሎት ከመፈፀም ባሻገር፤ ቡራኬ የሚሰጡ ሲሆን፣ 6ኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ደግሞ አስተዳደራዊ የሆነውን የቢሮ ሥራ እንደሚያከናውኑ ለማወቅ ተችሏል::

ከ26 ዓመት በፊት፣ አቡነ መርቆርዮስ የተደረገባቸውን መንግሥታዊ ጫና በመቃወምና ከዚያም በኋላ ባለው የአቡነ ጳውሎስ አሠራር ደስተኛ ባለመሆናቸው፤ በተለያየ ጊዜ ለስደት የተዳረጉትን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ወደ ሀገር እንዲገቡና በሚካሄደው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ መሰረት፤ በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በሚገኙ አህጉረ ስብከቶች የሚያገለግሉበት ሁኔታ በዕርቅ ስምምነቱ ላይ ተመቻችቷል:: በተጨማሪም ቀኖናዊ



ሁለቱ ሲኖዶሶች አንድነት በፈጠሩበት ወቅት

እይታ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፤ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር በሚሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ብቻ እንዲፈታና ከእንግዲህ በኋላ የሠላምና የፍቅር መሰረት የሃይማኖት አባቶች ሓላፊነት እንዲሆን በውይይቱ አፅንዖት ተሰጥቶበታል::

በቤተ ክርስቲያኒቱ የተንሰራፋው የሙስናና የዘረኝነት ጉዳይ፣ በቀጣይነት ከምንም በላይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና አዳዲስ ሹመት በማግኘት ወደ ሥልጣን የሚመጡት ሓላፊዎች ከፍተኛ ትግል የሚገጥማቸው በእነዚህ መሰል መንገዶች እንደሆነ ከወዲሁ እየተናገረ ነው:: የአስተዳደር ጉዳዮችን በተመለከተ፣ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት አንሥቶ እስከ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት ድረስ የዘለቀው የአንድ ብሔር የበላይነትና ቤተሰባዊ ሥራ፤ ህዝበ ክርስቲያኑ ባለፉት ዓመታት በሃይማኖት አባቶች ላይ ጣቱን እንዲቀስር ማድረጉን የሚደግፉ አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች፤ ሁለቱ ሲኖዶሶች ወደ አንድነት መምጣታቸው በእጅጉ የሚያስደስት ቢሆንም፤ ከላይ የተቀመጡት ግልፅ የሆኑ ችግሮች በፍጥነት መቀረፍ እንዳለባቸውና የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው የእምነቱ አገልጋዮችም ሊገሰጹ እንደሚገባ ጠቁመዋል::

በእኩል የሓላፊነት ሥልጣን የሁለቱም ቅዱሳን ፓትርያርኮች የሢመተ ፐትርክና በዓል የቤተ ክርስቲያን በዓል ሆኖ እንደሚከበር ታውቋል:: ለዘመናት ተራርቀው የቆዩትንና አንዱ ሌላውን በመወንጀል በቤተ ክርስቲያኗ መልካም ገፅታ ላይ ችግር ሆነው የቆዩት ሁለቱ ሲኖዶሶች በፍጥነት ዕርቀ ሰላሙን ተቀብለው ወደ አንድነት መምጣታቸው ከምዕመናን ባሻገር ታላላቅ የሃይማኖት አባቶችን ጭምር አስደስቷል:: የሰላምና ዕርቅ ኮሚቴ ልዑካን ቡድኑ መሪ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ፤ በተገኘው ውጤት ከመደሰታቸው የተነሣ ስሜታቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው በምስጋና እና በደስታ ዕንባ ሲታጠቡ ታይተዋል::

4ኛው ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ መርቆርዮስ ወደ ሀገር የሚመለሱበት ቀን ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሜሪካ ከገቡ በኋላ ይፋ እንደሚሆን ያመለከተው መረጃ፤ ከ26 ዓመት በኋላ ወደ ሀገር የሚመጡትን ፓትርያርክና ሌሎች ሊቃነ ጳጳሳትን ለመቀበል ከወዲሁ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የተዘጋጀው አቀባባል መርሐ ግብር በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ወይም በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ልዑካን አባቶችን ያካተተውን የሰላምና የአንድነት ኮሚቴ አባላት ባነጋገሩበት ወቅት የሰላም ስምምነቱን እውን አድርገው ከተመለሱ፤ ብዙ ሺህ ታዳሚ በሚገኝበት የሚሊኒየም አዳራሽ የዕውቅናና የምስጋና ፕሮግራም እንደሚያዘጋጁ የገቡትን ቃል ዕውን ለማድረግ ጎን ለጎን ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ለማወቅ ችለናል::

# ሀገር ለዜጎች ዕድል ትስጥ! “መንግሥት የዜጎቹ ሐሳብ ውጤት ነው”

በመላኩ ብርሃኑ

ስለመንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ሲነሣ “መንግሥት አባት ነው” ከሚለው የፊውዳል ሥርዓት ትርክት አንሥቶ “መንግሥት የመጨቆኛ መሣሪያ ነው” እስከሚለው የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ድረስ፤ ብዛት ያላቸው የመንግሥት ምንነት የተተነተነባቸው ፍልስፍናዎች አሉ። ከነዚህ መካከል፣ “መንግሥት የዜጎቹ ሐሳብ ውጤት ነው” የሚለው ፍልስፍና በተለይ ያለንበትን የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሥነ መንግሥት እሳቤ በምሉዕ የሚገልጽና በአብዛኛው በምዕራባውያን ዘንድም ተቀባይነት እንዳገኘ የሚነገርለት የነገረ መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ነው።

“በዴሞክራሲያዊ የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት ባህርይ የሚቀዳው፤ ከሚያስተዳድረው ህዝብ ፍላጎትና ያንን ፍላጎት ለማስፈጸም ከሚወስድ ውክልና አኳያ እንጂ፤ ከኖረው የመንግሥት አስተዳዳሪነት፣ ጨቋኝነት ወይም ገዢ መደብነት ሚና አይደለም” ይላሉ የዘርፉ ምሁራን። በአንጻሩ፣ “መንግሥት የዜጎቹ ሐሳብ ውጤት ነው” የሚለው ፍልስፍናም፤ በስሌቱ፣ “መንግሥትን የሚሠሩት ግለሰቦች ናቸው” ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል። የመንግሥት የዜጎች ሐሳብ ውጤትነት ኃያላን በሚባሉ ሀገራት ጨምሮ በሰለጠኑ ሀገራት መንግሥታት ላይ በተግባር የተገለጸ እውነት ነው።

ለዜጎቹ ክብር የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን፤ የዜጎቹ ሐሳብ የመዋቅሩ አዕማድ፣ አልያም ምሰሶ መሆኑን የሚያምን መንግሥት፤ በዜጎች ያልተገደበ የፖለቲካ ወይም ማህበራዊ ተሳትፎ ያምናል። በቀላል አነጋገር፣ እንዲህ ያለ መንግሥት፣ ዜጎችን ስለደጋፊ ወይም አመስጋኝነታቸው ብቻ ሳይሆን፤ ስለተቺ ወይም ነቀፌታ ሀሳባቸው ጭምር ሲል፣ ካሉበት ፈልጎ ወደአስተዳደር መዋቅሩ ያስጠጋል፤ ህዝብ በዜጎች በጎ ሐሳብና ችሎታ እንዲጠቀምም ዕድል ይሰጣል።

> “
> **የእያንዳንዱን ሰው ሕይወት ከቀየሩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ጀርባ ያሉት ግለሰቦች እንጂ፣ ፓርቲዎች አይደሉም። ዛሬ ለዓለም መብራት የሆነው አምፖል፣ የቶማስ ኤዲሰን እንጂ የሀገሩ መንግሥት ግኝት አይደለም። ለዓለም እፎይታ የሆነው የቢልሃርዚያ መድኃኒት ግኝት፣ የፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ እንጂ የአጼው ወይም የደርግ መንግሥታት አይደለም**

እንዳለመታደል ሆኖ ሀገራችንን ያስተዳደሩ መንግሥታት፣ በቃል አቋማቸው ቢያስመስሉትም፤ በተግባር ግን አጠገባቸው እንዳይደርስ አብዝተው ከሚጠነቀቁባቸው ነገሮች አንዱ፣ “በመንግሥት አሠራር ውስጥ የሚሰፋ የዜጎች ሚና” ነው። በተለይም ከሚመሩበት የፖለቲካ ርዕዮት በተቃራኒ የቆመ የመሰላቸውን ማንኛውንም ዜጋ፣ ቢችሉ ተሰሚነቱን ለመቀነስ መሥራት፤ ካልሆነም፣ በፊት ለፊት ወይም በዘዴ ከመዋቅራቸው አካባቢ በማግለል ሐሳቡ መዋቅራዊ ቅርጽ ይዞ እንዳይወጣ ማምከንን ዋነኛ ሥራቸው አድርገውት ኖረዋል።

በዚህ ሳቢያ ሀገራችን ብዙ ልትጠቀምባቸውና ልታተርፍባቸው የምትችላቸው ከዜጎች የሚመነጩ ሐሳቦች የተሳትፎ መድረክና የተሰሚነት ዕድል በማጣታቸው ሳቢያ መክነው ቀርተዋል። የሐሳቡ አመንጪና አራማጆችም፣ በግልጽም ይሁን በስውር እስከሕይወት መጥፋት ለሚደርስ ጥቃት ተዳርገዋል። ይህ በሀገራችን መንግሥታት ዘንድ ሰፍኖ የኖረው፣ “የሚያስተዳድሩትን ዜጋ የመፍራት አባዜ” ሁሉንም መንግሥታት ሊባል በሚችል መልኩ ከዴሞክራሲያዊ ይልቅ አምባገነን ባህርይ ይዘው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። የመንግሥታቱ ከመጠን ያለፈ ፍርኃት በሚፈጥረው ጨካኝ ባህርይ የተነሣም፤ ሀገራችን ትውልድ ሊያተርፍባቸው የሚችላቸውን ዕንቁ ዜጎቿን አጥታለች።

ግለሰቦችንና ሐሳባቸውን እጅግ ይፈራ የነበረውና በአምባገነን ባህርይ የተቃኘው ደርግ፣ ከራሱ ውስጥም ይሁን ከውጭ፣ አስተዳደሩን የተቀናቀኑትን ብቻ ሳይሆን፤ ለአስተዳደሩ መሻሻል ገንቢ የመሰላቸውን ሐሳብ የሰጡትን ጭምር በግልጽና በስውር እያስወገደ ተጉዟል። በዚህ መንገድ፣ ሥልጣን ላይ መቆየት የቻለው ግን ለ17 ዓመታት ብቻ ነው። ሁሉንም መንገዶች በኃይል የዘጋውን ደርግን፣ “በራሱ ቋንቋ አነጋግሮ” በትጥቅ ትግል የገረሰሰው ኢህአዴግ በበኩሉ፣ “ዴሞክራሲያዊ ▶



ቴዎድሮስ ካሳሁን(ቴዲአፍሮ)



ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ



ስለሺ ደምሴ (ጋሽ አበራ ሞላ)

መንግሥት" መመስረቱን አውጆ፤ ሥልጣን ከያዘ 27 ዓመታት ተቆጥረዋል። ዜጎችን ከማሳተፍና 'በዜጎች ሐሳብ የተፈጠረ መንግሥት' ሆኖ ከመውጣት አንጻር ሲመዘን ግን የኢህአዴግ መንግሥት፣ "በተለየ ኖታ ተመሳሳይ ሙዚቃ ከመጫወት አልዘለለም" የሚል ትችት ይሰነዘርበታል። ለዚህም ብዙ መላ ምቶች ይሰነዘራሉ።

## ራስን ማፍቀር፣ ዜጎችን መዘንጋት

ተቺዎች የኢህአዴግ መንግሥት ከደጋፊዎቹ ውጪ የሆኑትንና ከፖሊሲ አወቃቀር እስከ አተገባበር ያሉ ሂደቶቹን የሚተቹ ዜጎችን ከነሐሳባቸው ወደመዋቅሩ ሳያስቀርብ የኖረበትን ምክንያት ራሱን ከማፍቀር አባዜ (ናርሲሲዝም) ጋር ያያይዙታል።

በግሪክ አፈ ታሪክ፣ የወንዝ አምላክ የነበረው ሴፊስስ ናርሲስስ የሚባል ወንድ ልጅ ነበረው። ይህ ልጅ በመላው ግሪክ በመልከቀናነቱ የታወቀ ዝነኛ እንደነበር ይነገራል። ነገር ግን ያንን መልከ መልካምነቱን ራሱ እንዳያይ ፍጹም ክልከላ ተደርጎበት ነበር። ክልከላው በስህተት እንኳን መልኩን ውሃ ውስጥ ተንጸባርቆ እንዳይመለከት በላዩ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እስከማድረግ የደረሰ ነበር። ሆኖም ናርሲስስ አንድ ቀን በድንገት ወደወንዝ ውኃ ውስጥ ሲያጎነብስ የገዛ መልኩን በማየቱ ከራሱ ምስል ጋር በፍቅር ወደቀ። በዚህ ሳቢያ፣ ተደብቆ ወንዝ እየወረደ መልኩን ማየት የሁሌም ሥራው ሆነ። አንድ ቀን፣ እንደለመደው በቅርበት ወደውኃው አጎንብሶ መልኩን በሚያይበት ጊዜ፤ በዚያው በመስመጡ ለሞት መብቃቱን አፈ ታሪኩ ይነግረናል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ ከራሱ ጋር ፍቅር የያዘው ሁሉ፣ "ናርሲሲስ" ይባል ጀመረ። በተጋነነ የራስ አስፈላጊነት እሳቤ (በራስ ፍቅር) የመውደቅ በሽታም በሳይንሱ "Narcissistic Personality Disorder (NPD)" በመባል ይታወቃል።

ከሌኒን ቦልሼቪክ ፓርቲ ጀምሮ፣ ራሳቸውን አብዮታዊ ብለው የሚጠሩ ፓርቲዎች መገለጫ፤ ይኸው ራሳቸውን አይተኬ አድርገው ማሰብና በአባሎቻቸውም ከልክ በላይ መወደዳቸው ነው። ይህ ከፓርቲው ውጪ ያሉ ዜጎችን እና ሐሳባቸውን በበጎ ለማየት ዕድል የማይሰጠው በራስ ፍቅር መውደቅ፤ ውሎ አድሮ ፓርቲዎቹንም፣ ሀገራቱንም ዋጋ አስከፍሏቸዋል። በሀገራችን እንኳን፣ የ1966ቱን ህዝባዊ አመጽ ተከትለው ከተፈጠሩት ግራ ዘመም ፓርቲዎች አንዱ የነበረው ኢህአፓ፣ "ስህተት የማይሠራ ፓርቲ" ተብሎ፤ አባላቱም ከአብዮታዊው ፓርቲ ጋር በጥልቅ ፍቅር በመውደቃቸው፤ አስተሳሰቡ በስተመጨረሻ ዋጋ አስከፍሎታል። ሕይወት ተፈራ "Tower in the Sky" በሚለው መጽሐፏ እንዳሰፈረችው፤ ኢህአፓ፣ ከውስጥም ከውጭም የሚመጡ የተለዩ ሐሳቦችን "በጠላትነት"፣ ሐሳብ አመንጪዎችንም "በአንጃ" በመፈረጁ ከፍተኛ ዋጋ እንዳስከፈለው በምሬት ጽፋለች።

አሳዛኙ ነገር፣ ከድህረ 1966 ፖለቲካ የተማሪዎች ንቅናቄ ርዕዮት የተቀዳውና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው አግላይ አስተሳሰብ፤ ከዚያ በኋላ ሥልጣን ላይ የወጡ ፓርቲዎች፣ ከራሳቸው አባላት ውጪ ለዜጎች ሐሳብ ዕድል የማይሰጡ ሆነው እንዲቀረጹ አድርጓቸዋል። በዚህ የተነሣም አጥሩን ሰብረው ብቅ ለማለት የሞከሩ ዜጎች እየተኮረኮሙ መክነዋል። በውጤቱም ሀገር እና ህዝብ በተለዩ ሐሳቦች ለመተዳደር ወይም ለመገልገል የነበራቸውን ዕድል አሳጥቷቸዋል።

## "ዓለምን የለወጡ ግለሰቦች ናቸው"

በየትኛውም ሀገር የሥልጣኔ ታሪክ፣ በሳይንስም ይሁን በኪነ ጥበብ አልያም በፖለቲካ መስክ፤ ለሀገራቸው ከፍተኛ ቁም ነገር የሠሩ ግለሰቦች ወይም ዜጎች እንጂ፤ ቡድኖች፣ ፓርቲዎች ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አይደሉም። የእያንዳንዱን ሰው ሕይወት ከቀየሩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ጀርባ ያሉት ግለሰቦች እንጂ፣ ፓርቲዎች አይደሉም። ዛሬ ለዓለም መብራት የሆነው አምፖል፣ የቶማስ ኤዲሰን እንጂ የሀገሩ መንግሥት ግኝት አይደለም። ለዓለም እፎይታ የሆነው የቢልሃርዚያ መድኃኒት ግኝት፣ የፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ እንጂ የአጼው ወይም የደርግ መንግሥታት አይደለም። በስዕል ጥበባቸው ዓለም የሎሬት ሜትር አርቲስትነት ክብር ሰጥቶ፤ ዛሬ ድረስ በየመድረኩ የሚጠራው፣ አፈ ወርቅ ተክሌን እንጂ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ አይደለም።

እንደአንዳንድ ሐያስያን ትንተና፣ ፖለቲከኛ ማለት አምራችና ፈጣሪ ሳይሆን፤ ሌሎች ያገኙትንና የፈጠሩትን በሥልጣኑ ተጠቅሞ የሚቆጣጠር፣ በዚያም ኃይል የሚቀዳጅ አካል ነው። በዚያ መልኩም ቢሆን (ከጥቂት መገለጫዎች በቀር) ከሀገራችን ፓርቲዎች ውስጥ የዜጎችን ግኝት እና ሐሳብ በሥራ ላይ ለማዋልና ራሱን ለማጉላት ፍላጎት ያለው ፖለቲከኛ ሳይፈጠር መኖሩ አስገራሚ ተቃርኖ ነው።

## የመለስ ዜናዊ ቃል "የተነገረው ግን ያልተተገበረው"

በብዙዎች ዘንድ፣ "ዜጎች፣ ከመንግሥት ፖለቲካ በተቃራኒ ቆመውም እንኳን ቢሆን፤ ለሀገራቸው ሁለንተናዊ መሻሻል የሚያበረክቱት የሐሳብም ሆነ የተግባር አስተዋጽዖ ለህዝብ እስከጠቀመ ድረስ ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል" የሚል እምነት አለ። በአንድ ወቅት፣ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ራሳቸው፣ "ማንም በሙያው አስተዋጽዖ ማበርከት የሚችል ሰው፣ የኢህአዴግ አባል ባይሆንም፤ ፖሊሲውን የሚቃረን ተግባር እስካልፈጸመ ድረስ ማገልገል መብቱ ነው" የሚል ቃል በአደባባይ ቢናገሩም፤ ፓርቲያቸውም ሆነ ራሳቸው ይህንን ቃል በበቂ መጠን በተግባር ሲተረጉሙት ግን አልታዩም። በወቅቱ፤ የአቶ መለስ ቃል በብዙዎች ዘንድ፣ "ኢህአዴግ ለዜጎች ተሳትፎና ሐሳብ ጆሮና ልብ ይሰጣል" በሚል ግምት ተስፋ አጭሮ ነበር። በወቅቱ፤ በማህበራዊው፣ በኢኮኖሚውም ይሁን በፖለቲካው መስክ ጠቃሚ ነው ያሉትን ሐሳብና ምክር ይዘው ወደፓርቲው ብቅ ያሉ ወይም በሆነ አጋጣሚ የተነሱ ግለሰቦች፤ መጨረሻቸው፣ "ከፓርቲው ጋር ጥርስ መናከስ" ሆኖ ሲቀር ታይቷል።

## ዕውቅና መንፈግና ማግለል

በአቶ መለስ ዘመን፣ በፓርላማ መቀመጫ

የነበረው የኢዴፓ ሊቀ መንበር አቶ ልደቱ አያሌው፤ ፓርቲያቸው ያቀረባቸውን እንደኮንዶሚኒየም ግንባታ እና መሰል ሐሳቦች፣ "ኢህአዴግ የራሱ አስመስሎ ለምርጫ ዘመን ፍጆታ ተጠቅሞባቸዋል" ብለው ካሰሙት ክስ ባለፈ፣ ኢህአዴግ እንደፓርቲ የግለሰቦችን ሐሳብ፣ በመንግሥቱ ዕቅድ ውስጥ አስገብቶ ተግባራዊ የማድረግ እውነት ማረጋገጫ ምስክር የለውም፡፡ ይልቅስ፣ በተቃራኒው ሐሳብ ይዘው መጥተው፤ ነገር ግን ተቀባይ አጥተው በመንግሥት የተገለሉ፣ እንደአርቲስት ስለሺ ደምሴ ያሉ ዜጎች ስም በምሳሌ የሚቀርብበት ነው፡፡ ከመገለል አልፎ፣ "መንግሥታዊ ጫና ተደርጎበታል" የሚባለው ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን፤ በአንጻሩ፣ መንግሥትን በጎ ጎን ካመላከቱ ከብዙ የአንድነትና የፍቅር ሰባኪዎች ተርታ ቀዳሚ አድርጎ መጥቀስም ይቻላል፡፡

አርቲስት ስለሺ ደምሴ (ጋሽ አበራ ሞላ) ለረጅም ዘመን ከኖረበት አሜሪካ ወደ ሀገሩ ሲመለስ የቆሸሸችውን አዲስ አበባ ማጽዳት ነው የጀመረው፡፡ ስለሺ ከተማዋን ለማጽዳት ወጣቶችን በማሰባሰብ አካፋ ተሸክሞ ቆሻሻ ሲጠርግ በመዋሉ ግን፤ በወቅቱ ከተማዋን ሲያስተዳድሩ በነበሩ ባለሥልጣኖች ዘንድ ከድጋፍና ማበረታቻ ይልቅ፣ ዕውቅና መነፈግንና መገለልን ነበር ያተረፈው፡፡ አርቲስቱ ከፖለቲካ ዓላማ ውጪ፣ እንባ


ረ/ፐ ነብዩ ባዬ


ሠርፀ ፍሬ ስብሐት

አውጥቶ እያለቀሰ፤ መንግሥት ችላ ብሎት የኖረውን የከተማ ጽዳት ነገር መናገሩ፣ የከተማዋ ከንቲባ ያልሠሩትን ሥራ መሥራቱ፣ በባለሥልጣናቱ ዘንድ የተወደደለት አልመሰለም፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተስፋ ቆርጦ፣ አካፋውንና መጥረጊያውን እንዲጥል ጫና ሊደረግበት መቆየቱም ተነግሯል፡፡ ይህ ማግለል፣ ስለሺን ቀስ በቀስ ከጀመረው ሥራ እንዲርቅም አድርጎታል፡፡ ከመጸዳጃነት አላቅቆ ወደ መዝናኛነት የለወጣቸው፤ የባምቢሱን፣ "መንገድ ማረፊያ" የፒያሳውን፣ "ቸርቸል ቪው" እንዲሁም የራስ መኮንን መዝናኛ ማስታወስ ለዚህ በቂ መገለጫ ነው፡፡ ዛሬ ሁሉም ፈርሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ውስጥ፣ በግለሰብ ደረጃ የህዝብ ንቅናቄ (ፐብሊክ ሞቢላይዜሽን) በመፍጠር ረገድ የስለሺ ደምሴን ያህል የተሳካ ሥራ የሠራ አለመኖሩ እየታወቀ፣ እውቅና መስጠት ቀርቶ በተቃራኒው መገለሉ፤ ለአርቲስቱም ይሁን ለብዙ ደጋፊዎቹ ጥያቄ ሆኖ ኖሯል፡፡ በሌሎች ሀገራት ቢሆን ኖሮ፣ ይህ ማህበራዊ አክቲቪስት፤ ምናልባትም የመዘጋጃ ቤቱ የጽዳትና የውበት ኤጀንሲ ዳይሬክተርነት ቦታ፣ ከእርሱ በቀር ሌላ ተሿሚ አያየውም ነበር፡፡

ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በተራው እንደዝነኛ ዘፋኝ ብቻ ሳይሆን፤


ዲ/ን ዳንኤል ክብረት

የብሔራዊ አንድነትና ፍቅር ሰባኪ፣ አርበኛ አድርገው የሚስወዱት አድናቂዎቹ በርካቶች ናቸው፡፡ በተለይ ሦስተኛ አልበሙን፣ "ጃ ያስተሰርያል"ን ሲሠራ፤ ይህ ለሀገር የሚጠቅም ሐሳብ አፍላቂነቱ ጎልቶ ወጥቷል፡፡ ያም ሆኖ፣ መንግሥት አልበሙን በበጎ ዐይን አልተመለከተውም፡፡ በተለይ፣ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ሰሞን፤ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዓይነት የፖለቲካ ሰዎች፣ ዘፈኑንና አርቲስቱን በአደባባይ አድንቀው መናገራቸው፤ አርቲስቱ "አይደለሁም" ቢልም የፓርቲው አንጋፋዎች ጭምር ግን "ፖለቲካ አቀንቃኝ" አድርገው ስለውታል፡፡ በርካቶች እስከዛሬ እንደሚያምኑትም፣ "አርቲስቱ በገጭቶ ማምለጥ ወንጀል ሰበብ እስር ቤት የወረደው የተቀነባበረ የወንጀል ድራማ ተሠርቶበት ነው፡፡" ቴዲ አፍሮ፣ "ጥቁር ሰው" እና "ኢትዮጵያ" አልበሙ ተመሳሳይ ሀገራዊ አንድነትን የሚሰብክ በመሆኑ፤ አሁንም በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ አድርጎታል፡፡ በኢትዮጵያና ኤርትራ ሰላም ላይ የሠራቸው ዘመን አይሽሬ የጥበብ

ውጤቶቹም፤ የሰላም፣ የአንድነትና ይቅር የመባባልን እሴቶች ጠቃሚነት ይሰብካሉ፡፡ ይህንን ሐሳብ ተቀብሎ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ፤ ልጁን እንደፖለቲከኛ ማግለልና በመንግሥት ፕሮግራሞችና ሚዲያዎች ላይ ስሙን ከመጥራት መሸሽ ግን፤ በጊዜው፣ "ለአንድ ገዢ ፓርቲ የመመጥን ባህርይ አልነበረም" ተብሎም ተተችቷል፡፡

## መንግሥት የዜጎች ሐሳብ ውጤት የሆነባቸው ሀገራት

አሜሪካ፣ ዓለምን የምትመራበት ጥበብ፤ ከዜጎቿ አልፎ ከሌሎች ሀገራት ዜጎች ጭምር የተቃረመ ስለመሆኑ የምትመሰክረው ለራሷ፣ "ሁሉን የማቅለጫ ማሰሮ = The Melting Pot" የሚል ተለዋጭ ስም በመስጠት ጭምር ነው፡፡ በየወቅቱ የነበሩትን የአሜሪካ መንግሥታት የመሩ ፕሬዝዳንቶች የሚቀናቀኑዋቸውንና አስተዳደራቸውን የሚነቅፉትን ዜጎች ጆሯቸውን ሰጥተው በማድመጥ፣ ለሐሳብ አመንጪ ዜጎች ቦታ በመስጠታቸው፤ የሚመሩትን መንግሥት ለስኬት፣ ሀገራቸውንም ለትርፍ አብቅተዋል፡፡

በእንዲህ ዓይነት መልኩ ተጋብዘው፣ አሜሪካን ካገለገሉ ሰዎች አንዱ፤ ዋልተር ሊፕማን ነው፡፡ ሊፕማን፣ ዓለም አቀፍ ዝና ያለው ጋዜጠኛ ሲሆን፤ በ60 ዓመታት የሙያ ቆይታው በጋዜጠኝነት ዓለም ከፍተኛ ማእረግ የሚሰጠውን የፑሊትዘር ሽልማት ሁለት ጊዜ ያገኘ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው በኒዮርክ ሄራልድ ትሪቢዩን ጋዜጣ፣ "ዛሬና ነገ = today and tomorrow" የሚል ርእስ በተሰጠው ዓምድ ላይ በሚያቀርባቸው ተከታታይ ጽሑፎች፤ እንዲሁም "ዘ ኒው ሪፐብሊክ" በሚባል ሊብራል መጽሔት ላይ በሚያሰፍራቸው ነጻ አስተያቶች ሳቢያ ታዋቂ ሆኖ ነበር፡፡ ዋልተር ሊፕማን፣ በነዚህ ሁለት የፕሬስ ውጤቶች ላይ የሥራ ሰዓት 8 ሰዓት ብቻ እንዲሆን፣ ለሰራተኛው መብት መጠበቅ ሲባል የሰራተኛ ማህበራት እንዲመሰረቱ፣ በሴቶች ላይ የሚደረገው ጭቆና እንዲቀር ሽንጡን ገትሮ ተሟግቷል፡፡ የአሜሪካ መንግሥት የሊፕማን ሙግቶች ህዝባዊ መሰረት እንዳላቸው በማየት፣ ሁሉንም ሐሳቦቹን ተቀብሎ ተግባራዊ አድርጓቸዋል፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን፤ ሊፕማን፣ በመንግሥት ላይ በተደጋጋሚ ጊዜ የሚያነሣቸውን ትችቶች መሰረት በማድረግ፤ በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ዊድሮው ዊልሰን፣ በሊፕማን ሀሳብ መነሻነት፤ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፣ አሜሪካ ውስጥ የተካሄደውን የሰፈራ እቅድ እና የመንግሥታቱ ህብረት (ሊግ ኦፍ ኔሽን) ምስረታ እቅድ አውጥተው ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ ፕሬዝዳንት ዊድሮው፣ የዋልተር ሊፕማንን ሐሳብ መጠቀም ብቻ ሳይሆን፤ ራሱን ሊፕማንን "ቬርሳይልስ ትሪቲ" ለተባለው ስምምነት የአሜሪካ ተደራዳሪ አድርገው በመሾም እስከመላክ ደርሰዋል፡፡

ሌላው፣ መንግሥት ጠርቶት ሀገሩን ያገለገለው ታዋቂ አሜሪካዊው የታሪክ ምሁር፣ የቤተ መጻሕፍት ባለሞያና ጸሐፊ፤ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቦርስቲን ነው፡፡ ቦርስቲን፣ እ.ኤ.አ ፌብርዋሪ 28 ቀን 2004 ሲሞት፤ አሜሪካውያን፣ "ዛሬ የአሜሪካ እውቀት ተሰብስቦ መቃብር ገባ" ነበር ያሉት፡፡ ዳንኤል ቦርስቲን በስፋት የሚታወቀው የፑሊትዘር ሽልማት ያገኘበትን፣ "The American" የተሰኘ የአሜሪካ ታሪክ በሦስት ተከታታይ ጥራዝ ጽፎ ለኅትመት በማብቃቱ ነው፡፡ መጽሐፉ፣ የአሜሪካን ህዝብ ታሪክ ብጥር አድርጎ ከመግለጽ አልፎ፤ የአሜሪካውያን

ራስን ከሌላ አስበልጦ የማየት ባህርይ ቆንጣጭ በሆነ ትንተና ያቀረበበት ነው፡፡

ቦርስቲን፣ በአሜሪካ ህዝብ ዘንድ ታላቅ ዋጋ የሚሰጠውን ይህን መጽሐፍ የጻፈው ግን፤ ከመሬት ተነሥቶ አይደለም፡፡ ባገኘው መድረክ ሁሉ የአሜሪካ ህዝብ በተለይ አዲሱ ትውልድ አንባቢ አለመሆኑን አብዝቶ ይተች ነበር፡፡ ይህም፣ በወቅቱ 38ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በነበሩት ጄራልድ ፎርድ ዐይን ውስጥ ከተተው፡፡ ፕሬዝዳንቱ፤ በ1975 ቦርስቲንን አስጠሩና "መጻሕፍትን ስለምትወድ በተከበረው የኮንግረሱ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በሐላፊነት እንድትሠራ ዕድሉን ሰጥቼሃለሁ" አሉት፡፡ ቦርሲቲን፣ ግብዣውን ተቀብሎ፤ ኮንግረስ ላይብረሪ ውስጥ ሓላፊ ሆኖ እየሠራ ሳለ ነው እንግዲህ እነዚህን የአሜሪካ ሀብት የሆኑ ባለ ሦስት ቅጽ "ዘ አሜሪካንስ" መጻሕፍት ያሳተመው፡፡ ከዚያ በኋላም፣ "ዘ ኢሜጅ" እና ሌሎችንም ብዙ መጻሕፍት ጽፏል፡፡ ቦርስቲን፤ እስካሁንም በአሜሪካ ህዝብ ዘንድ ለሌላ ያልታየውን ማየት እንደሚችል አንድ ባለምጡቅ አዕምሮ ይቆጠራል፡፡ የአሜሪካ መንግሥትም የዚህን ግለሰብ ሐሳብ እውቅና ሰጥቶ በመጠቀሙ ለሀገሩና ለህዝቡ ዘመን የሚሻገር ትርፍ አስገኝቷል፡፡

የማህተማ ጋንዲ ሀገር የሆነችው ህንድ፣ ሌላዋ ለግለሰብ ሐሳብና ተግባር ቦታ የምትሰጥ ሀገር ናት፡፡ የጋንዲ የትውልድ መንደር ውስጥ በሚገኘውና አሁን ሙዚየም በሆነው የማህተማ ጋንዲ መኖሪያ ቤት ግድግዳ ላይ፤ በአንድ ቱሪስት የተጻፈ ጥቅስ በጉልህ ይነበባል፡፡ "የሚቀበልህና እውቅና ሰጥቶ የሚጠቀምብህ ካለ፣ እንደኔ ግቢ ብትጠርግም፤ እንደ ጋንዲ ህዝብ ብትመራም ሀገርን ትጠቅማለህ" ይላል፡፡ ቱሪስቱ ግቢውን ሲጠርግ ያገኘውን ህንዳዊ፣ "ስንት ይከፈልሃል?" ብሎ ሲጠይቀው፤ ህንዳዊው፣ "ጋንዲ ለእኛ እኩልነትና ነጻነት ብሎ ይህን ሁሉ መከራ ሲቀበል፤ ተከፍሎት አይደለም" የሚል መልስ ስለሰጠው፣ በዚያ ሐሳብ ተደንቆ ያሰፈረው ማስታወሻ ነው ዛሬም ድረስ የህንዶች መገለጫ የሆነው፡፡

በህንድ ታዋቂ የሆነውና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞች ያሉት እጅግ ግዙፉ "አሞል የወተትና የወተት ውጤቶች ማምረቻ ህብረት ሥራ ማህበር" አሞል፣ በሚባሉ ሰው የተመሰረተ ሲሆን፤ ግለሰቡ ሐሳብ ሲያቀርቡ፣ ተቀብሎ እውን እንዲያደርጉት የረዳቸው ደግሞ የህንድ መንግሥት ነው፡፡ ዛሬ፣ "አሞል" የዓለምን ህዝብ ሢሦ የያዘችውን ህንድ፤ ዘጠና በመቶ የወተትና ከ200 በላይ የወተት ውጤቶች አቅርቦት ይሸፍናል፡፡

በቅርቡ፤ ላንድሮቨር ኩባንያን የገዛውና ከመኪና እስከ ስኒ ማምረት፣ ከኢንዱስትሪ እስከ ታላላቅ ሆቴሎች ያልተሰማራበት ዘርፍ የሌለው "ታታ ኩባንያ"፤ በተመሳሳይ፣ "የህንድ ሌላ ስም" ለመባል የበቃ ኩባንያ ነው፡፡ የዚህ ኩባንያ መሥራች፣ "ታታ" የተባሉ ግለሰብ ሲሆኑ፤ ይህንን ድርጅት በመንግሥታቸው እየታገዙ፣ በረጅም ራእይ ቆርቁረውትና የእርሳቸውና የቤተሰባቸው ሳይሆን፤ የህንድ ህዝብ ንብረት አድርገውት ነው ያለፉት፡፡ ታታ፣ ዛሬ መንግሥት እንደራሱ ተቋም በሚመድባቸው ሐላፊዎች እየተመራ፤ የህንድን ስም በዓለም ዙሪያ የሚያስጠራ "ብራንድ" ሆኗል፡፡ "ህንድን ለዚህ ኃያልነትና እድገት ያበቋት፣ መንግሥታት ሳይሆኑ ግለሰቦች ናቸው" ብለው የሚናገሩት፤ በነዚህ ግለሰቦች የተሠራ ታሪክን በምሳሌ እያብራሩ ነው፡፡ የጃፓኑ "ቶዮታ" እና የኮሪያው "ሳምሰንግ"ም ዛሬ የሀገር ያህል ስማቸው የሚታወቅ፤ ነገር ግን ከብዙ በጥቂቱ የየሀገራቱ ዜጎች ሐሳብና የመንግሥታቸው ትብብር ውጤት የሆኑ ተቋማት ናቸው፡፡

# "በሀገራችን መንግሥታት ዘንድ ሰፍኖ የኖረው፣ "የሚያስተዳድሩትን ዜጋ የመፍራት አባዜ" ሁሉንም መንግሥታት ሊባል በሚችል መልኩ ከዴሞክራሲያዊ ይልቅ አምባገነን ባህርይ ይዘው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል

## በዜጎች የማመን ለውጦች በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ዘመን

"በሀገሪቱ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ ቁጣ ተንተርሼ ባካሄድኩት ጥልቅ ተሐድሶ፣ መጠነ ሰፊ ለውጥ ለማድረግ ተዘጋጅቻለሁ" ያለው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እየተመራ፣ እስካሁን የወሰዳቸው እርምጃዎች፤ ላለፉት 27 ዓመታት ተመዝግቦ የማያውቅ አንጻራዊ ሀገራዊ መግባባት እንዳመጣ ተመስክሮለታል፡፡ በተለይም፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአመራር ፍልስፍና፤ የህዝቡ የዘመናት ፍላጎት ውጤትና የጥያቄውም መልስ በመሆኑ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ዛሬ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ፣ የህዝቡ ድጋፍ ያልተለየው ለውጥ ለማስመዝገብ በቅተዋል፡፡ በውጤቱም፣ በሰላምና በልማት በኩል ሰፊ ሥራ የሚጠብቃቸው ቢሆንም፤ በየዕለቱ አዳዲስና በፈጣን ግስጋሴ የታጀቡ ዓበይት ተግባራትን በማከናወን የተጠራቀመውን የኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ጥያቄ በመመለስ ላይ ይገኛሉ፡፡

ከነዚህ እርምጃዎቻቸው መካከል (በሚፈለገው መጠን ባይሆንም) ከፓርቲው ውጪ ያሉ እውቀትና ችሎታ ያላቸውን ዜጎች፤ ወደመንግሥት ሓላፊነት ቦታዎች ለማምጣት የተገበሯቸው ጅምሮች በብዙኃኑ ዘንድ፣ "መንግሥት የዜጎችን ሐሳብ ማድመጥና መጠቀም ጀምሯል" የሚል ተስፋ እንዲፈነጥቅ እና እርሳቸውም አድናቆት እንዲያገኙ አድርጓቸዋል፡፡ ከነዚህ ዜጎች መካከልም፣ የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራዎች ድርጅት ዳይሬክተር የተደረገውን አቶ ሠርጸ ፍሬ ስብሐትን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የተሾመውን ረ/ፕ ነብዩ ባዬን፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቦርድ አባል ተደርጎ የተሾመውን ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን ምሳሌ አድርጎ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ፣ ከአባላቱ ውጪ ሹመት ከማያስብብት ዘመን ተላቅቆ፤ ወደዜጎች ዐይኑን በጣለበት በዚህ ጊዜ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የተቋማት ሓላፊ ተደርገው የተሾሙት እነዚህ ሦስት ግለሰቦች፤ በየሙያቸው የህዝብን እውቅናና አክብሮት ያተረፉ ሲሆኑ፤ በተመደቡበት መዋቅር ውስጥ ደግሞ፣ አዲስ ለውጥ እንደሚያመጡ ይታመናል፡፡ ይህ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እርምጃ በፓርቲው የሹመት ሂደት ውስጥ ቀዳሚ ዐይን ገላጭ ለውጥ ተደርጎ መወሰድ የሚችል ነው፡፡

ያም ሆኖ ወሳኝ የሚባሉ፣ ከፍ ያለ የአካዳሚ እውቀትና የሙያ ልምድ ብቃትን የሚፈልጉ የተቋማት ምደባዎች፤ አሁንም፣ "የፓርቲ ኮታ ማሟያ ከመሆን አላለፉም" የሚል ወቀሳም ይሰነዘራል፡፡ በሶሻል ሚዲያ ሐሳባቸውን የሚሰነዝሩ ሰዎች (ለሁለት ዓመት ብቻ የሚቆይ ቢሆንም) የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባዎችን ሹመት ለዚህ መከራከሪያ ምሳሌ አድርገው ያነሣሉ፡፡ ከዚህ ቀደም፤ ከተማዋ፣ በባለአደራ ቦርድ ስትመራ የሽሽግግሩ ጊዜ ከንቲባ ተደርገው የነበሩትን ብርሃኑ ደሬሳን በመጥቀስ፣ "ያንን ልምድ በማጎልበት መቀጠል እንጂ፣ ዳግም ወደኋላ መመለስ አይገባንም ነበር" ብለው ይከራከራሉ፡- አስተያየት ሰጪዎቹ፡፡ በሌላ በኩል፣ እንዲህ ዓይነት ስፍራዎች ከፍ ያለ የህዝብ ጥያቄ ያለባቸው ከመሆኑና የሙያ ብቃትና ልምድ የሚፈልጉ ከመሆናቸው አንጻር፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይሁንታ፤ የአደረጃጀትና የመዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ተቋቁሞ ያጠናውና ከ2009 ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል ያለው "ተደበላልቀው የሚገኙትን ፖለቲካንና የባለሙያ ሥራዎችን የመለየትን እርምጃ ከግምት ያላስገባ ሹመት ተካሂዷል" የሚሉ ዘገባዎችም ለንባብ በቅተዋል፡፡ የሁሉም ማጠቃለያ "ብቃትና ያላቸው ዜጎች እየተመለመሉ፤ ለውጥ በሚያመጡበት የሥራ ዘርፎች ተመድበው ይሥሩ" የሚል አንድምታ አለው፡፡

ሀገሪቱ፣ የፓርቲ አባላት የኮታ ምደባን ሳይሆን፤ በዘርፉ የካበተ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ዜጎቿን የምትፈልግበት ሰፊና ያልተነካ ቦታ እንዳላት የሚገልጹ ወገኖች፤ በአንጻሩ፣ "በሀገርም ይሁን ከሀገር ውጪ የሚገኙ ለውጥ ለማምጣት የሚችል እውቀትና አቅም ያላቸው ዜጎችም ለነዚህ ቦታዎች መታጨት ይገባቸዋል" በማለት ይከራከራሉ፡፡ በዚህ ረገድ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በውጭ ሀገር የሚገኙ፤ ከኃይል ልማትና ሽያጭ ጋር የተያያዘ ሙያ ያላቸው የተማሩ ኢትዮጵያውያን፤ በበጎ ፈቃደኝነት ሀገራቸውን እንዲያግዙ ያቀረቡትን ጥሪ እንደመልካም መነሻም መውሰድ ይቻላል፡፡

ይህ ጥሪ ተቋማዊ ቅርጽ ከተበጀለትና መዋቅራዊ ከሆነ፤ ዜጎች በበጎ ፈቃድም ይሁን በምደባ፣ ያላቸውን ልምድና እውቀት ተጠቅመው በመሥራት፤ ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ለመጥቀም ከፍ ያለ ፍላጎት እንዳላቸው በተለያዩ መድረኮች እየገለጹ ይገኛሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በአሜሪካ በሚኖራቸው ቆይታ ኢትዮጵያ ታተርፍበታለች ከተባለባቸው ዘርፎች አንዱም ይኸው የተገለለው የሰው ሐብት ወደሥርዓቱ ገብቶ ለማገልገል የመቻሉ ዕድል ነው፡፡ ይህ ልምድ ዳብሮ ተቋማዊ ከሆነም፣ በኢትዮጵያ የሚኖረው ቀጣይ መንግሥት ሁሉንም የሚያግባባ የዜጎቹ ሐሳብ ውጤት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ሀገርን የሚለውጠው ግለሰብ እንጂ፤ ቡድን አይደለምና፡፡

# ያልጠሩ ጉዳዮችና የጠ/ሚኒስትሩ ቀጣይ ፈተናዎች !

ከመቶ ቀናት የእፎይታ ጊዜ፣ ወደ ዋናው የሽግግር ወቅት እየተንደረደረ የሚገኘው የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት፤ ቃል ከተግባር የሚያዋህድበት፣ የህዝብን ስሜትና ፍላጎት ተረድቶ አንገብጋቢ ጥያቄዎችን የሚመልስበት ሰአት ላይ እንገኛለን:: ብዙ ተስፋዎችን ያጫረው የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መንገድ፣ በትክክልም የኢትዮጵያን ዐቢይ ጉዳዮች እውነተኛ እልባት ያበጅላቸዋል ወይ? የሚለው ወሳኝ ነጥብ ግልፅ የሚሆንበት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ቁመናል::

ይቅርታ፣ ፍቅር፣ የአንድነት ስሜት የተዘመሩበትና የተተገበሩበት፣ "መቶ ቀናት" የጠ/ሚኒስትሩ መንደርደሪያና ቀጣይ ሀገራዊ ሥራዎችን ደርዝ ለማስያዝ የሚታሰቡ የመንደርደሪያ ጊዜያት ሆነው ቢታሰቡም፤ እሳቸው ግን ከበቂ በላይ ሠርተዋል:: ባለፉት 27 ዓመታት ውስጥ፣ በየትኛውም የኢህአዴግ ባለሥልጣን ባልታየ መልኩ ተሸርሽሮ የነበረውን የሀገር ፍቅር ስሜት፣ ተበትኖ የከረመውን አንድነት በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ዳግም በማስረጽ ታሪክ የማይረሳው ታላቅ ሥራ አከናውነዋል::

ከታሰበው ፍጥነት በላይ የተጓዘው፣ የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ የፖለቲካ ዕርምጃ፤ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን የሚጋብዝና ተሳትፎአቸውን የሚጠብቅ እንደሆነም በይፋ ተነግሮናል:: ግን የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጥሪ ላይ፣ ቀጣይ ዕጣ ፈንታቸውን በተመለከተ፤ እስካሁን ጥርት ባለ መንገድ ለህዝብም ሆነ ለጉዳዩ ባለቤቶች የተገለፀ አንዳችም ነገር የለም:: ጠ/ሚኒስትሩ ለፖለቲካ ፓርቲዎቹ ያቀረቡት ግብዣ ውስጣዊ ይዘቱ ምን እንደሚመስል ከፓርቲያቸው በኩልም የታየ ፍንጭ አልተገኘም::

ኢህአዴግ፣ በማይረባ ጥቅማ ጥቅም እየደለለ፤ ሰነጣጥቆ ካስቀመጣቸውና በተቃዋሚ "ጭንብል" ሕዝብን ለማደናበር ሲሞክሩ ከነበሩት የተቃዋሚ/የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ ውጭ የሆኑና በተለይም በባህር ማዶ የሚገኙት፣ ህዝብ በእጅጉ የሚጠብቃቸውና የሚያምናቸው የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ወደ ሀገር ቤት ለመምጣት በቂ ዋስትና በሚፈልጉበት ወቅት፤ ፈጥነው ወደሀገር ቤት ገብተው የነበሩ የፖለቲካ ድርጅት አመራሮች፣ ምንም የተጨበጠ ነገር ሳያደርጉና ሳይዙ፤ ወደመጡበት ሹልክ ብለው የተመለሱም እንዳሉ ሰምተናል::

ትልቅና ትክክለኛ የሚባሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ "በምን አይነት ዋስትና ወደ ኢትዮጵያ ሊመጡ፣ ብዙ መሥዋእትነት የከፈሉለትንም ህዝብ እንዴት ሊያገለግሉ ይችላል?" የሚለው በዚህ ወቅት በብዛት የሚስተጋባ የህዝብ ድምጽ ነው:: ኢህአዴግ ለሀገር የሚያስቡ ድርጅቶችን አክብሮና በቅንነት ተመልክቶ፤ ሥልጣኑን የማጋራትና አብሮ የመሥራት ባህል የሌለው ከመሆኑ አኳያ፤ እየቀረበ ያለው ግብዣ፣ "እንዳያማህ ጥራው" እንዳይሆን የሚል ፍራቻ ቢኖር አያስገርምም::

ብዙዎችን በፈጣን እንቅስቃሴያቸው ያስደመሙት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ "ለውጡን ከሚያደናቅፉት ወገኖች የሚገጥማቸው ፈተና ተቋጭቷል" ማለት ባይቻልም፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ለውጥ ፈላጊ ከሆነው ህብረተሰብ ግልጽ የሆኑና ጠንከር ያሉ ፈተናዎች፣ ከፊት ለፊታቸው እንደሚጠብቃቸው ሊያውቁት ይገባል:: ኢህአዴግ የተከተለው ጥገናዊ ለውጥ አሁንም ከላይ በተቀመጡ ጥቂት ግለሰቦች ቀናነት የተገኘ እንጂ በሥርዓቱ ውስጥ የተዘረጋና መስመር የያዘ የለውጥ አሠራር አለመሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም::

ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረው ኢህአዴጋዊ ስሜትና የፓርቲ ፍቅር፣ ዛሬም በሁሉም መንግሥታዊ ተቋማት ላይ በግልፅ እየተንፀባረቀ ይገኛል:: በተለይም፣ ሕብረተሰቡን በቀጥታ የሚያገኙት የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ያሉ ሠራተኞች፤ ከተከተቡት ድርጅታዊ ፍቅር መላቀቅ ተስኗቸው በ"ተደምረናል" ስም ሕዝብን ክፉኛ እያበሳጩ ይገኛሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ "ኢህአዴግ በጥቂቱ ሊሻሻል ይችላል እንጂ፤ ሙሉ ለሙሉ አይቀየርም" ብሎ እንዲያምን የሚያስገድዱት እውነታዎች በርካታ ናቸው::

በየቦታው እየተስተዋሉ ያሉ ግጭቶችን ሥርዓቱ ጥሎ ያለፋቸውና የጎጠኝነት ስሜትን የተንተራሱ መሆናቸው ባያጠራጥርም፣ "የፀረ ለውጥ" ኃይሎችን የጥፋት ዕርምጃ በአጭር ለመግታት፤ በቁንጮዎቹ ላይ የተወሰደ ሕጋዊ እንቅስቃሴ አለመኖሩ ያስከተለው እንደሆነም መዘንጋት የለበትም:: ተዋልዶና ተከባብሮ የኖረ ህዝብ፣ በቀላሉ በየቦታው እንዲባላ የሚያደርጉት ኃይሎች፤ በማን አለብኝነት አንድ ቦታ ተከማችተው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ፤ እስከ መቼ በዝምታ እንደሚታለፍ አናውቅም::

የነፃነት እስትንፋስ የናፈቀው ህዝብ፣ አደባባይ በወጣባቸው ቅርብ ጊዜያት ውስጥ፤ ከስሜታዊነት በዘለለ መልኩ ያቀረባቸው የባንዲራና የሽግግር መንግሥት ምሥረታ፣ የአምባገነኖች ለፍርድ የመቅረብ ጉዳይ፤ በቀጣይ ወራቶች በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አያጠራጥርም:: በግፍ ሥርዓት ውስጥ ያለፈው ሕብረተሰብ፣ ለበቀል ሳይሆን የፍትሕን የበላይነት ከማረጋገጥ አንፃር፤ ሀገሪቷን ከመጠን በላይ የበዘበዙና የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ የነበሩ አካላት፣ በክቡር የሰው ሕይወት ላይ አላስፈላጊ ዕርምጃ የወሰዱና የተለያዩ የሰብዓዊ ጥሰቶችን የፈፀሙ ግለሰቦችም ተገቢውን ፍርድ ሊያገኙ እንደሚገባ አጠያያቂ አይደለም::

ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሸቀበ የመጣውን የኑሮ ውድነት በመቆጣጠር ረገድ፤ የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት የወሰደው አንዳችም ተጨባጭ ዕርምጃ የለም:: የዶላር ዋጋን በተወሰነ ደረጃ በማውረድ፣ በውጭ ምንዛሬ የገቡ ዕቃዎችን ውድነት ለመቆጣጠር የተደረገው ጥረት፣ አመርቂ ቢሆንም፤ የህብረተሰቡ መሰረታዊ ፍላጎት በሆኑት፤ ጤፍ፣ ስኳር፣ ዘይትና ዱቄት ላይ አንዳችም መሻሻል አልታየም:: በትራንስፖርት አጠቃቀም (የነዳጅ ዋጋ) ዙሪያ የታየ በጎ ነገርም የለም ማለት ይቻላል::

ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ባሻገር፣ በዚህች ሀገር ዕድገትና የሕዝብ ተጠቃሚነት ላይ የተንጠለጠሉ ችግሮች፤ በምን መልክ መፍትሔ እንደሚበጅላቸው የምንጠይቅበት ትክክለኛ ወቅት አሁን ነው:: በቀጣይ፣ የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ የሥልጣን ዘመን ፈተናዎች የሚሆኑት፤ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዮች፣ የመጀመሪያዎቹ አንድ መቶ ቀናት ማለቅን ተከትሎ፤ ከዳር ዳር መስተጋባታቸው አይቀርምና ሀገር ወዳዱ ጠ/ሚኒስትር ለዚህ መሰሉ ቀጣይ፣ ጠንካራ የሰላማዊ ትግል ጊዜ ከወዲሁ ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ሳንጠቁም አናልፍም::


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ዘኤልያስ ወልደ ሚካኤል

**ዋና አዘጋጅ**
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 314

**አዘጋጆች**
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
መስፍን ጌታቸው
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ታምራት መርጊያ
ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
enqu2013@ gmail.com
Facebook Gihon-meg Fekadu

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤
አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



ታምራት መርጊያ

# ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ያለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ...

የዴሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብና ትርጓሜ እንደየሀገሩ የመንግሥት ሥርዓት፣ ባህል እና ልማድ ሊለያይ የሚችል መሆኑን የፖለቲካ ልሂቃን ይስማማሉ። ይሁን እንጂ፣ የሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል የመታየትን፣ የፖለቲካ ነጻነትን፣ የሕግ የበላይነትንና ሌሎችንም የተመለከቱ መሠረታዊ ባህርያት በየትኛውም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተከታይ ሀገራት ውስጥ ጸንተው የሚኖሩና ሊቀያየሩ የማይችሉ ቋሚ የዴሞክራሲ መለያዎች ናቸው።

ዴሞክራሲ እንደየሀገራቱ ሕዝቦች እሴት፣ አመለካከትና ልማድ ትርጉሙ ሊለያይ የሚችል ከመሆኑ አኳያ፣ የፖለቲካ ዘርፍ ሊቃውንት ከላይ ለመመልከት የሞከርናቸውን መሰረታዊ የዴሞክራሲ ሀሁዎች ዓይነተኛ መለያ ባህርያት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው የዴሞክራሲያዊ ሥርዐት ገዢ መርሆዎች መሆን እንዳለባቸው ያለአንዳች ልዩነት ይስማሙባቸዋል። በመሆኑም የየትኛውም ሀገር ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ከነዚህ መርሆዎች አንጻር ሊለካና ሊመዘን የሚችል ይሆናል።

ዐሥራ ስድስተኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት "አብርሃም ሊንከን" በአንድ ወቅት ዴሞክራሲን አስመልክተው ሲገልጹ፣ "ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማለት፣ ከሕዝብ የሆነና ለህዝብ አገልጋይ የሆነ መንግሥት ማለት ነው" በማለት የተናገሩት አገላለጽ በዓለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ ላይ እንደ ዴሞክራሲ መሪ ቃል ተደርጎ የሚያገለግልና ለዓመታት ሲታወስ የኖረ ነው። በዚህ አገላለጽ መሰረት የየትኛውም ሀገር ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የሚወክለውም ሆነ መላበስ ያለበት ፖለቲካዊ ማንነት የሚመራውን ሕዝብ ፍላጎትና መሻት የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት።

በመሆኑም፣ በአንድ ሀገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዲኖር በማስቻልና ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ እንዲፈጠር በማድረግ ረገድ፣ የዚያች ሀገር ሕዝቦች የማይተካ ሚና የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል።

የየትኛውም ሀገር ዜጋና ማህበረሰብ፣ ዴሞክራሲን የመሻትና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት በሀገሩ እንዲኖር የመታገል ሂደት ተፈጥሮአዊና የሚጠበቅ እውነታ ነው። ምክንያቱ ደግሞ፣ ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር፣ ሰው በመሆኑ ብቻ እንደ ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትህ ያሉ ዴሞክራሲያዊና ተፈጥሮአዊ መብቶቹን መሻቱ፣ እንዲሁም እነዚህን ፍላጎቶቹን የሚገድብበትን የትኛውንም ዓይነት ጫና ላለመቀበል አሻፈረኝ ማለቱ አብሮት የተወለደ፣ ከሰብአዊ ተፈጥሮው የሚመነጭ እውነታ ነው።

በአንጻሩ ደግሞ በአንድ ሀገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ሳይፈጠር፣ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ለመገንባት መሞከር፣ "በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ አዲስ ወይን" እንደመጨመር ተደርጎ ይወሰዳል።

ስለሆነም በአንድ ሀገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መገንባት፣ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ከመፍጠር በፊት መቅደም ያለበት ግንባር ቀደም ተግባር መሆን ይኖርበታል።

በዘመናዊውና በሰለጠነው ዓለም ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ባለባቸው ሀገራት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች፣ በጎ የሆኑ ማህበረሰባዊ እሴቶቻቸውን የመጠበቅና ለነዚህ እሴቶች በወል የመገዛት፣ እርስ በርሳቸው መተባበርና በልዩነት ውስጥ የመቻቻልን ባህል ማስፈን፣ እንዲሁም እርስ በርስ መከባበርን፣ እንደገዢ መርህ ወስደው ለዚህ ተግባራዊነት ቁርጠኛና ሁሌም ዝግጁ ሆነው ሞራላዊና ማህበረሰባዊ የሐላፊነትን ግዴታቸውን በጋራ ይወጣሉ።

ከዚህ ሐሳብ በተቃራኒ፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ባልዳበረባቸው ሀገራት ውስጥ የምንኖር ዜጎች ደግሞ፣ ዴሞክራሲን አጥብቆ የመሻት ጽኑ ፍላጎት እንጂ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመገዛትና የዴሞክራሲን እሴቶች በአግባቡ ተረድቶ፣ ከዴሞክራቲክ ማህበረሰብ የሚጠበቅን ማህበራዊና ሞራላዊ ግዴታ የመወጣት ሐላፊነትን መላበስ ያልተለመደ ነው። በዚህም ምክንያት ብልጭ ያሉ አፍላ የዴሞክራሲ ዕድሎችንን በእንጭጩ በመቅጨት እንደማህበረሰብ ራስን በራስ የማጥፋት ተግባራት በስፋት ሲፈጸሙ ይስተዋላል። በቅርቡ እንዳየነው፣ በሀገራችን ብልጭ ያለውን ሀገራዊ የዴሞክራሲ ተስፋ ለማጨለም የሚደረገው ከንቱ ልፊያና የጋራ የመጠፋፋት ሙከራ ለዚህ እንደማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

በዚህ ረገድ ሕንዳዊው የዴሞክራሲና የነጻነት አባት፣ ማህተመ ጋንዲ እንደገለጸው፣ "የአንድ ሀገር ሕዝቦች የእርስ በርስ አለመቻቻል በራሱ፣ የዴሞክራሲን መንፈስ የሚያጠፋ፣ ከባድ የዴሞክራሲ ማነቆና መሰናክል ነው።"

አሁን በሀገራችን እየሆነ ያለው ነገርም ከዚህ እውነታ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። በየክልሉ ፍጹም ኢትዮጵያዊ ባልሆነ ባህርይ፣ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ወገን በብሔር መነጽር እየተመለከቱ፣ ከቀዬ ከማሳደድ አንሥቶ፣ ሕይወት የማጥፋትና አካል የማጉደል ድርጊቶች ተደጋግመው ሲፈጸሙ እየተመለከትን ነው።

በሀገራችን፣ "ልሂቃን ነን" የሚለው ተዋረዳዊ የማህበረሰብ ፈርጅ ምክንያታዊ ሆኖ፣ ሐሳቡን በመርህና በተጨባጭ ማስረጃ ታግዞ ተንትኖ በማቅረብ፣ ማህበረሰቡን በማሳወቅና በማንቃት፣ ህብረተሰቡ ኢትዮጵያዊ እሴቶቹን አስጠብቆ፣ እርስ በርሱ የሚከባበርና የሚቻቻል፣ በሥነ ምግባርም የታነፀ እንዲሆን፣ ከልሂቃን በሚጠበቅ ማህበረሰባዊና ሞራላዊ ሰብእና የበኩሉን አዎንታዊ አስተዋፅኦ ከማበርከት ይልቅ፣ አሉታዊ በሆኑ ብሔርን ከብሔር በሚያጋጩ ተግባራት ላይ ሲባክን ይስተዋላል።

እንደኛ ያልዳበረ የዴሞክራሲ ባህል በተንሰራፋበት ሀገር ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብ ደግሞ፣ ከነዚህ ወገኖች የሚቀርብለትን ሐሳብ በአግባቡ መዝኖና በምክንያታዊነት መርምሮ በመመልከት የሚስማማውን ሐሳብ ከመሸመት ይልቅ፣ "የእኔን ቡድን ወይም ብሔር፣ እምነት ወይም አመለካከት የሚወክል ነው" ብሎ ባመነው ልሂቅ የሚሰነዘርለትን ሐሳብ እንደወረደ በመቀበል በተበጀለት ቀዳዳ እንደጅረት ይፈስሳል።

በዚህም ምክንያት ነው፣ ባለቅኔው ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን፣ በአንድ ወቅት እንደገለጸው፣ ማህበረሰባችን በወረረው ባዕድ ሞት ማግስት፣ አዲስ ተስፋን ለተራበው ህልውናው፣ አዲስ የሀገር ውስጥ ሞት፣ ለአዲስ ትንሣኤ በቃተተው ዓይኑ፣ አዲስ መቃብር እየከፈተ የሚገኘው።

ዴሞክራሲ ግን ከቶውንም በዚህ መልክ ሊገነባና ሊዳብር እንደማይችል የተረጋገጠ ነው። ፍትሕን፣ እኩልነትንና ነጻነትንም እንዲህ ባለ ሁኔታ ለመቀዳጀት መሞከርም በሰባራ ፎሌ ውሃ እንደመቅዳት ዘበትና ከንቱ ልፋት ብቻ ነው። ይልቁንም በዚህ አካሄድ የፍቅርን ወዙን ሳይሆን፣ ስሙን፣ የነጻነትን ግብሩን ሳይሆን፣ ተረቱን ብቻ ነው መቀዳጀት የሚቻለው። የቋመጥንለትን ዴሞክራሲያዊ ነጻነት ከማግኘት ይልቅ ከአቀበት ወደ ቁልቁለት ተንደርድረን፣ ዝቅ ወዳለበት በጋራ እንፈሳለን።

በመሆኑም የጋራ ጎጇችንን በጽኑ ዴሞክራሲያዊ መሰረት ላይ ጸንታ እንድትቆም ለማስቻል፣ ከጠቅላላው ማሕበረሰብም ይሁን "በቅቻለሁ፣ ነቅቻለሁ" ከሚለው የልሂቃን ማሕበረሰባዊ ፈርጅ፣ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ የመፍጠር ታላቅ ሀገራዊ ሐላፊነት ይጠበቃል።

ለዚህም ተፈጻሚነት፣ ማህበረሰቡ እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ፣ የኔ ሐሳብና አመለካከት ብቻ ነው ትክክል፣ ከሚል ነባር ኢ-ዴሞክራሲያዊ ልማድ ራሱን አላቅቆ፣ ልዩነትን እንደ ጸጋና ውበት ተቀብሎ፣ መቻቻልና ትብብርን የማዳበር፣ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ባህልን ወደ ውስጡ አስርጾ፣ የቀረበለትን ሐሳብ መርምሮና መዝኖ፣ በሐሳብ የበላይነት በማመንና በአብላጫ ድምፅ በመገዛት ራሱን ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ አድርጎ የማብቃት ሀገራዊ ሐላፊነት ይጠበቅበታል።

ልሂቃኑም ክፍል በበኩሉ፣ ልዩነትን፣ ጥላቻንና መከፋፈልን ከሚሰብኩ ትርክቶች ራሱን በማራቅ፣ በልዩነት ውስጥ ስለሚኖር አንድነት፣ ስለመደመር፣ ስለምክንያታዊነት፣ ስለ ዴሞክራሲ እሴቶች፣ ስለጋራ እድገትና ብልጽግና በሚያትቱ ትርክቶች ዙሪያ ትኩረቱን በማድረግ፣ ሕብረተሰቡን የማንቃት፣ የማብቃትና የማሳወቅ ሞራላዊና ሀገራዊ ግዴታውን በመወጣት፣ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ እንዲፈጠር የበኩሉን እገዛ ማበርከት ይጠበቅበታል።

ይህ ካልሆነ ግን በሀገራችን ዴሞክራሲን ለማስፈን እስካሁን የተከፈለው መሥዋእትነት የባከነና ከንቱ ይሆናል። አሁን ላይ የታየው አበረታች ተስፋም በንኖ እንደሚጠፋ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል። ይህም በራሱ ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ሕይወታቸውንና አካላቸውን ያለስስት የገበሩ ሰማዕታትን መሥዋዕትነት እንደመካድ የሚቆጠር ነው። ስለዚህም፣ ራሳችንን የታሪክ ተወቃሾች ከሚያደርጉ ተግባራት አቅበን፣ የፍቅርን፣ የአንድነትንና የይቅርታን መንገድ በጋራ ለመጓዝ እንትጋ።

*ክብርና ሞገስ ሕይወታቸውን ገብረው ዛሬ ላየነው ተስፋ ላበቁን ሰማዕታት!*



ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# ኢትዮጵያና የብሔር ፖለቲካ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የአራት ክልል ፖለቲካ ፓርቲዎች በመሠረቱት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) መመራት ከጀመረች እነሆ ሃያ ሰባተኛ ዓመቷን አስቆጥራለች:: ፓርቲው የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለም ከግንባሩ መጠሪያ በቀላሉ መረዳት ይቻላል:: ይኼውም አንድም አብዮታዊ ሲሆን፣ አንድም ዴሞክራሲያዊ የሚለው ነው:: አሁን ባለው ሁኔታ ግንባሩን የመሰረቱ አራቱ ፓርቲዎች በተናጠል ያሉ ቢመስሉም፤ በግንባርነት ስለመኖሩ የሚጠራጠሩ ሰዎች በርካታ ናቸው:: ግንባሩ በዚህ ርዕዮተ ዓለም እመራለሁ ብሎ ሀገር ማስተዳደር ከጀመረበት ወቅት ጀምሮ ከራሱ ከፓርቲው ግለሰብ አባላት፣ ከሀገራችን ምሁራን፣ እንዲሁም ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ቀላል የማይባል ተቃውሞ ገጥሞታል:: የተቃውሞው መነሻ የተለያየ የነበረ ቢሆንም፣ ዋነኛውና የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ያነሱት የነበረው ጥርጣሬ፣ ግንባሩ የርዕዮተ ዓለሜ ምሰሶዎች ናቸው ብሎ መጠሪያው ላይ ጭምር ያሠፈራቸው አብዮታዊነትና ዴሞክራሲያዊነት ጥምረት በተመለከተ ነበር:: እነዚህ አካላት አብዮታዊነትና ዴሞክራሲያዊነት በተናጠል እንጂ በጋራ ሊሆኑ የማይችሉ ፍፁም በተቃራኒ የቆሙ ርዕዮቶች ናቸው ብለው ተከራክረዋል:: አብዮት ብሎ ዴሞክራሲያዊነት ሊኖር አይችልም ብለው በዓለም ላይ የተደረጉ አብዮቶችን ከፈረንሣይ አብዮት ጀምረው እንደ ምሳሌ እያጣቀሱ ሞግተዋል::

ሌላው ዛሬም ድረስ በኢህአዴግ በተለየ ሁኔታ ተቃውሞ እየገጠመው ያለ ብሔር ተኮር (ዘውጌኛነቱ) ላይ ያለው እይታና ብሔርንና ቋንቋን ከፖለቲካው ጋር በማገናኘት የፈጠራቸው ፓርቲዎች፤ ዛሬ እነዚህ በዘውጌኛ ቅኝት የተደራጁ ፓርቲዎች አብረው የመቀጠል እድላቸው አጠራጣሪ ከመሆኑም በላይ፤ ኢህአዴግ እንደ ኢህአዴግ መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆሞ መሄጃውን መንገድ ያጣ መስሎ የቆመ ይመስላል:: የኢህአዴግ የዘውጌ አደረጃጀቱ መነሻው፣ አማርኛ የተናገረ ምድርን አማራ፤ ኦሮምኛ የሚናገር መሬትን ኦሮምያ፤ ትግርኛ የሚናገርን ትግራይ …ወዘተ በማለት ማካለሉ ነው:: የኢትዮጵያና የህዝቦቿ ክልሎች ሊካለሉ ይገባቸው የነበረው በመልክአ ምድር ወይም ለአስተዳደር አመቺነት በሚል እንጂ፤ እየቆየ እሳትና ጭድ የሚሆነው የብሔር (የዘውግ) አወቃቀር መከተሉ፤ እነሆ 27 ዓመት የብሔር ቅራኔዎችን እያስተናገድን እዚህ ደረጃ እንድንደርስ አስችሎናል:: ዛሬም በከፋ መልኩ በብሔር ቅራኔ ውስጥ እንዳክራለን:: “ከዘረኝነት ይልቅ ሰውነት ይቅደም = Humanity Before Ethnicity” የሚለውን መሪ ቃል ሳንከተል በመቅረታችን፣ አሁን የደረስንበት ምስቅልቅል ሕይወት ውስጥ ልንገኝ በቅተናል:: ማንዴላ፣ “ሰው በቆዳው ቀለም፣ ወይም ደግሞ በማንነቱ፣ ወይም በሃይማኖቱ ምክንያት ብቻ ማንም ማንንም ሊጠላ አልተወለደም:: ሰዎች መጥላትን መማር አለባቸው” ብለው ነበር:: በ27 ዓመት ውስጥ ከአንድነት ይልቅ ልዩነት ላይ አተኩረን በመሥራታችን ህዝቡን ያስተማርነው ጥላቻንና ልዩነትን እንጂ ፍቅርና አንድነትን አልነበረም:: በዚህም 27 ዓመት የዘራነው ሌላውን የመጥላት ዘር ፍሬ አፍርቶ ልናየው በቃን:: የዘሩ ፍሬ የሚፈልጉትና የሥልጣን እድሜአቸውን እንዲያቆይላቸው ለሚመኙ ሌላውን የመጥላት ፍሬ ለመልቀም ጎንበስ ቀና እያሉ ናቸው::

አሁን ያለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አስተዳደር አባላት የሆኑት ክልሎች፣ ለቁጥራቸውና ለማንነታቸው ምክንያት የሆነው ቋንቋ አከፋፈል መነሻ ምክንያት ብሔረሰቡን ወይም ማኅበረሰቡን በሚኖርበት ሥፍራ የሚገድብና የሚያጥር እንዲሆን አድርጎታል:: ክልል ማለት ለተከለለለት ብሔረሰብ ብቻ የተከለለ፣ ለሌላው የተከለከለ የይዞታ ቦታ ሆኖ እንዲታይ ሆኗል:: ሕገ መንግሥቱ ቋንቋ በሚል የተፈጠረው የብሔር አከላለልና በተያዘው የተሳሳተ የፌደራል ሥርዓት ግንዛቤን ጨምሮ ዛሬ በአንዳንድ የሀገራችን ክልሎች ኢትዮጵያዊነትን የሚያምስ፣ ኢትዮጵያን የሚያተራምስ፣ ብሔራዊ ድርጅቶችን ደግሞ በሚገዙት የርስት ምድራቸው ውስጥ አድራጊ ፈጣሪ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: በክልሎቹ አመራሮች አምባገነንነት፣ ሙስናና መልካም አስተዳደር እንዲንሰራፋ ዋነኛ ምክንያት ሆኗል:: ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ዋነኛ ፈተና የሆነው ደግሞ፣ እነዚህ አክራሪ ብሔርተኞች በየክልሎቻቸው የሚያደርጉት ፀረ ህዝብ ድርጊት፤ ህዝቡ በሰላም ሥራውን እንዳይሠራና በሰላም እንዳይኖር እንቅፋት ሲሆኑ በስፋት እየተስተዋለ ነው::

በአሁኑ ሰአት አንዳንድ ሙሰኞች በሥልጣን ላይ የሚገኘውን ኃይል በብሔርተኝነት ተጠግቶ ጥቅም እንደሚገኝ በማስላት ጥቅም ለመጋራት ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ:: በዚህም ምክንያት የነገዱ ሳይሆን በመንግሥት ሥልጣን የከበሩ ሌቦችን በየአካባቢው የተንደላቀቀ ኑሮ ሲመሩ የሕግ ያለህ ቢልም፣ ምንም እርምጃ እንደማይኖር በማወቁ ቀላል የማይባል የኅብረተሰብ ክፍል ብቸኛ የመክበሪያ መንገድ ወይ የመንግሥት ሥልጣን መያዝ ወይ ከመንግሥት ባለሥልጣን መጠጋት ወደሚል እሳቤ እንዲገባ የመንግሥት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር:: ይህ ደግሞ ከፍተኛ የእሳቤ ንቅዘት ነው:: እንዲህ የሚያደርጉት ጥቂት ከየብሔሩ የሚገኙበት ጥገኛ ኃይሎች እንጂ የአንድን ብሔር አጠቃላይ ንቅዘት አይወክልም:: በሥልጣን ላይ የነበሩት አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግራይ …ወዘተ በግለሰብ ደረጃ ሙስናውን ፈፅመው ሀብት አጋብሰዋል እንጂ፤ እንደ ብሔር አማራ፣ ኦሮሞና ትግራይ …ወዘተ በከፋ ድህነት ወይም በሴፍቲ ኔት እርዳታ የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው::

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ ሀብት ክፍፍል ከብሔር ብሔረሰብ አኳያ የሚያሠሉና የአማራ፣ የጉራጌ፣ የትግሬ፣ ኦሮሞ፣ የሐረሪ፣ ወዘተ ምን ያህል ሀብታም አለ? ምን ያህል ካፒታልስ ደርሶታል? እያሉ ከሕዝብ ብዛት ጋር የሚያነፃፅሩ ዜጎች በብዛት ተፈጥረዋል:: የዚህ ዓይነት ሥሌት ኅብረተሰቡን ለማቃቃር የሚውልና መበላለጥን እየፈለጉ ከማቅረብ በስተቀር፤ የሚሰጠው ጥቅም እንደሌለ ቢረዱም በሰላማዊ ህዝብ መካከል ቅሬታ እንዲፈጠርና ህዝቡ በፈለገው ቦታ ሠርቶ እንዳይኖር ለማድረግ ነው:: ቀመር ሠርቶ የዚህ ወገን ድርሻ በዝቷልና ከዚህ ወደዚህ ይቀነስ ወይም የዚህኛው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ቆሞ እየተንቀራፈፈ ስለሆነ የዚህኛው ይስፋ ሊባል አይችልም:: በሀገራትና በክልሎች መካከል ያልተመጣጠነ ዕድገት አጠቃላይ የሰው ልጅ ታሪክ ባህርይ ነው:: ማድረግ የሚቻለው አድሏዊነት መወገዱንና አቀራራቢ የልማት ፖሊሲ መኖሩን በተግባር ማረጋገጥና በዚያ ውስጥ መጣር ነው:: አድሏዊነት የሌለው ፖሊሲ ተይዞ ጥረት ቢደረግም ▶

እንኳን ከአድልዎ ውጪ በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች የክልልና የሀገራት የኢኮኖሚ መበላለጥ መከሰቱ የማይቀር ጉዳይ ነው::

በቀጣይ ኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ ዴሞክራሲ እንዲዘረጋና ፍትሐዊ ምርጫም ዕውን እንዲሆን ከተፈለገ ፓርቲዎች እንዲኖሩ፣ ኖረውም በሕግና በተግባር እኩል እንዲሆኑ፣ በምርጫም እኩል ወጪና ወራጅ መሆን እንዲችሉ ከተፈለገ ፅንፍ የወጣው የአክራሪ ብሔርተኝነት አመለካከት በሀገራችን ከሥሩ ተመንግሎ ሊወገድና ሊጠፋ ይገባል:: አክራሪ ብሔርተኝነት የሚወልዳቸው ትምክህትና ጠባብነትን ነው:: በመንግሥታዊ ዓምዶች ከፓርቲ ወገናዊነት፣ ተቀጥላነትና ይዞታነት ውጪ ነፃ ሆነው መደራጀት ቢችሉም አክራሪ ብሔርተኝነት ካለ ዴሞክራሲን እግር ከወርች ሊቀፈድደው እንደሚችል እሙን ነው::

የብሔርተኝነት ድጥና የትምክህት ችግር ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ በከፋ ደረጃ እየተከሰተ ነው:: ጠባቦች፤ ክልልተኞች፣ ወገንተኞችና ትምክህተኞች በሚፈጥሯቸው ቅራኔዎችና ፍርኃቶች ውስጥ ህዝብ በሰላም መኖር አልቻለም:: ከጊዜ ወደ ጊዜ ህዝብ ከእነዚህ ችግሮች ጋር መኖርን ጠልቶ በክልሎች መካከል በርካታ የሀገር ውስጥ ስደትን እየተመለከትን ነው:: መንግሥትም ከቦታ ቦታ እየሮጠ በዚህ ዙሪያ የተፈጠረውን ሁከት ለማብረድና ለማስታረቅ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፤ ችግሮችን ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሔ መስጠት አልተቻለም:: ሀገራችን በዚህ ረገድ አዲስ ራዕይ፣ አዲስ ቅኝትና አዲስ መፍትሔ ያስፈልጋታል:: አዲሱ መፍትሔ ደግሞ ከሕገ መንግሥቱ ማዕቀፍ ውስጥ በመውጣት፣ የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አጠቃላይ የዴሞክራሲ ጥያቄ አካል እንጂ በተገላቢጦሽ የብሔርን ጥያቄ የሁሉ ነገር መፍቻ አድርጎ ማየት ተገቢ አይደለም:: ስለዚህ ከብሔርተኝነት በላይ በሀገራዊ አንድነት ዙርያ መለስ ጥናትና ምርምር በምሁራን ዘንድ ተካሂዶ ዘላቂ ሀገራዊ መፍትሔ ሊቀርብ ይገባል::

ኦሮሞነት፣ ትግሬነት፣ ሐድያነት፣ …ወዘተ በአብሮ መኖር ትስስር የሚገኙና ሰዎች ላይ የሚቀረፁ ማኅበራዊ ማኅተሞች ናቸው:: በደም መወራረስን በጋራ ባህል የመቀረፅ አጥር አይገድበውም:: ብሔረሰባዊና አካባቢያዊ ማንነት እንደዚሁ በደም አይወሰንም፣ በደም አይተላለፍም:: ከየትኛውም ማኅበረሰብ ይበልጥ ክፍት የሆነው ኦሮሞ፤ በጉዲፈቻና በሞጋሳ ኦሮሞነትን ሊያቀዳጅ የቻለው ለዚህ ነው:: አንድ ኤርትራዊ የኦሮሞ ባህልና ቋንቋ ውስጥ ቢያድግ ኦሮሞ ነው የሚሆነው:: የኦሮሞን ሥነ ልቦና፣ ባህልና አመለካከት ሊይዝ ግድ ይላል:: አንድን ኦሮሞ ደግሞ ኤርትራ ወስደው ቢያሳድጉት ኤርትራዊ ሆኖ ነው የሚወጣው:: እዚያ ከተዋለዱት ኤርትራውያን እኩል ኤርትራዊ የሚያሰኘው ባህልና ሥነ ልቦና ይጎናፀፋል:: በኦሮሞ ያደገው ኤርትራዊ ደግሞ በኦሮሞ ማኅበራዊ ማህፀን ውስጥ ሦስት ጉልቻ መሥርቶ መኖር ቢቀጥል፤ በዙሪያው የሚያገኘው የቅርብ ዕድል፣ ከነባሮቹ ጋር መጋባትና መዋለድ ነው:: በአንድ ሰው ያየነው ምሳሌ ብዙ ውጥንቅጥ፤ ግለሰቦች አንድ አምሳያ ማኅበረሰብ ውስጥ ቢቀላቀሉም ያው አንድ አይነት ነው::

ሙስናና አክራሪ ብሔርተኝነት የሚዛመዱ ወዳጆች ናቸው:: አንደኛው ከተከሰተ ሌላኛው መኖሩ ግድ ነው:: በሀገራችን የኮንትሮባንድና የጥቁር ገበያ ንግድ በስፋት የመንግሥትን መዋቅር በመጠቀም ጭምር ይከናወናሉ:: ሀገሪቷ እየፈጠረች በመጣችው ሀብት ምክንያት በራስ አቅም የተወጠኑ ሰፋፊ ፕሮጀክቶች የታለመላቸው ግብ ሩቡን እንኳ ሳይመቱ፣ አንድ ፕሮጀክት የተመደበለት የሀገሪቱና የሕዝቡ ሀብት እንደጉም ተኖ ሲጠፋ፤ ሓላፊነቱን ወስዶ የሚጠየቅ አለመኖሩና መቀጣጫ አለመሆኑ፣ ብዙ ፕሮጀክቶች ተመሳሳይ ጎዳና እንዲከተሉ አድርጓል:: በዚህ ወቅት ያልተጓተቱ የመንግሥት ፋብሪካዎች፣ መንገዶችና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች በጀታቸው ባክኖ እንኳን የሚጠይቅ አካል የለም:: ምክንያቱም ለሙስና ሲባል የተዘረጋው ኔትዎርክ ብሔርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ፤ አንዱ አንዱን አጋልጦ ለመስጠት አይፈልግም::

ብሔርን መሰረት ያደረገው የሙስና እንቅስቃሴ መንግሥት (ሙስናን የሚከላከለው ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ) በቀላሉ ለመከላከል አዳጋች ሆኖበታል:: አንድ የሕዝብ ፕሮጀክትን የሚመራ ዜጋ በራሱም ሆነ በሌላ ምክንያት የተሰጠውን ሕዝባዊ አደራ መወጣት ካልቻለ፣ ሌላው ቢቀር በራሱ ሓላፊነቱን የማስረከብ ባህል ሊኖር ይገባ ነበር:: ይህ እንዳይኖር ግን መንግሥት ከሚከተለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ መስመር ይልቅ፣ የሌቦች ፍላጎት የፖለቲካ ኢኮኖሚ የበላይነት በማሳየቱ፤ ህዝብ ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማትና ዴሞክራሲ በእንጭጩ እንዲቀር አድርጓል:: በብሔር ብሔረሰቦች መካከል ጥላቻ እንዲፈጠር ሌት ተቀን የሚለፉት አክራሪ ብሔርተኞች እንዲህ በማድረጋቸው ብቻቸውን የሚጠቀሙት ጥቅም ስላለ ነው:: አጠቃላዩን ህዝብ ለማይጠቅም አክራሪ ብሔርተኞች ብቻቸውን ሊጠቀሙበት የሚፈልጉትን አካሄድ በግልጽ ልንቃወም ይገባል:: የአክራሪ ብሔርተኛው ግለሰባዊ ጥቅም ሲነካ፣ ብሔራችን ተነካ ብለው ሊያነሳሱንና ከሌላው ብሔር ብሔረሰብ ጋር እንድንጋጭ ሲጠሩን ተባባሪያቸው ልንሆን ሳይሆን፤ ድርጊታቸውን በመቃወም ባለንበት ቦታ ሁሉ ልንታገላቸው ይገባል::

በጋንዲ መርሆ፣ "ኃጢአተኛውን ሳይሆን ኃጢአቱን እንጥላ" በጥላቻ የተመረዙትን አክራሪ ብሔርተኞች ብሔራቸውን የምንጠላ ከሆነ የእነርሱ የመስታወት ነጸብራቅ እንሆናለን፤ መጥላት ያለብን መጥፎ ድርጊታቸውን እንጂ በግለሰብ ደረጃ መጥፎ ድርጊት የሠራውን ብሔር ሊሆን አይገባም:: እንደ ሰው ሰብዕና በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች፤ አክራሪ ብሔርተኞች በክልሎች መካከል አጥር በማበጀት ለረዥም ዘመናት አብሮ የኖረውን ህዝብ በመግደልና በማፈናቀል የሚያደርጉትን እኩይ ድርጊት ልንጠላ እንችላለን:: እኛ የምንጠላው ብሔርን መሰረት በማድረግ የሚፈፅሙትን እኩይ ምግባራቸውን እንጂ እንደ ሰው ጉዳዩን በተሳሳተ መንገድ እየፈፀሙ ያሉትን የግለሰቦቹን የብሔር አባልነትን መሆን የለበትም::

**በአሁኑ ሰአት አንዳንድ ሙሰኞች በሥልጣን ላይ የሚገኘውን ኃይል በብሔርተኛነት ተጠግቶ ጥቅም እንደሚገኝ በማስላት ጥቅም ለመጋራት ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ**

በሩዋንዳ የተከሰተው ጥላቻ የሚሊዮኖች ሩዋንዳውያንን ሕይወት ቀጥፏል:: ጥላቻ ጠንካራ ኃይል ነው:: በናዚዎች የተሰራጨው ጥላቻ ሀገሮችን በጠቅላላ እንዲጠፉ አድርጓል:: በዳርፉር የተቀሰቀሰው ጥላቻ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሱዳን ዜጎችን ሕይወት አጥፍቷል:: በምንም ዓይነት መንገድ ብሔርን ከግለሰብ ሳንለይ ወደ ጥላቻ መግባት የለብንም::

በጠ/ሚር ዐቢይ አመራር ሥር ላለችውና "ፍቅር ያሸንፋል" በማለት በአዲስ የይቅር ባይነት መንፈስ አዲሲቷን ፍቅር የነገሰባትን ኢትዮጵያን ለመገንባት ተነሥተናል:: በፍቅርና በይቅር ባይነት "ተደምረናል" ካልን፤ መልሰን የመቀነስ ሥራ መሥራት የለብንም:: በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ተደምረናል ባሉ በሳምንቱ፣ በተሳሳተ መንገድ የመቀነስ ድርጊት ሲፈፅሙ ይታያሉ:: የመደመር መርህ ማለት ማንም ወንድ ወይም ሴት ባለው ሥልጣን በመመካት ባልታጠቁ ዜጎችና በሰላማዊ ሰዎች ላይ የጦር እልቂት ሊያዝዝ የማይችልበትን፤ ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብም ሊወገድ የሚችልበትን ነጻ ህሊና መፍጠርና ሁላችን በእኩል የምንኖርባትን፣ አሳዳጅና ተሳዳጅ የሌለባትን፣ ፍቅር የነገሠባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ መገንባት ማለት ነው::

በእያንዳንዱ ግለሰብ የጎሳ፣ የእምነት ወይም የቋንቋ ልዩነት ሳንፈጥር፤ በአንድነት በመሆን የእያንዳንዱ ዜጋ መብትና ክብር የሚጠበቅበትን ህብረተሰብ ለመፍጠር በጋራ መነሣት ይኖርብናል:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው የወደፊቱን ብሩህ ዘመን ለመፍጠር የምንችለው::

እስካሁን የተጓዝንበትን የኢትዮጵያዊነት መንገድ ወደ ኋላ መለስ ብለን ልንፈትሽ ይገባል:: ኢትዮጵያ ኩራታችን ናት:: የበለጠ እንድኮራባት ግን የአስተሳሰብ ለውጥ በሁላችንም እንዲሁም እንደ ሀገር የሥርዓት ለውጥ ያስፈልጋል። ዛሬ በEthnic empowerment የሀገራችን ፖለቲካ ችግር አይፈታም:: Civic political transition ያስፈልገናል። የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄን መመለስ የሚቻለው የተግባባ ማህበረሰብ (ብሔር ብሔረሰብ) ሲኖር፤ ብሔራዊ መግባባትና ብሔራዊ እርቅ በህዝቡ መካከል ሲፈጠር በመሆኑ፤ ሁላችንም ለኢትዮጵያ ሀገራችን ሰላምና እድገት ሲባል አንገታችንን ቀና አድርገን ስለ አንድነት፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ መግባባት ሲባል እንደ አንድ የእናት ልጆች በጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበን ስለ ዛሬው ትውልድ ብቻ ሳይሆን፤ ስለ ቀጣዩ ትውልድ መልካም እጣ ፈንታ በቀናነት፣ በእውቀትና በብስለት እንነጋር።

***ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!***

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትናንትና እና ዛሬ



ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

*ጠቅላይ ሚኒስትራችን የሀገራችንን ፖለቲካ እንደአዲስ ቀደው ከመስፋታቸው በተጨማሪ አንዳንድ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለውጦችን በማድረግ ላይ ናቸው። መንግሥት ስላቀዳቸው የፖሊሲ ለውጦችና ምክንያቶቹ ለማስገንዘብ፤ ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ ስለሀገራችን ኢኮኖሚ፣ ወቅታዊ ተግዳሮቶችና ስለታቀዱ መፍትሔዎች የተለያዩ ንግግሮችን አድርገዋል። አንዳንድ ተቃዋሚዎች ቢኖሩም እነዚህ የፖሊሲ ለውጦች በብዙ የዘርፉ ምሁራን ተቀባይነትን አትርፈዋል።*

*ይህ ጽሑፍም በሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አንዳንድ ነገሮችን በመጨመር፤ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከትናንት እስከዛሬ ከዳሰሰ በኋላ፤ ላለፉት 27 ዓመታት በልማታዊው አጠቃላይ ኢኮኖሚ፣ የግብርና መር ፖሊሲና በዘርፉ የነበረውን አፈፃፀም ይመለከታል።*

ትናንትም ይሁን ዛሬ በግብርና፤ በሰብል ልማትና እንስሳት እርባታ ላይ የተመሰረተው የሀገራችን ኢኮኖሚ ዛሬም ድረስ የመሰረታዊ ለውጥ ባለቤት አይደለም:: ትላንት በፊውዳሏ ኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ የተመረተው የብዙኃኑ አርሶ አደርና አርብቶ አደር ምርት የየአካባቢው መኳንንትና መሳፍንት፣ ከዚያም የማዕከላዊው መንግሥት ሲሳይ ነበር:: ገባሩ ያመረተው ትርፍ ምርት የበላተኞች ብቻ ስለነበር ቀጣይነት የነበረው ዕድገት ማስመዝገብ ሳይቻል ቀርቷል:: የደከመበትን ምርትና ዋጋውን አግኝቶ ካልተጠቀመበት፣ መልሶ ሥራውን ካላጎለበተበት፤ የሰው ልጅ በድካሙ ለውጥን ማሸተት ካልቻለ ምርታማነትና ዘላቂ እድገት አይታሰቡም::

ሀገራችን ዘመናዊ ጉዞዋን ከጀመረች በኂላም ቢሆን በወታደራዊው መንግሥት መሬት ላራሹ ታውጆ ብዙኃኑ የመሬት ባለቤት ቢሆንም፤ የእያንዳንዱ አምራች ምርትና ዋጋው የአምራቾች ማህበራት፣ የመንግሥት የገበያ ፖሊሲ ሰለባወች ነበሩ:: ስለዚህ ተመሳሳይ ነበር ማለት ይቻላል:: ላለፉት 27 ዓመታት ድህነት ለተንሰራፋበት ኢኮኖሚ ይበጃል ብሎ መንግሥት አዛዥና ናዛዥ የሚሆንበትን የኢኮኖሚ መስመር የተከተለው አብዮታዊውና ልማታዊ መንግሥታችንም ቢሆን፣ ፖሊሲውን የተጠቀመበት የቆየውን የፊውዳሎችንና የጭሰኞችን ግንኙነትና ባህርይ በሚያስቀጥል መልኩ ነበር ማለት ይቻላል::

የመጀመሪያውን የፊውዳሉንና የመጨረሻውን የልማታዊ መንግሥት ኢኮኖሚ ለማወዳደር ግብርን እና ትርፍን ማስተዋል ተገቢ ነው:: በፊውዳል ኢኮኖሚ በጥቂት ፊውዳሎችና በብዙኃኑ አምራች መካከል የነበረው ግንኙነት የገባሮችና የአስገባሪዎች ብቻ ነበር:: አስገባሪዎች ጌቶች ወይም የጌታ ልጆች፣ ባለርስት ነን ስላሉ ብቻ፣ ከአምራቹ ግብር ይጠይቁ ነበር፤ አምራቹም ይህን ተቀብሎ እንደግዴታ ሲፈፅመው ዘመናት አልፈዋል:: ግብር ግዴታ ብቻ ነበር፤ በውስጡ አማራጭ፣ ስምምነት አልነበረውም፤ አስገባሪዎች በአንድ ሀገር ውስጥ የተወሰነ ሚና እንደነበራቸው ግልፅ ቢሆንም፤ የሚበልጠው ግን ሽክምነታቸው ነበር::

ዓለም ላይ ከኂላ ቀሩ ፊውዳሊዝም ከድክመቶቻቸው ጋር የተሻሉ ወደሆኑት ዘመናዊው ስርዓቶች ካፒታሊዝም፣ ሶሻሊዝምና የሁለቱ ቅልቅል ወደሆነው ልማታዊ ኢኮኖሚ የተደረገው ሽግግር በተለያዩ ዘዴዎች ከላይ የተገለፀውን የገባሮችንና የአስገባሪዎችን የግንኙነት ባህርይ በመቀየር ነው:: ይህ ሽግግርም የሚፈልጉትን ግብር ወደ ዜጎች የጋራ አስተዳደራዊና ልማታዊ ወጭ መቀየርና መመጠን፣ ለዜጎች በፍትሐዊነት በማከፋፈል፣ ገቢውን ለታለመለት አላማ በተገቢው ሥርዓት በመጠቀም ነበር:: ወደ ታክስ ማለት ነው::

ሌሎች ለውጦች ደግሞ በፊውዳሉ ስርዓት አቆጥቁጠው የነበሩ ተጨማሪ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ማዘመንና ማስፋፋት ናቸው:: ይኸውም በግብርናው ዘርፍ የተለያዩ ምርቶችን ወደ ገበያ የሚያደርሱ፣ ለአምራቹ አርሶ አደርና አርብቶ አደር ግብዓትና መሰረታዊ ሸቀጦችን የሚያቀርቡ፣ መሰረተ ልማቶችን የሚያቀርቡ ሥራዎችን በማዘመንና በማጎልበት ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ ነው::

> **ከግብርናው ዘርፍ ጋር ለሚቀራረብ የሥራ አደጋ ተጋላጭ የሆነውን፣ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ፣ የቴክኖሎጂና የአስተዳደር ዕውቀት የሚጠይቀውን የማምረቻ ኢንዱስትሪውን ዕድገት መጠበቅ ሞኝነት ነው**

ሁለተኛው የማምረቻ ኢንዱስትሪን፣ ዘርፍ ማዘመንና ማስፋፋት ነው:: ይህንን ዘርፍ እድገቱን ለማስቀጠል፤ ለማምረቻ ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ማምረትና በኢንዱስትሪው ለሚመረቱ ምርቶች ሰፊና አስተማማኝ የሀገር ውስጥ ገበያ መቅደም ይኖርባቸዋል:: ሂደቱ ሁሉንም በሚጠቅምና በመደጋገፍ ላይ እንጂ አንዱን በአንዱ ላይ በመጫን ብቻ ኢንዱስትሪን ማስፋፋት አይቻልም::

ለዚህ ደግሞ ከግብርናው ጀምሮ የአገልግሎት ዘርፉና የማምረቻ ኢንዱስትሪው ተዋናዮችና ባለቤቶቻቸው ግለሰብም ይሁን ማህበራት፣ የፓርቲ ድርጅትም ይሁን የመንግሥት የልማት ድርጅት በሃገር ኢኮኖሚ ውስጥ በሚሰሩት ሥራ (Business) ልክ የአደጋ ተጋላጭ (Business Risk) መሆን አለባቸው:: ይህ የኢኮኖሚ ሁኔታ በእያንዳንዱ ዘርፍ፣ በግብርናው፣ በአገልግሎቱና በኢንዱስትሪው የሚፈለገውን ፍትሐዊ የማዋዕለ ንዋይ ፍሰት የሚገፋ፣ በሂደት የሚያስተካክል ቅድመ ሁኔታ ነው::

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ባለው የሀብት ዓይነት፣ አጠቃላይ ኢኮኖሚው ባለበት ደረጃና በባህርዩ ላይ ተመሥርቶ ተገቢውን መንገድና ፖሊሲ ተከትሎ በመፈፀም፤ ከጅምሩ የነበረውን የፊውዳል ሥርዓት፣ የብዙኃኑን ገባሮችና የጥቂት አስገባሪዎችን ግንኙነት በመሰረታዊ ባህርዩ መቀየር አስፈላጊ ይሆናል::

ከላይ የተገለፁት ዐቢይ ተግባሮች መንግሥት በትክክል በሚቆጣጠረው ኢኮኖሚ፣ በከፊል ጣልቃ በሚገባበት የልማታዊ መንግሥት ወይም በሂደት ብዙኃኑ ገዥና ሻጭ ሆነው በሚሳተፉበትና ጥቂቶች ተፅዕኖ የማይፈጥሩበትን የገበያ ሥርዓት ዕውን በማድረግ መፈፀም ይቻላል::

በፊውዳሉ ሥርዓተ ማህበር ስለነበሩ ብቻ ተጠቃሚ የምንላቸው አስገባሪዎችን ነበር:: በመረጃ ላይ ባልተመሰረተ ገበያ፣ በአምራቹና በሀገሪቱ መሰረተ ልማት ኋላ ቀርነት እና በግዴለሽ የመንግሥት ፖሊሲ ምክንያት የብዙኃኑን ምርት ወደገበያ ስላቀረቡ ብቻ ጥቂቶች ምንም የስራ አደጋ (Business Risk) ተጋላጭ ሳይሆኑ፣ በቀላሉ ከተሳካላቸው፤ ንግድ ፈቃድ መንግሥት ቢሰጣቸውም፣ ግብር ቢከፍሉም፣ አስገባሪዎች መሆናቸውን መረዳት ተገቢ ነው:: በተመሳሳይ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት ተወዳዳሪ የሌላቸው አስመጭዎች፣ በብዙኃኑ ጥረት የተገኘ የውጭ ምንዛሬን ተጠቅመው ከውጭ ሃገር ባስገቡት ሸቀጥ በብዙኃኑ ላይ ዋጋ ጭነው የልባቸውን ካደረሱና ከተንቀባረሩ አዲሶች፣ የበለጠ አቅምና ጉልበት ያላቸው ፊውዳሎች ናቸው ማለት ነው::

በመካከል ያሉ አገልግሎት ሰጭዎች፤ የትራንስፖርት፣ የፋይናንስ ተቋማት ስላሉ፣ ስለጀመሩ ብቻ ትርፋማ ሆነው ከቀጠሉ፣ ▶

አምራቹን ካላገለገሉ፣ የአምራቹን ከፍተኛ አደጋ ካልተጋሩ ተመሳሳይ ነው::

ላቡን የሚያንጠፈጥፈው አርብቶ አደርና አርሶ አደር፣ በባህርዩ የከፍተኛ አደጋ ተጋላጭ የሆነው የግብርና ዘርፍ፣ ባመረተው ምርትና በሚጠቀምበት ሸቀጥ የሚተረፍበት ዘመናዊ ጭሰኛ ነው:: ጭሰኛና ዘርፉ በሂደት ቢቆረቁዝ ደግሞ አይገርምም፤ በዚህ ሂደት የሚመዘገብ ዕድገት ጥቂት ሲሆን፤ ባለቤቱም ብዙኃኑ አምራች አይሆንም:: ስለዚህ ተመልሶ ለዘላቂ ዕድገት አይውልም:: በሀገራችን የከተማ ኢኮኖሚ ሳያድግ ከተሞቻችን ከወረዳ ጀምሮ ያበጡት በዚህ ምክንያት ነው:: የሀገራችን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ችግሮች መንስኤ ዕድገት ብቻ ሳይሆን፣ ዕድገቱ እብጠት በመሆኑ ነው፤ እብጠት ደግሞ ሁልጊዜም ገደብ አለው::

በዚህ አውድ ከግብርናው ዘርፍ ጋር ለሚቀራረብ የሥራ አደጋ ተጋላጭ የሆነውን፣ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ፣ የቴክኖሎጂና የአስተዳደር ዕውቀት የሚጠይቀውን የማምረቻ ኢንዱስትሪውን ዕድገት መጠበቅ ሞኝነት ነው:: ከውጭ ሀገር የገባ ጥሬ ዕቃን ተጠቅሞ፣ ምርቱን በረጅም የየብስና የባህር ትራንስፖርት አንገላታና የወደብ ኪራይ ከፍሎ፤ ከዓለም ገበያ የውጭ ምንዛሬ የሚያፍስ ዘርፍ መመኘት ህልም ብቻ ነው::

ልማታዊ፣ አብዮታዊ፣ ወዛደራዊ ቢሆንም ይህን ሁኔታ ያስቻለ፣ አብሮ የነገደ ፓርቲና መንግሥትም የአዔዎች መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው:: በብዙኃኑ ምርት ላይ የሰበሰበውን ገቢ በሙስና፣ የላቀ ፋይዳና ውጤት በሌላቸው በቅንጦት መሰረተ ልማቶች ያባከነ መንግሥት እንደጥንቱ አስገባሪ ፊውዳል እንጂ ዘመናዊ መንግሥት ሊባል አይችልም::

የወቅቱ የኢኮኖሚያችን ችግሮች የተከተልነው ፖሊሲ በትክክል ስላልተፈፀመ የነበረውን የፊውዳሎች ባህርይ በዋናነት በማስቀጠሉ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው:: ባለፉት 27 ዓመታት የተከተልነውን የልማታዊ መንግሥት ፖሊሲ፣ አፈፃፀሙንና ውጤቱን በኢኮኖሚው ዘርፎች ከፋፍለን ስንመለከተው የበለጠ ግልፅ ይሆናል::

## የግብርናው ዘርፍ፤ የልማታዊ መንግሥት አቅጣጫ፣ ግብርና መሩ የኢኮኖሚ ፖሊሲና አፈፃፀሙ

አብዮታዊ የኢህአዴግ መንግሥት፣ ለሰፊው አርሶ አደርና አርብቶ አደር የቆምሁ ነኝ፤ የግብርናው ዘርፍ ድህነት የተንሰራፋበት ኢኮኖሚ ነው በማለት ልማታዊ መንግሥት ነኝ ብሎ ቢነሣ ትክክል ነበር:: ከኢኮኖሚ ሀብቶች መካከል በአፃራዊነት ብዙ የሰው ጉልበት፣ ሰፊ ለእርሻ ሥራና ለእንስሳት ግጦሽ የሚሆን መሬት እንዲሁም እጅግ አነስተኛ መዋለ ንዋይና ዕውቀት ባሉት የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ፤ ግብርና መር ፖሊሲን ቢያስቀድም ተገቢ ነበር::

ነገር ግን በተበጣጠሰ መሬትና በዝናብ ላይ ጥገኛ የነበረውን የሰብል ልማትም ይሁን የእንስሳት እርባታ "ከየት ጀምሮ የት አደረሰው?" የሚለው ጥያቄ ግን መልሱ በነበረበት ነው:: ለዘርፉ የተደረጉ ድጋፎችንና የግብዓት አቅርቦቶችን፣ የተመረቱ ምርቶችን የገበያ ሂደትና ዋጋቸውን እንዲሁም የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን መመልከት እንችላለን::

መንግሥት ለሰብል ልማቱ ዘመናዊ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ኬሚካሎች አቅርቧል፤ ነገር ግን ላለፉት 25 ዓመታት በፓርቲ ድርጅቶቹ ከአቅርቦቱ ረብጣ ገንዘብ አትርፏል:: በ2010 እና 2011 ዓ.ም. ከአቅርቦቱ የሰበሰበው የሁለቱ ዓመት ትርፍ ብቻ የማዳበሪያ ፋብሪካ ሀገር ውስጥ የሚያስገነባ ነበር:: አለአግባብ የበላተኞች ሰለባ ሆኖ አነስተኛ መጠን ማዳበሪያ ለመጠቀም፣ ለዝቅተኛ ምርታማነትና ተጠቃሚነት ተዳርጎ የኖረውን የአርሶ አደሩን ችግር ለማየት የምንችለው እንዲህ እንዳጋጣሚ ከ25 ዓመታት በኋላ በተደረገና በትክክል በማይገለፅና በሚሽሞነሞን ለውጥ ነው::

ለአርሶ አደሩ ኬሚካሎችና ምርጥ ዘር የሚቀርቡት በተመሳሳይ መንገድ ነበር:: እስካሁን የማዳበሪያ ፋብሪካ ሀገር ውስጥ የለም:: አርሶ አደሩ ለማዳበሪያ አቅርቦቱ በየክልሎቹ የፋይናንስ ተቋማት የብድር አገልግሎት ያገኛል፤ ወለዱና አመላለሱ ግን ከአራጣ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ደደቢትን፣ ጉናን፣ አብቁተን፣ አምባሰልን እንዲሁም በየክልሉ ያሉትን አርሶ አደሮችና የማዳበሪያ ዕዳቸውን መመልከት በቂ ነው::

መንግሥት "በዐሥር ሚሊዮኖች ሄክታር የሚቆጠር ለእርሻ የሚውል መሬት አለኝ" ብሎ ለውጭ ባለሐብቶች ቢሰፍርም፤ ጠብ ያለ ነገር የለም:: የእርሻ መሬቱ የሚገኘው የህዝብ ቁጥራቸው አነስተኛ በሆኑት በጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ሲሆን፤ በእርሻ ሥራ ጥርሱን ከነቀለው የኦሮምያ፣ የደቡብና የአማራ አርሶ አደር በጥንቃቄ እየተጠበቁ ዘመናት ሊያልፉ ችለዋል:: ከሰፊው አርሶ አደርም በላይ ለዚህ ዘርፍ የሚቀርብ ምርጥ ዘር፣ የሚደረግ የቴክኒክ ድጋፍ የለም:: በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል፣ በበጋ ተሰፍሮ በተረከቡት ማሳ ሌላ መሰረተ ልማት ሳይሆን መንገድ ስለሌለው በክረምት ወጥተው መግባት አይችሉም፤ ስለዚህ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ብዙ የሰው ጉልበት በሚፈልገው ሥራ ከሀገሪቱ ሕግ ውጭ በሆነ ልማዳዊ አሠራር ከመጠን ያለፈ ከፍተኛ ወጭ ያወጣሉ:: በዚህ ሁኔታ ምርት ቢያመርቱ መንገድ ስለሌለ ብቻ በወቅቱ ለገበያ ለማቅረብ በጋውን መጠበቅና ከተመረተው ምርት ዋጋ ሃያ አምስት በመቶ የሚሆን ከፍተኛ የትራንስፖርት ወጭ ይጠብቃቸዋል::

የእንስሳት ሐብት ልማታችንም ተመሳሳይ ነው:: አርብቶ አደሩ እንደ ጥንቱ ለከብቶቹ ውሃና መኖን ለመፈለግ የእንስሶቹን ጭራ እየተከተለ ነው:: የከርሰ ምድር ውሃ በልፅጎ ወይም አነስተኛ መስኖዎች ተገንብተው በያካባቢው ለራሱና ለእንስሶቹ የመጠጥ ውሃ ማግኘት ተፈጥሮ ከምትለግሰው ውጭ ለእንስሳቱ መኖ ማግኘት አልቻለም:: በቋሚ ስፍራ ላይ ባለመርጋቱ ምክንያትም ሌሎች የዘርፉ ግብዓቶችን ውጤታማነት የማይቻል ያደርገዋል::

በዚህ መልኩ የተመረተው ምርት ወደ ገበያ ሲወጣ በተለመደው መንገድ በላተኛ ነጋዴ ወረዳ ላይ፣ ጅምላ ነጋዴ አዲስ አበባ ላይ፤ ከዚያም የግብርና ምርት ላኪዎች ዘንድ ሊደርስ ይችላል:: ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ሰሊጥና ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆነውን የጥጥ ዋጋ የሚወስነው ገበያ፤ ወይም አቅርቦትና ፍላጎት አይደሉም:: አምራቹ ምንም ድርሻ የለውም:: በአምራቹ ላይ ዋጋውን የሚጭኑት ፊታውራሪዎቹ ምርት ገበያና ጅንአድ ናቸው:: የየራሳቸውን ካተረፉ በኋላ ሁለቱም የቀጣይዎች፣ የላኪዎችና የማምረቻ ፋብሪካዎች ብቻ ጠበቃ ናቸው::

ሀገሪቱ ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ቢኖራትም፤ የውጭ ምንዛሬ ገቢው ተጠቃሚ አይደለችም:: ምክንያቱም ከሌሎች በተጨማሪ ብዙው ሀብት የሚገኘው በሀገሪቱ ጠረፍ አካባቢዎች ስለሆነና እነዚህ የሀገራችን ቁም እንስሳት ለዓለም ገበያ የሚቀርቡት በሱዳንና በሶማልያ በኩል እንደሆኑ ጥናቶች ስለሚያረጋግጡ፤ የተራዘመው፣ ሕጋዊው የሀገራችን የገበያ ሰንሰለትና የመንግሥት አሠራር፣ ግብርናና ቀረጥ ጋር ተባብረው እንስሳቱን ወደኮንትሮ ባንድ ሽያጭ ስለሚገፏቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ሕገ ወጡ የኮንትሮባንድ ንግድ አደጋና ወጭ አለው፣ የኮንትሮባንድ ገበያው አማራጭ የሀገር ውስጡን ገበያ የሚያስከነዳ ባይሆን ሕጋዊ መሆንና ሀገሩን የሚጠላ ሰው አይኖርም ነበር:: ይህ ደግሞ ከመንግሥት ቀረጥ እስከ አቀባባይ ነጋዴዎች ትርፍ ድረስ መሆኑን በመረዳት፣ ማስተካከል፤ ከኬላና ከፌደራል ፖሊስ የድንበር ጥበቃ የተሻለ ዘዴ ነው:: እነዚህ ጥቂት የግብርናው ዘርፍ ምርት ነጋዴዎች ምን እንደሆኑ ከአዲስ አበባ ጀምሮ አካባቢንና ሌሎች ከተሞችን መመልከት በቂ ሲሆን፤ የአገልግሎት ዘርፉ አንድ ተዋናይ ናቸው::


በርካታ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች በደረቅ መሰረተ ልማቶች ግንባታ (hard infrastructure) ምሳሌ ሊሆን የሚችል ሥራ ተሠርቷል ይላሉ:: ትክክል አይመስልም፣ ጠ/ሚ ዐቢይ ባደረጓቸው ንግግሮች፤ ላለፉት 27 ዓመታት በሀገሪቱ ለግብርናው ዘርፍ የፈሰሰ መዋእለ ንዋይ፣ የተገነባ መሠረተ ልማት እንደሌለና ዘርፉ በሚገባው መልኩ ዘምኖ ከዝናብ ጥገኝነት እንዳልተላቀቀ አስገንዝበዋል:: ከሁሉም መሰረተ ልማቶች በፊት ለዚህ ዘርፍ ትኩረት ቢደረግና ዛሬ ይህ ዘርፍ በሁለትና ሦስት እጥፍ ቢያድግ ኖሮ ለሀገራችን ኢኮኖሚ ዛሬ ሌላ ቀን ነበር:: የአስፋልት መንገድም ይሁን የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ ቀድመው የተጀመሩትንና የተገነቡትን፣ ብዙም ውጤታማ መሆን ያልቻሉትን መሰረተ ልማቶች መገንባት ጭንቅ ሳይሆን ቀላል በሆነ ነበር::

ከሰማንያ አምስት በመቶ በላይ በግብርና ላይ በተመሰረተና በከፍተኛ ደረጃ ለዘመናዊ ማዳበርያ ጥገኛ ሆኖ ለ27 ዓመታት ለዘለቀ ዘርፍ፤ በውጭ ምንዛሬ ከባህር ማዶ እየገዛ፣ የወደብ ኪራይ እየከፈለ፣ በከፍተኛ የሀገር ውስጥ የየብስ ትራንስፖርት ወጪና ከፍተኛ ገንዘብ እያተረፈ ማዳበሪያ ያቀረበ መንግሥት፤ የሀገሪቱን ሐብት በአስፋልት መንገድ፣ በኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች እና የቅንጦት መሰረተ ልማቶች ላይ ቀድሞ ያባከነ፤ በመዲናዋና በከተሞች ለሰማይ ጠቀስ ግንባታ ቅድሚያ የሰጠ መንግሥትና ኢኮኖሚ፤ "ልማታዊ መንግሥትና ኢኮኖሚ ነበርሁ፤ ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነበረኝ" ካለ ሸፍጥ ብቻ ነው:: የሀገሪቱ የመንግሥትም ይሁኑ የግል የፋይናንስ ተቋማት፣ ሌሎች የአገልግሎት ዘርፉ ተዋናዮች ለግብርናው ዘርፍ ባዕድ ሆነው መዝለቃቸውን፣ ዘርፉን በሩቁ ብለው ግን የምርቱና የውጤቱ ጥገኛ ሆነው፣ ስላሉ ብቻ እንደፈለጉ እያተረፉ እስከ ዛሬ መቀጠላቸው ግልፅ ነው::

ይህንን ለማረም ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት ሲገባ፤ ብዙ ህዝብና ሰፊ መሬት ይዞ፣ የምግብ እህል ከውጭ ገበያ የሚሸምት ኢኮኖሚ፣ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በሚፈልግና አነስተኛ የሰው ጉልበት በሚጠቀም የኢንዱስትሪ ዘርፍ፤ "የሥራ ዕድል እፈጥራለሁ፤ በዓለም ገበያ ተወዳድሬ የውጭ ምንዛሬ አስገኛለሁ፤ ለዚህ የኢንዱስትሪ ፓርክ እገነባለሁ" ማለት ደግሞ ቀጣይ ሸፍጥ ይሆናል:: ለሁሉም መሠረቱ ግን የፊውዳሎች ባህርይ በአዲስ መልክ መቀጠሉ ነው:: የዓለም ቁጥር አንዷ ባለሐብትና ባለቴክኖሎጂ ሀገር አሜሪካ በውጭ ንግድና ሸፍጡ "ከስሬያለሁ" እያለች ባለችበት ሁኔታ የእኛን ውጤታማነት ማሰብ ድንቅና ተአምር ነው::

# “የ19 ዓመት ወጣት ነኝ፤ 27 ዓመቱን ኖርሁበት አልልም”

## ተዋናይ መኮንን ላዕከ



ተዋናይ መኮንን ላዕከ

*አዲስ አበባ ቂርቆስ (ጨርቆስ) ሰፈር ነው ተወልዶ ያደገው፤ ለቤተሰቦቹ ሁለተኛ ልጅ ነው፤ በልጅነቱ እንዲህ ታዋቂና ሕዝብ በሥራዎቹ የሚወደው አርቲስት እሆናለሁ ብሎ አስቦ አያውቅም፡፡ በትምህርት ውጤታማ እሆናለሁ፤ ካልሆነም በእግር ኳስ ትልቅ ደረጃ እደርሳለሁ የሚል ግምት ነበረው፡፡*

*በተግባረ ዕድ በኤሌክትሪሲቲ የትምህርት ዘርፍ በዲፕሎማ የተመረቀው መኮንን፣ በዙሪያው ባሉ ወጣቶች ግፊት ወደትያትሩ ዓለም ከገባ በኋላ በጊዜ ሂደት ውጤታማ ለመሆን በቅቷል፡፡ ዛሬ ላይ የፊልም ባለሙያዎችም ሆነ ተመልካቾች ቁጥር አንድ ምርጫ ከሆነው ተዋናይ መኮንን ላዕከ ጋር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ እንደሚከተለው አነጋግሮታል፡፡*

**ግዮን፡- መኩዬ አሁን ዕድሜህ ስንት ደረሰ?**

**መኮንን**፡- አስራ ዘጠኝ::

**ግዮን፡- አልገባኝም…**

**መኮንን**፡- ዕድሜዬን አይደል የጠየቅሽኝ? እንግዲህ እኔ የ19 ዓመት ወጣት ነኝ፤ ያለፉትን 27 ዓመታት በዕድሜዬ ውስጥ አልደምራቸውም::

**ግዮን፡- 27 ዓመቱን አልኖርሁም እያልከኝ ነው?**

**መኮንን**፡- የኖረ አለ እንዴ? እንዲሁ እየተንገዋለሉ፣ እህህ እያሉ መኖር ከኑሮ ይቆጠራል? አሁን ግን ያንን የሚያስረሳ ተስፋ እያየን ነው፤ ወደ ፊት ለልጆቻችን የተሻለ ሕይወት የሚያመጣላቸው፣ የኢትዮጵያዊነትን ስሜት በውስጣቸው የሚያሰርፅ መንገድ ተዘርግቷል:: መሪም ተገኝቷል::እኔም ከዚህ በመነሣት 100 ዓመት እኖራለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

**ግዮን፡- ልጅ ሆነህ በጣም ነጭናጫ ነበርህ የሚባል ነገር ሰምቻለሁ፤**

መኮንን፡- ወደኋላ እንመለስ ካልህማ ልክ ነህ:: ሲበዛ ነጫናጫ፤ ነዝናዛ የሚሉት ዓይነት ሰው ነበርሁ:: ብዙ ጊዜ ከመረጋጋት ይልቅ ቶሎ ብዬ ወደግጭት ነበር የማመራው፤ ቤት ውስጥም ሆነ ውጪ ይሄ ነበር አመሌ::

የሚገርምህ ግን በዚህ ባህሪዬ መሃል የማንበብና የመጻፍ ፍቅሬ ልዩ ነበር:: እንደ ትረካ የራሴን ጽሑፍ በቴፕ እየቀዳሁ ድምፄን አዳምጥ ነበር:: ብዙ ጊዜ ገለልተኛ ነኝ፤ ፊቴ ራሱ ለመቅረብ አይመችም፤ ሰዎች እንዲያውም ይሄ ጭፍግግ ፊት ይሉኛል::

**ግዮን፡- ታዲያ ይሄ የኮሜዲያንነቱ ባህርይ ከየት ተወለደ?**

**መኮንን**፡- ፊቴ ኮሶ ቢመስልም በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች ግን የእኔን ተጫዋችነት በጣም ይረዱ ነበር:: በርግጥ እኔም የሐምሌ ደመና የመሰለውን ፊቴን ከጎረቤት ልጆችና ከአንዳንድ የት/ቤት ጓደኞች ጋር በቅርበት ስንጫወት ነው ወደ መስከረምነት የምቀይረው:: ያኔ ልጅነቱም ነው መሰለኝ ብዙም ማህበራዊ ግንኙነት የለኝም::

አሁን አሜሪካ ሀገር የሚኖር፣ ተመስገን መላኩ የሚባል ስታዲዮም አካባቢ የሚኖር ጓደኛ ነበረኝ፤ እሱን ከረዥም ጊዜ በኋላ ሳገኘው፣ ‘አፍለኛው የሚባል የቲያትር ክበብ አለን፤ ለምን እዚያ አትመጣም?’ ሲለኝ እኔ መድረክ ላይ ወጥቼ ቲያትር መሥራት አይሆንልኝም፤ የመፃፍ ዝንባሌ ስለሌለኝ ሥልጠና ባገኝ ደስ ይለኛል አልሁት::

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ በዚያ ጊዜ የሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ሀሁ በስድስት ወር ቲያትር ሲሠራ፣ ከልጆቹ ጋር በደንብ ስለተግባባሁ፣ አዳራሽ ውስጥ ቁጭ ብዬ ሲያጠኑ እከታተል ነበር::

ለካስ ቲያትር ደስ ይላል? የሚያዝናናው ኳስ ነው ብዬ ነበር የማምነው:: አንድ ቀን ቲያትሩ ላይ የሚሠራው አንደኛው ልጅ ቀረ፤ “እኔ እችለዋለሁ” አልኋቸውና ልሠራው ገባሁ፤ ከዚያ ደብል ካስት አድርገው ያዙኝ:: እንዲያውም ሳምሶን ወርቁ፣ ‘በጣም ትችላለህ’ በሚል እንድገፋበት ሌላ ሥራ ሰጠኝ::

**ግዮን፡- በዚህ መንገድ ከጥበብ ጋር በፍቅር ወደቅህ ማለት ነው?**

**መኮንን**፡- በደንብ… አሁን ሰዎች፣ ‘ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ’ የሚሉት ነገር አለ አይደል? በዚያ ጊዜ ደግሞ የነበረ ጭብጨባ ‘አዳራሽ አንቀጥቅጥ’ ይባላል፤ በየመድረኩ እንዲህ ዓይነት ነገሮች በምሠራባቸው ቦታዎች ላይ ሲደጋገሙ፣ እውነት እኔ መሥራት እችላለሁ እንዴ? ማለት ጀመርሁ::

**ግዮን፡- እኔ በግሌ በቲያትር ውስጥ በ1980ዎቹ መገበደጃ ነበር የማውቅህ፤ ከሕዝብ ጋር በደንብ የተዋወከው በቅርብ ጊዜ ነው፤ ተሳስቻለሁ?**

**መኮንን**፡- ልክ ነህ፤ እንዳልከው በ1980ዎቹ መጨረሻና በ90ዎቹ መጀመሪያ እኔም ሆንሁ ጓደኞቼ በጊዜው በጥሩ ሁኔታ መንቀሳቀስና ከሥር መነሣት ጀምረን ነበር:: የሚገርምህ በጊዜው በጣም ጎበዝ ልጆች ነበሩ፤ ግን ግሩፕ የሚባል ነገር ተፈጠረና ሥራዎች በሞኖፖል ተያዙ::

ይሄ ነገር በጣም ያሳፍረኛል፤ እኔ እዚያው መካከላቸው ቁጭ ብዬ የራሳቸውን ግሩፕ ይዘው ወደ ሌላ ሥራ ይሄዳሉ፤ እኔም አልጠይቅም:: አሁን ድረስ አሠሩኝ ብዬ ማንም ሰው ደጅ ላይ ቆሜ አላውቅም:: ይሄን ብትጠይቅ ማንም ይነግርሃል:: ጠይቀህ ሳይሆን ሲያምንብህ ነው ሊያሠራህ የሚገባው::

በዚህ የተነሣ ትንሽ ዘግይቻለሁ:: ግን የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ሕዝብ በሚቀበለኝ ደረጃ መሥራት እንደምችል አውቀው ነበር:: በእርግጥ አሁንም ገና ነኝ፤ ብዙ ይቀረኛል::

**ግዮን፡- በፊት ብዙ የቲያትርና የሙዚቃ ክበቦች በየሰፈሩ በወጣቶች ይቋቋም ነበር፤ አሁን እንዲህ ዓይነት ነገር አለመኖሩ ጎበዝ ልጆች እንዳይፈጠሩ እንቅፋት አይሆንም?**

**መኮንን**፡- ነው እንጂ:: …ያኔ የተለያዩ አማተር የቲያትር ክበቦች በየት/ቤቱ፣ በየቀበሌው፣ በየመንደሩ ነበሩ:: አሁን ወጣት ሊግ ነው ያለው:: እነዚህን ወጣት ሊጎች ሽሽት እኮ ነው ወጣቱ ወዳልሆነ አቅጣጫ የተበታተነው::

አሁን አንድ ሥራ ላይ አዲስ ሰው ሲመጣ ደስ ይለኛል:: ሁለት ሦስት ጊዜ ከሠሩት ጋር ግንኙነት የለኝም:: እኔ ላይ ባለፈው ዘመን የደረሰው ነገር እንዳይደርስ አዳዲስ ሰዎችን እመክራለሁ:: ያለፈው አይቆጨኝም፤ እንደመማሪያም ነው የምቆጥረው:: ▶



*ተዋናይ መኮንን ላዕከ ከቤተሰቦቹ ጋር*

**ግዮን፦- በቲያትርና በፊልም ደረጃ እስካሁን ምን ያህል ሠራህ?**

***መኮንን፦-*** ቲያትሮቹ ዐሥር ይሆናሉ፤ ፊልሞቹ 39 የደረሱ መሰለኝ:: በ1994 ዓ.ም በኤች አይ ቪ ዙሪያ 'አያትየው' በሚል የተሠራው የመጀመሪያው የማስተማሪያ ፊልሜና ከክበበው ጋር የሠራሁት ቪሲዲ ወደዕውቅናው በተወሰነ ደረጃ አንደርድረውኛል::

ግዮን፦- እስካሁን ከሠራሃቸው ፊልሞች መካከል የትኛው ገፀ-ባህሪይ ይመችሃል?

መኮንን፦- 'ሜድ ኢን ቻይና' ፊልም ላይ ለሰፈሩ ልማት እየዞሩ ገቢ የሚያሰባስቡት ሰውዬ ባህሪይ ደስ ይለኛል:: ብዙ ጊዜ በሥራዎቼ ላይ ማህበራዊ ችግራችንን ማንሣት እወዳለሁ::

**ግዮን፦- ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በታየው የሕዝብ የነፃነት ትግል ላይ ከጥቂቶች በቀር ብዙዎቻችሁ አርቲስቶች "ዝም ብላችኋል" ተብላችሁ እየተወቀሳችሁ ነው፤**

***መኮንን፦-*** እኔ ዝም ብዬ አላውቅም:: በሥራዬ የመንግሥትን አካል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ነቀር እያደረግሁ ነው::

**ግዮን፦- ከዚህ በኋላ የህዝብን ብሶት በማስተጋባት ረገድስ?**

***መኮንን፦-*** በጀመርኩት መንገድ እቀጥላለሁ:: የሕዝብን ብሶት በሥራህ ከመግለጥ በላይ ምን አለ? እኔ ሁሌም ራሴን ችዬ ማድረግ የምፈልገውን ነው የማደርገው::

ሁሉንም መንግሥታዊ ሥራ በሞኖፖል እንደያዙት እንደሌሎች ሰዎች ወደመንግሥት ኮምዩኒኬሽን ቢሮ አልመላለስም:: ጧት ተነሥቼ ጠ/ሚኒስትር ቢሮ ደጅ አልጠናም:: እነዚያ አካላት ለጥቅም ሲሉ የፈለጉትን አድርገዋል፤ መንግሥትም 'ከምር የህዝብ አገልጋይ ናቸው' ብሎ ከእነሱ ውጪ ያለነው አልታየነውም ነበር፤ ውጤቱ ግን ያየነው ነው::

**ግዮን፦- ዝነኛ ነኝ ብለህ ታስባለህ?**

***መኮንን፦-*** ምን ሠርቼ? …እኛ ሀገር እኮ ትልቁ ችግር ይሄ ነው:: በትንሽ ሥራ መኮፈስ፤ ህዝብ ሲያጨበጭብልን ሌላ አዲስ ሰው ከመጣ 'ዝናዬን ይቀማኛል' በሚል መንገዱን በግሩፕ በማጠር መዝጋት፤ ዝናን ጠቅልሎ ለመያዝ ሲባል ተረግጠህ ትቀራለህ:: የሚመጣውን አዲስ ሰው በደስታ መቀበል፣ መንገድ ማሳየትና መምራት ያስፈልጋል:: ግን ብዙዎች አዲስ ሰው እንዲፈጠር አይፈልጉም::

**ግዮን፦- በአሁኑ ወቅት ለአንድ ፊልም ምን ያህል ትጠይቃለህ?**

***መኮንን፦-*** የጠየቅሁትን መች ይሰጡኛል? …ይልቅ የሚከፍሉኝን ልንገርህ፤ እኔ እስከ መቶ እየጠየቅሁ ነው:: አሁን አሁን ግን ሳልጨምር አልቀርም:: የኑሮ ወጪውም ጨምሯል::

ግዮን- በፊት ቲያትሮች ትሠራ ነበር፤ አሁን ርቀሃል፤ ምናልባት ክፍያው ይመስለኛል…

መኮንን፦- ትክክል:: መዋሸት አልፈልግም፤ ከመድረክ ሥራ ያራቀኝ ክፍያው ነው:: ብዙ ቲያትሮች ሠርቼ ምንም ያገኘሁት ነገር የለም:: ለመጨረሻ ጊዜ ቲያትር በቃኝ ብዬ ከመድረክ ስወርድ 400 ብር ነበር የሚከፈለኝ:: ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ወጥቼ፣ ታክሲ ሁሉ ገብቶ በእግሬ ነበር የምሄደው? አራት መቶ ብር ይዤ ቤተሰብስ እንዴት ነው የምመራው?

ቲያትር ስትሠራው በጣም ደስ ይላል:: አዳራሽ ሙሉ ህዝብ ታስቃለህ፤ ቤተሰብህን ታስለቅሳለህ:: ይሄ መሆን የለበትም:: ብቻዬን በነበርኩበት ጊዜ ለሙያው ስል በእግሬ እየሄድኩ ሠርቻለሁ:: መክፈል ያለብኝን መሥዋዕትነት ከፍያለሁ:: አሁን ግን ቤተሰብ አለ፤ ቅድሚያ መስጠት ያለብኝ ነገር ይኖራል ማለት ነው:: ባይሆን ወደፊት ራሴ ፕሮዲዩስ የማደርገው ቲያትር እስኪኖር መድረክ ላይ የምወጣ አይመስለኝም:: ብዙ ዘመን ሰዎችን ሳስቅ አምሽቼ እያለቀስኩ በሬ ድረስ በእግሬ ሄጃለሁ::

ጅቡን መኪና መጥቶ እስኪያሳልፈኝ ወይም እስኪያባርርልኝ ድረስ ብዙ ቀን ቆይቻለሁ:: ከዚህ የበለጠ ለሙያው ፍቅር ምን ይከፈላል? እኔ ቢሳካልኝ ወደፊት ቲያትር ፕሮዲዩስ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ት/ቤት የመክፈት ሐሳብ አለኝ፤ ሙያው ትልቅና ሀገር ሊለውጥ የሚችል እንደሆነ ስለማውቅ::

**ግዮን፦- ብዙ ጊዜ የምትሠራቸውን ገፀ ባህርያት እያዩ አንዳንዶች፣ 'ይሄ ሰውዬ ጠጅ ቤት ነው የሚያመሸው' ሌሎች ደግሞ፣ 'ከአዛውንቶች ጋር ዳማ ሲጫወት ነው የሚውለው' ይሉሃል::**

***መኮንን፦-*** እኔ ካራክተሮችን በውስጤ በመሳል ነው እንጂ ሁለቱም የተባሉት ነገሮች አይገልፁኝም፤ እኔ እኮ መጠጥ አልጠጣም፤ የምወደውን እወዳለሁ …(ሳቅ) እንኳን ጠጅ ቤትና ሌላም መዝናኛ አልገባም:: በፊት ፒያሳ እያለሁ ነው እንጂ አሁን ከቆመ አንድ ዐሥር ዓመት ሆኖታል::

**ግዮን፦- ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ እንዴት ነህ?**

***መኮንን፦-*** በቻልኩት መጠን ሁሉም ላይ አለሁበት:: ኃዘንም ይሁን ደስታ ባለችኝ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ በርግጥ የእኛ ሥራ አስቸጋሪ ነው፤ ረዥምም ወቅት በቀረፃ ስለምታሳልፍ አይመችም:: ሆኖም፣ አቅሜ በሚችለው ነገር ከሰው አልለይም::

ትዳር ላይም አለሁበት፤ ብዙ ሰዎችን ሽማግሌ ሆኜ ድሬያለሁ:: አበረታታለሁ:: ምክንያቱም እኔ በሕይወቴ ለውጥ ያየሁበት ስለሆነ:: መኖር ምን ማለት እንደሆነ የገባኝ ትዳር ከመሰረትሁ በኋላ ነው:: ራስህን እንድታይና ወደፊት ለመራመድ ትዳር ወሳኝ መሆኑን በተግባር አይቻለሁ:: ቅስቀሳን ለምርጫ ሳይሆን ለትዳር ነው የምጠቀምበት::

**ግዮን፦- "ኪነ ጥበብና ፖለቲካ ልዩነት አላቸው" የሚሉ አርቲስቶች በዝተዋል፤ እውነት ሁለቱ ይለያያሉ?**

***መኮንን-*** እንዴት ይለያያሉ? ጥበብና ፖለቲካ አንድ ናቸው:: 'በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ?' የሚባል ነገር አለ:: ፖለቲካ ላይ ቆመህ አይደል እንዴ ኢኮኖሚውን የምትመራው? አሁን ተሳሳቱ የምንላቸው ሰዎች እኮ ኢኮኖሚው መርቷቸው እኮ ነው ጉድ የሆኑት:: እነዚያ የጥበብ ሰዎች ህዝብ የሚፈልገውን ነገር ትተው መንግሥት የሚፈልገውን ለዘመናት በአደባባይ ለፈለፉ:: በፖለቲካ ውስጥ ያለው ኢኮኖሚ የጥበብ ካባቸውን ገፈፋቸው ማለት ነው::

እኔ ግን የኢኮኖሚ ጉዳይ ወይም ጥቅም አይመራኝም ብያለሁ:: እንኳንም ያኔ እነሱን አልተጠጋሁ:: የነበረውን ሥርዓት፣ የሚደረጉትን ነገሮች ሕዝብ ስለማይፈልጋቸው እኔም በዚያው መንገድ ነበር ለህዝቤ ያለኝን ፍቅር የምገልፀው:: የአፍ ድለላና በየቦታው አለሁ ማለት አልወድም፤ አላውቅበትምም::

ኑሮን እኮ እየኖርሁት ነው? ምን ቀረብኝ? ከሰው ጋር ሁሌም ስላለሁ ምን እንደጠላ ምን እንደሚወድ አውቃለሁ:: ስለዚህ በሥራዬ የሚጠላውን ነገር ስነግርለት ነበር:: ይሄ ሳይሆን ቀርቶ አሁን ማልያ ለመቀየር ዳር ዳር እንዳሉት ሰዎች ብሆን ኖሮ በዚህ ወቅት መደበቂያ እየፈለግሁ ነበር::

**ግዮን፦- በቀጣይነት ከመንግሥት ጋር ሕዝባዊ ፋይዳ ባላቸው ኪነ ጥበባዊ ሥራዎችህ ላይ እናይህ ይሆን?**

***መኮንን፦-*** መንግሥት ጋር ምን ታደርጋለህ? ለምሳሌ፦- ጠ/ሚ ዐቢይ ፕሪንስፐሉ ይመቸኛል:: ለእኔም ለልጆቼም የሰነቀው ተስፋ 'ንጉሥ' የሚያስብለው ነው:: ግን መቼም እዚያ አካባቢ አልሄድም፤ ሕዝቤ ጋር ነው የምሆነው:: በጥዋት ተነሥቼ ቅድም ወዳነሣኋቸው የመንግሥት መ/ቤት ቢሮዎች አልሄድም::

ጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤትና ኮምዩኒኬሽን ጽ/ቤት የሚያወጣውን እየጠበቅሁ ለገንዘብ ስል አልሠራም፤ እስካሁንም አልሠራሁም:: አብሮኝ ካለው ህዝብ ጎን ሆኜ የሚፈልገውን ነው የምሠራው:: ለጠ/ሚ ዐቢይ በርቀት ሆነን በሙያችን 'ይህ ማህበረሰብ ይህ ችግር አለበት' ብለን ልንጠቁማቸው ነው የሚገባው::

**ግዮን፦- እስቲ ባለቤትህንና ልጆችህን አስተዋውቀን…**


***መኮንን፦-*** ባለቤቴ ሠላም ሰማው ትባላለች፤ የመጀመሪያዋ ልጄ ኖቤል መኮንን ትባላለች:: ኖቤል ኢትዮጵያዊ ስም አይደለም፤ የአልፍሬድ ኖቤል የሽልማት ቀን ዕለት ስለተወለደች እህቴ ናት ኖቤል ያለቻት፤ ዘጠኝ ዓመቷ ነው::

ሁለተኛው ወንድ ሲሆን ናታን ይባላል:: እኔ ልዑል መኮንን ነበር ያልሁት፤ 'ራስህን ልዑል ለማድረግ ነው' በሚል ባለቤቴ ውድቅ አድርጋ ራሷ ተስማሚ ነው ያለችውን ስም አውጥታለታለች::

**ግዮን፦- የምታስተላልፈው መልዕክት፣ የምታመሰግነው ሰው ይኖራል?**

***መኮንን፦-*** ባለቤቴንና ቤተሰቦቼን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ:: በሥራዬ ሁሌም ከጎኔ ሆነው የሚደግፉኝን፣ አይዞህ የሚሉኝን አድናቂዎቼን በሙሉ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ::

**ግዮን፦- አመሰግናለሁ::**



ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

## የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስን ጽናት ሳስብ

# የሦስቱ ፓትርያርኮች አሳፋሪ ታሪክ

ነገ፣ ሐምሌ 22 ቀን፣ 2010 ዓመተ ምሕረትን ስናስብ፤ ኢትዮጵያን የወረረው የኢጣልያ ፋሺስት በዕለቱ የገደላቸውን ሰማእተ ጽድቅ ዘኢትዮጵያን ያስታውሰናል:: ቀኑ፣ ወራሪው የፋሺስት ጦር በ1928 ዓ.ም. ሰማእተ ጽድቅ አቡነ ጴጥሮስን በ11 ጥይት የገደለበት ዕለት መታሰብያ ነው፤ በዚህን ቀን በልጅነት ስማቸው "በላቸው (በላይ) እርገጤ"፤ በምንኩስና ስማቸው "አባ ኃይለ ማርያም"፤ በጵጵስና ስማቸው "አቡነ ጴጥሮስ" የተባሉት ኢትዮጵያዊ አባት፤ በሞታቸው ዕለት ቅድስናቸውን የገለጹበትና የሃይማኖት ጽናታቸውን ለኢትዮጵያውያን ያሳዩበት ዕለት ነው::

ከጥንት ጀምሮ ሀገር መውረርና የሃይማኖት አባታቸውን መግደል፣ ኢጣልያውያን ልማዳቸው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው፣ በጢባርዮስ ቄሳራቸው ውሳኔ ነው:: የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ቢፈርስ፣ ከእነሱ ወገን በኾነው በጥጦስ ነው:: በኢትዮጵያና በአቡነ ጴጥሮስም ላይ ያደረጉት ከዚህ የተለየ አልነበረም:: ኢጣልያውያን ከጊዜ በኋላ፣ "ሁሉን አቀፍ ክርስትና አለን" ቢሉም፤ አሕዛብነታቸው ስለሚያመዝንባቸው እግራቸው ደም ለማፍሰስ ይቸኩላል:: እኛ "ክርስቲያን ነን" ስንልና፤ ኢጣልያኖች "ክርስቲያን ነን" ሲሉ ታሪካዊ መነሻውም ኾነ ግብረ ገባዊ ማንነታችን ከመሠረቱ ይለያያል:: በርግጥ ሐምሌ 22 ቀን 2010 የሚከበረውን የአቡነ ጴጥሮስን የሰማዕትነት ቀን ስናስብ፤ በኢጣልያኖችና በኢትዮጵያውያን መካከል የነበረውን የክፍተት መነሻና የሃይማኖት ልዩነት ማወቅ ስለሚገባ ወደታሪክ መዛግብት ዳሰሳ አስቀድመን እንሂድ::

የኢትዮጵያ ክርስትና ታሪክ የሚጀምረው እግዚአብሔርን ያመልክ ከነበረው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አቤሜሌክ (ባኮስ) ነው፤ የኢጣልያውያን ክርስትና የሚጀምረው ግን ከአሕዛባዊውና ከኢጣልያዊው መቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ነው፤ ኢጣልያኖች ግን ክርስትናቸውን ከመቶ አለቃው ከመጀመር ይልቅ፣ ቁልቁል ሰቅለው በሰማዕትነት ከገደሉት ከሐዋርያው ጴጥሮስ ይጀምራሉ:: መጀመራቸው ባልከፋ፣ ነገር ግን የቆርኔሌዎስን የክርስትና አባት ቅዱስ ጴጥሮስንም ኢጣልያኖች ገደሉት እንጂ፤ በትምህርቱ አልተለወጡም:: ይሁንና፣ እነሱ ስለክርስትናቸው የሚናገሩትን ልዩ ልዩ ተረት ትተን ኢጣልያውያንን ክርስትናቸውን በይበልጥ ያስረዷቸው በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት መኾናቸውን አንዘነጋውም:: በተለይም ኢትዮጵያውያን በኢጣልያ ውስጥ በምትገኘው የፖፑ ከተማ የእስጢፋኖስን ቤተ ክርስቲያን ተክለው ኢጣልያውያንን የወንጌል ትምህርትና ግዕዝ አስተምረዋቸዋል::

ኢጣልያኖች ግን፣ በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት ከመለወጥ ይልቅ፣ መግደልን መምረጣቸውን ከላይ ተመልክተናል፤ እንደዚሁ ሁሉ ኢትዮጵያውያን ላይ ያከናወኑት ተመሳሳይ ድርጊት ነበር፤ ይህ ዓይነቱ ተደጋጋሚ ታሪካቸው በየዘመኑ እየተከሰተ፣ እነሱን ደም አፍሳሽ እያደረገ ያስቃያቸዋል:: ይልቁንም "ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች" እንደሚባለው፤ ኢትዮጵያውያንን እናስተምር፣ መጽሐፍ ቅዱሱን ከምንጩ እንተርጉምላችሁ፣ አስተያይተን እናርምላችሁ፤ ማለትም ፈልገው ነበር:: ለዚህ ዓላማቸውና ኢትዮጵያንም ለመበርበር፣ ታሪኳንም ለመበረዝ በማሰብ፤ በኢጣልያ በፖፑ ከተማ ያለውን የእስጢፋኖስን ቤተ ክርስቲያን፣ ኢትዮጵያን የሚሰልሉበት ተቋም አድርገው አሳደጉት:: ከዚያም እየሰለጠኑ ሀገርን የሚወሩ፣ የሚያሸብሩ፤ "ደቂቀ እስጢፋ" የሚል መጠርያ ያገኙ እስጢፋኖሳውያን ወራሪዎችን ላኩብን::

በኋላ ዘመን፣ በአጼ ሱስንዮስ ዘመን የመጡትን ፖርቱጋላውያንን ጨምሮ፤ ከቤተ እስጢፋኖስ እየሰለጠኑ የመጡት ብዙ የቬነስ ነጋዴዎች ከአጼ ዳዊት ዘመን ጀምሮ፤ እስጢፋኖሳዊነትን ለማስፋፋት ወደ ኢትዮጵያ እየሰረጉ ገብተዋል:: በአጼ ዳዊት ዘመን የነበረው፣ በአጼ ይስሐቅም የስለላ ቡድን መሪ የኾነው፣ የቤተ እስጢፋኖሱ አንቶንዮ በርቶሊ በጣልያን፣ የፍሎሬንስ ተወላጅ የኾነው የዚህ ታሪክ ተጠቃሽ ነው:: እንደዚሁ ሁሉ፣ ሌላኛው ከአጼ ዳዊት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው፤ የአጼ ዘርዐ ያዕቆብ የውጭ ግንኙነት ጉዳይ አስፈጻሚ የነበረውና በተለይ፣ ወደ ሮሙ ሊቀ ጳጳስ ልዩ መልእክተኛ ኾኖ የተላከው፤ ፔትሮ ራምቡሎ የተባለ ኢጣልያዊ ተጠቃሽ ነው:: የእነዚህ መልእክተኞች ስብስብ ነው "ደቂቀ እስጢፋ" እየተባለ ሀገራችን ኢትዮጵያን በአንድ ዘመን ያወከው:: "እስጢፋ" ማለትም "እስቲፋኖ" የሚለው የጣልያንኛ አጠራር የፈጠረው ምኅጻረ ቃል ነው:: በተለይ፣ እዚያችው መንበረ ፖፑ ካለባት ቫቲካን ውስጥ፤ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከጣልያናያውያን ቤተ እስጢፈፋኖሶች ጋር ለብዙ ጊዜ የሃይማኖት ክርክር እንዲያደርጉ ፖፑ ለኢትዮጵያውያን ማረፊያ ስፍራ አዘጋጅቶ፤ በአጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን እንደተሰጣቸው ፍራንሲስኮ አልፋሬዝ ጽፏል::

በኢትዮጵያም፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ የእስጢፋኖሳውያን ዋና የመከራከርያ ሥፍራ በመኾኑ፤ መካነ እስጢፋኖስ የሚል ስያሜ ማግኘቱን ኡቲንፎርግ የተባለው ተመራማሪ፤ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ካርታ ባሳየበት መጽሐፉ ገልጧል:: ለመጀመርያ ጊዜ፣ በኢጣልያ ካለው ቤተ እስጢፋኖስ በኩል በተደረገው ጥሪ መሠረት፤ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን ጨምሮ በኢየሩሳሌም የነበሩት አባ ጴጥሮስና አባ ኒቆዲሞስ በኢጣልያን ፍሎሬንት ተገኝተው ከቤተ እስጢፋኖሶች ጋር ተከራክረዋል:: በሀገር ቤትም በሐይቅ መካነ እስጢፋኖስ ከደቂቀ እስጢፋ ጋር ሰፊ ክርክር አድርገዋል::

የአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ጥንታዊ ዜና መዋዕልን መሠረት በማድረግ፣ "የዳዊት አራተኛ ልጅ የኾነው ዘርዐ ያዕቆብ 44 ዓመት ከ2 ወር ነገሠ፤ የንግሥና ስሙም ቆስጠንጢኖስ ተባለ፤ በዘመኑም ስለሃይማኖት ፋክክር ተነሥቶ ነበር፤ ምሥጢር ተገልጾለት፣ መጽሐፈ ምሥጢርንም እስኪደርስ ድረስ፤ አባ ጊዮርጊስ ከአንድ ፈረንጅ ደቀ እስጢፋ ጋር ተከራክሯል" የሚለውን የዜና መዋዕል ንባብ በመጥቀስ፤ ፈረንሳዊው የታሪክ ሊቅ ባሴትም በዘመኑ የነበረውን የደቂቀ እስጢፋንና የኢትዮጵያውያንን ክርክር አሣይቷል::

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ብቻም ሳይኾን የተከራከረው፣ ከኢትዮጵያውያን ወገን የአባ ጴጥሮስና የአባ ኒቆዲሞስ ክርክርም በየአንድምታው መጽሐፍ ተጠቅሶ ይገኛል:: ከፍሎሬንቱ ጉባኤ በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ላይ ምንም ዓይነት ክርክር የሚያነሡትን "የቤተ እስጢፋኖሳውያን የልዮን ቡድኖች ናቸው" ለማለት፣ "ደቂቀ እስጢፋ" የሚል ስያሜአቸው እየገነነ መጥቷል:: ደቂቀ እስጢፋ ማለትም እውነተኛውን የክርስቶስን ትምህርት በመተዋቸው "ማኅበረ ኬልቄዶን" ተብለው ስለመጠራታቸው የተሰጣቸው ስያሜ ኾኖ ተንጸባረቀ::

ይህን የደቂቀ እስጢፋን ልዮናዊ ትምህርት ለመከላከል፤ አጼ ዘርዐ ያእቆብ በዘመናቸው "ማኅበረ ቅዱሳን" የሚል የሊቃውንት ኅብረት በኢየሩሳሌምና በሰሜናዊት ኢትዮጵያ ከሰዋ ላይ አስፍረዋል:: ከሰዋ ማለትም ከሸዋ የሄዱ ለማለት እንደኾነ ግልጽ ነው:: በዚህ ገዳም የደቂቀ እስጢፋን ሙግት የሚገልጹ ልዩ ልዩ ሰነዶች ተገኝተዋል:: አጼ ዘርዐ ያዕቆብ አብዛኛውን ጊዜውን ከመንገሡ በፊት ያሳለፈው በዚህች ሰሜናዊት ኢትዮጵያ ከሰዋ ወይም እደ ሰዋ ገዳም ነበር፤ ይህም የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የቆብ ልጆች አባ በጸሎተ ሚካኤል፤ አባ ሳሙኤል ዘደብረ ከሰዋ፤ ከሸዋ ሄደው የመሠረቱት ገዳም ነበር:: በዚያ ሰፍረውም የነበሩት የሸዋ ሰዎች እንጂ እንደዛሬው የ"ትግራይ" ሰዎች አልነበሩም፤ ዘመኑን ለማወቅ በዚያው ዘመንነት ታሪኩን ከመንገር ይልቅ ከዛሬ ዘመንና ማንነት ጋር አጣልዘው በግእዝ ስም ያለ ልፋፊ ሐሰት ▶

የሚተረጉሙ፤ የሚጽፉም ኾነ የሚናገሩ ወይም ዘጋቢ ፊልም ያጠናቀሩ መኖራቸውን ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም::

የደቂቀ እስጢፋ ዋና ዓላማቸው፣ ሀገሪቱን በሃይማኖት አበጣብጦ መንግሥት መገልበጥ ነበር፤ ምን አልባትም ይህ ዓላማቸው አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ላይ ባይሳካላቸው በአፄ በእደ ማርያም ጊዜ የቤተ ክህነቱን ሥራ ተጋርተው፤ የመንግሥትን ሓላፊነት ተካፍለው መሥራት ጀምረው ነበር:: መንዝ ውስጥ "ምስሐለ ማርያም" ላይ ደቂቀ እስጢፋ የሳሉት ማርያም ከልጇ በስተግራ በኩል ሆና የምትታይበትና መላእክት የሌሉበት የማርያም ስዕል፤ የኢጣልያኖቹን ልዮናዊ ትምህርት መሠረት ያደረገ በመሆኑ (አሁን በገድለ እስጢፋኖስ የአማርኛ ትርጉም መጽሐፍ መግቢያ ላይ የተሳለው ዓይነት) ስዕሉ ወርዶ በዘመኑ "አትሮንሰ ማርያም" ዕቃ ቤት ለታሪክ ተቀምጦ ነበር:: በዘመኑ የነበረው የመራቤቴው አቡነ መልከ ጼዴቅ ተከራክሮ ደቂቀ እስጢፋን ስለረታቸው ስዕሉን የሳለውን ኢጣልያዊ ደቀ እስጢፋ ብራንካ ሊዎኔንን አውግዟል፤ የመንዝ ሰዎች፣ የተሳለውን ስዕል "አንቀበልም" በማለታቸው ደቂቀ እስጢፋን ከሀገር መንደሩ አስወጥቷቸዋል::

በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ተጀምሮ ያልተሳካው፤ የአፄ በእደ ማርያምን መንበር የነቀነቀው የኢጣልያኖቹ መልእክተኞች የደቂቀ እስጢፋ እንቅስቃሴ በአፄ ሱስንዮስ ዘመን መልኩን ቀይሮ ብዙ ደም አፋሷል:: የኢጣልያኖቹን የጦርነት ሁኔታ የዘገበው ስንክሳራቸው እንደጻፈው፤ "ኢትዮጵያ ከሩቅ ምሥራቆች ጋር የነበራት ግንኙነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል" በሚል የኢትዮጵያን ሥልጣኔና የበላይነት ከመፍራት ይጀምራሉ:: የዮሐንስን ራዕይ ሲያነቡ፣ የጸሐይ መውጫ ሕዝቦች ሥልጣኔ የዓለም መነጋገርያ ሊኾን እንደሚችል ትንቢቱን እየመረመሩ ኢጣልያኖቹ ስለትንቢቱ ፍጻሜም ተጨንቀው ነበር::

ከዚህም ጭንቀታቸው የተነሣ ኢትዮጵያን ለመውረር ወሰኑ፤ መውረራቸው ፍጻሜ እንዲኖረው የሐሰት ፕሮፖጋንዳ አስቀድመው መለፈፍ ጀመሩ:: ኢትዮጵያ ውስጥ የዘርም ኾነ የሃይማኖት ጭቆና "አለ" ብለው ማውራት የጀመሩት ያኔ እነርሱ ናቸው፤ በዘመነ ኢሕአዴግ እንደተጻፈው፣ "የቡርቃ ዝምታ" መጽሐፍ ዓይነት፤ ወይንም የሃይማኖት ልዩነትን ከብሔር አንጻር ለመፍጠር ቀድሞ፣ ኢጣልያዊው ፕሮፌሰር ካርሎ ኮንቲሮንሲኒና አሜሪካዊው ትርሚንግሀም ስፔንሰር እንዳቀነባበሩት ዓይነት ገድለ እስጢፋኖስ የተባለ "ልፋፈ ሐሰት" ዓይነት መጽሐፎች፤ ከወረራው በፊትም ኾነ በኋላ የሃይማኖትና የዘር ግጭት ለማስነሣት ተዘጋጅተዋል:: የእነዚህ ኀትመቶች አካል አንዱ የኾነውና ነጮችን ያስቆጣል የተባለው መጽሐፍ "ኢትዮጵያ፡ የባሩድ በርሜል" ተብሎ የተተረጎመልን ኢጣልያንያዊው ጸሐፊ የጻፈው የውርደት መጽሐፍም ታትሞ ለዓለም ተሰራጭቷል:: በእነዚህ ፕሮፓጋንዳዎች የታጀበው የፋሺስት ኢጣልያ እንቅስቃሴ፤ በ1928 በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መልኩን ቀይሮ በእነ ሞሶሎኒ መልእክተኞች በእነግራዝያኒ መሪነት ኢትዮጵያ ተወረረች::

ይህንን ወረራ አልቀበልም የሚሉት ታላቁ ሰማዕተ ጽድቅ አቡነ ጴጥሮስ በዘመኑ ተከሰቱ:: በተለይም በዚያ የፋሺስት ኢጣልያን ወረራ ጊዜ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለፋሺስቱ የሚሠዉ ባንዳዎችን የሚከላከሉት አርበኞችን ያጽናኑበት የአቡነ ጴጥሮስ ቃለ ምዕዳን የማይረሳ ነው:: አቡነ ጴጥሮስ፣ ወደ ቆላስይስ ሰዎች ምዕራፍ ሦስት ከቁጥር ዐሥራ ሁለት



*አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት*

ላይ የተጻፈውን፣ "እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ" የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስ የኢጣልያን ፋሺስት እንዲመክቱ ሀገራቸውን እንዲጠብቁ አርበኞችን አበረታትተዋል፤ ሀገራቸውን ላይክዱ ማዕተባቸውን ላይበጥሱ ለራሳቸውም ቃል ገብተዋል:: ሰማዕተ ጽድቅ አቡነ ጴጥሮስ፣ "ለኢጣልያ አንገዛም፤ ሃይማኖታችንን አንለውጥም" በማለት ጸኑ፤ እስከማይጨው ድረስ ከንጉሡ ጋር ዘምተው ለሞቱት ፍትሐትና ጸሎት በማድረግ ለሀገራችን ኢትዮጵያ መሥዋዕት በመኾን ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል::

አቡነ ጴጥሮስ፣ ይህንን መሥዋዕትነት የመረጡት በኢጣልያው መንበረ ፓፕ የሮሙ ፓፕ እኩሌታ የኾነ ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚችል ተነግሯቸው እምቢ በማለታቸው ነው:: በግብጽም በአቡነ ቄርሎስ በኩል ልዩ ሹመት ማግኘት እንደሚችሉ ተሰብኮላቸዋል፤ እርሳቸው ግን "እምቢኝ" ብለዋል፤ ለራሳቸው ሹመት ለማዳበርና ሽልማት ለማግኘት ከሀገር ተሰደው በግብጽ ወይም በዘመኑ በነበረችው አሜሪካዊት ሮም መንበር መዘርጋት ሳያስፈልጋቸው መከራን ተቀበለው በሰማእትነት አረፉ::

የአቡነ ጴጥሮስን ታሪክ ማንጸርያ አድርገን ወደዛሬው አባቶቻችን ታሪክ በህሊና ተመልሰን ፍርዱን ለእግዚአብሔር እንስጥ:: በአቡነ ጳውሎስ ፓትርክና ለመጀመርያ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ልዩነቱና ሥርዓት አልበኝነቱ መጀመሩን ሳንዘነጋ፤ የአሁኑን የአቡነ ማትያስንና የአቡነ መርቆርዮስን ዕርቅና አንድነት በይሁንታ እየተቀበልን፤ የነበሩበትን የሲኖዶስ ዓይነት፣ ፓትርክናና የሃይማኖተኝነት መንገዳቸውን የኋሊት ሄደን ስንመረምረው፤ የቤተ ክርስቲያን አሳፋሪ ገጽታ እንደነበር ታሪክ ጸሐፊዎች ሳይዘግቡት እንዳያልፉ አሳስባለሁ::

አቡነ ጴጥሮስ በነበረው የፋሺስት ወረራና ግድያ ጊዜ ንጉሡ ወደ ውጭ ለአቤቱታ በሄዱበት ወቅት እንደዘመኑ አባት ተብዬዎች የፋሺስትን ጦር ፈርተው ሀገራቸውን አልካዱም፤ ንጉሡን ተከትለው አልፈረጠጡም:: አቡነ ጳውሎስ፣ በደርግ ዘመን ሞትን ፈርተው፣ ወደ ውጭ ሀገር ኮብልለው መኖራቸውን የምንረሣው አይደለም፤ የዛሬው ፓትርያርክ አቡነ ማትያስም በደርጉ ዘመን፣ ሀገር ከድተው፣ ከሲኖዶስ አባልነታቸው ተሰርዘው መኮብለላቸው ሳያንስ፤ ጳድቅ ወመናኝ የነበሩትንና የሾሟቸውን ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን መራገምና መሳደባቸው፤ ከምን የመጣ እንደኾነ አይጠፋንም:: አቡነ መርቆርዮስም ቢኾኑ፣ በተራቸው ፓትርያርክ ኾነው ሳለ፣ መንጋውንና ቤተ ክርስቲያንን ትተውና ሞትን ፈርተው፤ በኢሕአዴግ ዘመን ወደአሜሪካ መንጎዳቸው ከአንድ ፓትርያርክ ይጠበቅ ነበርን? ነገ በዓላቸውን ከምናከብረው ከአቡነ ጴጥሮስ ታሪክ ይህን አላየንም፤ በየዓመቱ የአቡነ ጴጥሮስን ሐውልት ቀለም እንደካባቸው የቀለም ዓይነት ከሚያሳድሱትና ከሚባርኩ፤ አባቶችም ስለተሰየሙለት ሕዝብና ሀገር ሞትን መፍራት አይጠበቅም:: "ወዮላችሁ! እናንተ የነቢያትን መቃብር የምታሳምሩ" የሚለው ኃይለ ቃል ከቶ ለማን ይኾን የተጻፈው? ለቄሳርያውያን የሃይማኖት መሪዎች የተጻፈ አይደለምን?

በርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ስንኖር፤ ሞት፣ መከራ፣ ግርፋት፣ መታሠር፣ ይኖራል፤ ነገር ግን ዓለምን ለናቀ መነኩሴ ወይም ጳጳስ፤ ይሄ ጥሪው እንጂ እርግማን አይደለም:: ይህንንም ጥሪ ሐምሌ 22 ቀን 1928 ከተቀበሉት ሰማዕት ታሪክ መረዳት ይቻላል:: በዮሐንስ ራእይ ምእራፍ ሠባት ላይ እንደተጻፈው፤ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ፣ ሐምሌ 22 ቀን፣ ሀገርና ሕዝብን ሲጠብቁ የነበሩት አቡነ ጴጥሮስ፤ በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ሕዝብ በተሰበሰበበት በ11 ጥይት ተረሽነው ስለሀገራቸውና ስለሃይማኖታቸው ሰማእትነትን ተቀበሉ:: ይህንን የሰማእትነት ዘመን በተመለከተ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የኾነውን የዮሐንስ ራእይን የሚተረጉሙ መናንያን የይሁዳ ነገድ 12 ሺ ሰዎች ለዚህ ጥሪ መጠራታቸውንና ብዙ ብሔረሰቦች በኢጣልያን ፋሺስት ወረራ ስለሀገራቸው ሊሞቱ እንደሚችሉ የዮሐንስ ራእይ ምእራፍ ሰባትን በተረጎሙበት መጽሐፋቸው አስቀድመው ተናግረው ነበር::

በትንቢት መጽሐፍ ሳይቀር የተጻፈው፣ የፋሺስት ጣልያን ወረራ የኾነውና በኢትዮጵያዊው ሰማዕተ ጽድቅ አቡነ ጴጥሮስ ላይ የተላለፈው የሞት ፍርድ አባቶች በሀገራቸው ኾነው ከሕዝባቸው ጋር የሰማእትነት መንገድ እንዲመርጡ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ማስተማርያ ይኾን ዘንድ ተጻፈ:: የሰማእቱ አቡነ ጴጥሮስን ጽናት ስናስብ፣ ኢትዮጵያን እየካዱ ይልቁንም በኾነ ባልኾነው ዜግነታቸውን እየቀየሩ የሚኮበልሉ ፖለቲከኞች የኾኑ ጳጳሳትን ማየት እንዴት ያሳፍራል!!! ዛሬ ላይ፣ "በባሌ" የወጡት አቡኑ "በቦሌ" ሊገቡ እንደኾነ በሰማንበት በአሁኑ ሰዓት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ዕርቅ ሲባል ደስታችን ወደር የለውም፤ ነገር ግን አባቶች ያለፉውን አሳፋሪ ታሪካቸውን ትተው፤ ከዚህ በኋላ ዘመን ያጸደቀውን፣ ጊዜ የወለደውን የፖለቲካ ትኩሳት "አይመለከተንም" በማለት ለቤተ ክርስቲያንና ለኢትዮጵያ የሚበጀውን በጽናትና በሰማእትነት እንዲታገሉ ከሰማእተ ጽድቅ አቡነ ጴጥሮስ ታሪክ መማር ይበጃቸዋል:: ይቆየን !!!

*"ኵሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንዑ::"*

*ገለቶማ!!!*

*ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ*
*የጥንታውያን ቋንቋዎችና ጽሑፎች ተመራማሪ*



# "የቂሊንጦን የእሳት ቃጠሎ ያስነሳው ፤ የታጋይ ልጅ ነው"

## ካፒቴን መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ

*በፎቶ ከሄሊኮፕተር ላይ ጋ ከተረፉ በኋላ በግመል ሲወስዱት*

*መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፣ በጎጃም ክ/ሀገር መርጡለ ማርያም በምትባል ከተማ ነው ተወልዶ ያደገው፡፡ በ1999 ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት የአየር ኃይል ባልደረባ ለመሆን ችሏል፡፡ ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር የትራንስፖርትና የውጊያ አውሮፕላኖችን በማብረር ብቃቱ ከተረጋገጠ በኋላ፣ በቋሚ የጦር ሄሊኮፕተር አብራሪነት በመመደብ ከሠባት ዓመት በላይ በአየር ኃይል አባልነት ሀገሩን አገልግሏል፡፡*

*ከጊዜ በኋላ ባለው የፖለቲካ ልዩነትና አንዳንድ ጉዳዮች የተነሣ፤ ለእስር የተዳረገውና በሽብርተኝነት የተወነጀለው መቶ አለቃ ማስረሻ፤ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ በሰጠው ትርጉም በእስር ሕይወቱ ከባድ መከራዎችን አስተናግዷል፡፡ አሳሪዎቹ በመደበኛነት ከመሰረቱበት የሽብርተኝነት ክስ ባሻገር፤ 'በቂሊንጦ የተነሣውን የእሳት ቃጠሎ ያቀናበረው እሱ ነው' በሚል የሐሰት ውንጀላ ብዙ ግፍ ፈፅመውበታል፡፡*

*የዋልድባ መነኮሳት፣ አግባው ሰጠኝና ሌሎች ታሳሪዎች፤ በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የከፋ በደል ሲፈፅምበት እንደነበር የተናገሩለት፤ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ ለመሆኑ ማነው? የእስር ቤት ሕይወቱና አጠቃላይ የፖለቲካ ተሳትፎውስ ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅና ማስረሻ ሰጤ፤ በሥራ አጋጣሚ፣ በድሬዳዋ ከተማ በተገናኙበት ወቅት ያደረጉትን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡*

**ግዮን፡- ለመሆኑ የአየር ኃይል አባል ለመሆን መነሻህ ምን ነበር? ዕድሉንስ እንዴት አገኘኸው?**

**መቶ አለቃ ማስረሻ፡-** ማንም ሰው ሀገሩን በተለያየ መንገድ ማገልገል ይፈልጋል፤ እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ የአየር ኃይል አብራሪነት ፍላጎቱ ስለነበረኝ ነው ወደ አየር ኃይል አብራሪነት ለመግባት የቻልሁት:: በርግጥ ሂደቱ ከባድ ነው:: ፓይለት ስትሆን ሜዲካል አለ፤ የፖለቲካ አመለካከትህ ይታያል፤ ከዚህ ሌላ የግለሰቦች ፈቃደኝነትም አንዳንዴ አብሮ ይታያል:: እነዚያ ግለሰቦች ካልወደዱህ፣ 'ጣቱ አጭር ነው፤ እግሩ አጭር ነው' እያሉ የተለያዩ ምክንያቶች እየሰጡ ሊያባርሩህ ይችላሉ::

**ግዮን፡- "መከላከያ የሕዝብ ነው፤ ከወገንተኝነት የፀዳ፣ ገለልተኛ ነው" ይባላል:: አንተ ደግሞ አየር ኃይል ስትገባ የፖለቲካ አመለካከት መስፈርት እንደሆነ እየነገርከኝ ነው፤**

**መቶ አለቃ ማስረሻ፡-** እኔ ወደ አየር ኃይል የገባሁት በ1997 ዓ.ም ከታየው የሕዝብ ንቅናቄ በኂላ ስለሆነ፤ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ የፖለቲካ አመለካከትህንና እነሱን የማትቃወም መሆኑን ያጣራሉ:: የቃል ኢንተርቪው ላይ በተለያየ መንገድ ይሄንን ነገር ይጠይቁሃል:: 'ከፖለቲካው ነፃና ገለልተኛ የሆነ' የሚለው እንደ መመሪያ ቢሆንም አይሠራም፤ የሌለ ነገር ነው::

በዚህ መልክ በሰዓቱ፣ አንድ ሺህ ሰባ የምንሆን ሰዎች ነበርን፤ በመጀመሪያ አምስት መቶ ያህሉ በሜዲካል ምርመራ ወደቁ:: የተቀረነው አምስት መቶ ያህል ሰዎች ለተሞክሮ ተብሎ ወደ ትግራይ ክልል ተላክን:: እዚያ በሚገኘው የምድር ጦር፣ 24ኛ ክ/ጦር ውስጥ ለሦስት ወር ያህል አገልግያለሁ:: በዚያ የተሞክሮ ጊዜ ውስጥ የከዳ አለ፤ የጠፋ አለ:: በምን ምክንያት እንደሆነ ሳይታወቅ እንደወጡ ያልተመለሱና በዚያው የቀሩ አባላትም አሉ::

2000 ዓ.ም ላይ አራት መቶ ያህል ለፓይለትነት የተመለመልን ሰዎች፣ ከትግራይ እንድንመለስ ተደረገ:: የበረራ ትምህርት፣ በደብረ ►

ዘይት አየር ኃይል ተጀመረ፤ ትምህርቱ በጣም ከባድ ነው:: ዲሲፕሊኑም በዚያው መጠን ከባድ ነው:: ለስድስት ወር ያህል ከግቢ አልወጣንም፤ ከማንኛውም ሰው ጋር እንድንገናኝ አይፈቀድም:: በዚህ መካከል ብዙ ልጆች ወድቀዋል:: ሰልጣኙ እየተንጠባጠበ አራት ልጆች ብቻ ነው የተመረቅነው::

**ግዮን፡- ከምርቃቱ በኋላ የነበረው የሥራ ሂደት ምን ይመስላል?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ከተመረቅሁ በኋላ፣ በ2002 ዓ.ም የትራንስፖርት አውሮፕላን፣ ስድስት ወር አብርሬ ነው ወደ ተዋጊ ሄሊኮፕተሮችና የጦር ጄቶች የተዘዋወርሁት:: 2003 ዓ.ም ላይ በይፋ ደምወዛችን እየተከፈለን፤ ቋሚ የአየር ኃይል ባልደረባ መሆናችን ተረጋገጠ:: ከዚያ በኋላ ሱዳን ዳርፉር ለነበረው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ የቡድን አባል በመሆን አንድ ሄሊኮፕተር ይዤ ገብቻለሁ::

**ግዮን፡- የዳርፉር ቆይታህ ምን ይመስላል?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** እዚያ ባለሁበት ሰዓት አውሮፕላኖቹ አቅማቸው ተዳክሟል፤ ስፔር ፓርት አይቀየርልንም ነበር:: ከዚህ የተነሣ ብዙ ጊዜ ለአደጋ ተጋልጫለሁ:: ሐምሌ 3/2003 ዓ.ም ከአየር ላይ ወድቄያለሁ:: አውሮፕላኑ ከጥቅም ውጪ ሲሆን፤ እኔ በፓራሹት ወርጄ ተርፌያለሁ:: በየዓመቱ ያን ቀን አከብረዋለሁ::

በጊዜው፣ የእኔ መውደቅ፤ አንዳንድ ድራማ የሚመስሉ ነገሮች ተጨማምረውበት ስለነበር፤ እኔን ወደ ሌላ ነገር ውስጥ ሲከተኝ፤ እግረ መንገድ የእነሱንም ድብቅ አጀንዳ ያየሁበት አጋጣሚ ነው:: አውሮፕላኑ የወደቀው ቻድ ድንበር ላይ ነው:: እኔን አርሶ አደሮች አንሥተው፣ በግመል ጭነው ወደ ከተማ ሲወስዱኝ፤ በሬዲዮ መገናኛ ላይ የደወለልኝ አንድ የህወሓት አመራር፣ 'እንኳን እግዚአብሔር አተረፈህ' አላለኝም፤ 'አውሮፕላኑ መነሣት ይችላል ወይ?' ነው ያለኝ፤ የሚቀድመው 'እንዴት ሆንህ? ጤንነትህ በምን ሁኔታ ላይ ነው?' የሚል ነበር:: በጊዜው በጣም ስሜታዊ ሆኜ የያዝሁትን መገናኛ ሬድዮ ወርውሬዋለሁ::

በዩናይትድ ኔሽንስ ሆስፒታል፣ በፓኪስታኖች የተወሰነ ዕርዳታ ከተደረገልኝ በኋላ፤ ወደ ኢትዮጵያ አምጥተው ባህር ዳር ፓፒረስ ሆቴል ውስጥ፣ የቁም እስረኛ አድርገው ነው ያስቀመጡኝ::

**ግዮን፡- "የያዝኸውን የጦር ሄሊኮፕተር ጥለሃል" በሚል ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ዕርምጃ ተወስዶ ያውቃል?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ከእኔ በፊት የተለያዩ የጦር አውሮፕላኖች በተደጋጋሚ ይወድቃሉ:: እንዲያውም የእነሱ፣ የህወሓቶች ታጋይ የነበረ ወደ ስድስት አውሮፕላኖች አጋጭቷል፤ ከአየር ላይ ጥሏል:: 2006 ዓ.ም ድሬዳዋ ላይ አንድ አንቶኖቭ ጥሏል:: ብዙ ጊዜ ደግሞ ይሄ የሚሆነው፣ በቴክኒክ ብልሽት ሳይሆን፤ በአብራሪዎቹ ብቃት ማነስ ነው:: የእኔ ግን የቴክኒክ ችግር ነው፤ ቀደም ብዬም የሄሊኮፕተሩ ብቃት እያነሰ መሆኑን፣ የቴክኒክ ችግር እንዳለበትና በቂ ጥገና ከነመለዋወጫ እንዲያገኝ ጠይቄ ነበር:: ቴክኒሺያኖች ጭምር ይሄን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል አሳውቀዋል::

ይሄ ሁኔታ ተመርምሮ፣ ችግሩ ከእኔ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፤ ከቁም እስረኝነት ተለቅቄ ወደ ዳርፉር በመመለስ የነበረኝን ጊዜ አጠናቅቄ ተመልሻለሁ::

**ግዮን፡- አንድ የአየር ኃይል ባልደረባን፣ በሆቴል ውስጥ እስረኛ አድርጎ ማስቀመጥ ይፈቀዳል?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ሕጋዊ አግባብ የለውም:: ግን እነሱ፣ ማንኛውም ሆቴል ውስጥ ሳይሆን፤ 'የራሳችን ነው' ብለው የሚያስቡት ሆቴል ውስጥ ሰዎችን አስረው እንደሚያስቀምጡ መቶ ፐርሰንት ርግጠኛ ነኝ:: ይሄ ሙሉ በሙሉ በእኔ ላይ ታይቷል:: የሚከታተለኝ ደህንነትና ጠባቂ አለ፤ መውጣት አልችልም፤ ቤተሰቦቼም ወደ ሀገር ቤት መምጣቴን አያውቁም:: በከፍተኛ ጥበቃ ውስጥ ነበርሁኝ::

**ግዮን፡- ወደሥራህ ከተመለስህ በኋላ ምን ተፈጠረ?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** የዳርፉር ግዳጃችንን ጨርሰን፣ ወደ አየር ኃይል ከተመለስሁ በኋላ፤ ብዙ ነገሮችን ታዝቤያለሁ:: ቤቱ ሙስና የተንሰራፋበት፣ የጥቅም ሰንሰለትና ዘረኝነት፣ እጅግ በጣም የገነነበት ሆኖ ነው ያገኘሁት:: ዕውቀት ያለበት ቤት ነው ተብሎ ይታሰባል:: እውነታው ግን ያ ሳይሆን የብሔርተኝነትና የማን አለብኝነት ስሜት በግልፅ የሚታይበት ተቋም ነው::

ከላይ እስከ ታች፣ የአንድ አካባቢ ሰዎች፤ ከብሔር አልፈው በሰፈርና በመንደርተኝነት የተቆላለፉ ናቸው:: ቤዝ አዛዡ፣ ኦፕሬሽን ኮማንደሩ፣ ዊንግ ኮማንደሩ፣ ቴክኒካል ዊንግ ኮማንደሩ… ሁሉም ቦታ ላይ የአንድ አካባቢ ሰዎች ናቸው የተመደቡት:: ይሄ ተዋጊ ሄሊኮፕተር ውስጥ፤ ወይም ምድብ ውስጥ ያለ አደረጃጀት ነው:: እስከሠራተኝነት ድረስ ወርደው ሁሉንም የተቆጣጠሩት የህወሓት ሰዎች ናቸው::

**ግዮን፡- ዳርፉር እያለህ፣ ቻድ ድንበር ላይ የምታበረው የጦር ሄሊኮፕተር፣ በቴክኒክ ብልሽት ሲወድቅ የአንተ ሕይወት ተርፏል፤ ችግሩ የቴክኒክ ከሆነ፣ ከሚመለከተው አካል የተገኘ የካሣ ክፍያ ነበር?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** እኔ ምንም የደረሰኝ ነገር የለም፤ በርግጠኝነት፣ እነሱ ግን በአውሮፕላኑም በእኔም ካሣ ተቀብለውበታል:: እዚህ ከመጣን በኋላ፣ ካሣ እንዳልጠይቅ ፈልገው ነው መሰል፤ ያንን ኬዝ እያነሡ ለማሸማቀቅ ይሞክሩ ነበር:: ራሴን ከጉዳት በመጠበቄና ሙያው የሚያዘውን ሕግጋት ጠብቄ፣ ከአቅም በላይ በሆነ የቴክኒክ ችግር፣ አውሮፕላኑ በሰው ላይ ጉዳት በማያደርስበት ቦታ ነው እንዲወድቅ ያደረግሁት:: ያ በዩናይትድ ኔሽንስ ተሸላሚ አድርጎኛል::

**ግዮን፡- ወደ እስሩ እንምጣ፤ እንዴትና በምን ምክንያት ነው የታሰርኸው?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** በተደጋጋሚ ምሁራን ሲሰደዱ እናያለን፤ ማንነት መሰረት እየተደረገ ብዙ ሰዎች ሲታሰሩ፣ ጋዜጠኞች ሥራቸውን እንዳይሠሩ ሲዋከቡ እናያለን:: የዜግነት ግዴታቸውን በሚወጡና መብታቸውን በሚጠይቁ ሰዎች ላይ፣ መንገላታት ሲፈፀም በመመልከታችን፤ የተወሰንን ሰዎች በአየር ኃይሉ ውስጥ 'ለምን?' የሚል ጥያቄ ማቅረብ ጀመርን::

በንጉሡ ጊዜ በነበረው የለውጥ እንቅስቃሴ፣ የአየር ኃይል ፓይለቶችና ቴክኒሺያኖች፤ የተማሪዎችንና የአርሶ አደሩን አመፅ ሲደግፉ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል:: በኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጊዜም ቢሆን በርካታ የአየር ኃይል አባላትና አዛዦች ጭምር፤ እነ ጄኔራል ፋንታ በላይ፣ ጄኔራል አምኃ ደስታና ሌሎችም ከሕዝብ ጎን በመቆም፣ 'ከዚህ በላይ አምባገነን መሆን አትችልም' በሚል አየር ኃይሉ አጋርነቱን አሣይቷል::

ህወሓት ወደሥልጣን ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ የአማራን ሕዝብ እንደ ጠላት እያየ፣ እየተሳደበ፤ ብሔር ተኮር ግጭቶችን ሲቀሰቅስ ነው የኖረው:: ሥርአቱን እየከዱ፤ በካናዳ፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በሌሎች የዓለም ሀገራት ተሰደው ለመቅረት የተገደዱ የአየር ኃይል ባልደረቦች በርካታ ናቸው:: አንዳንዶች ከአየር ኃይል አባልነት ከድተው የትጥቅ ትግሉን በመቀላቀል ኤርትራ በረሃ ለመግባት ተገደው ተመልክተናል::

ህወሓት በኢህአዴግ ውስጥም ሆነ በሕዝብ ላይ የበላይነቱን ይዞ መቆየት እንጂ፣ ለሀገርና ለሕዝብ መጨነቅ ጉዳዩ ስላልነበረ፤ እስካሁን ድረስ በዚያ መንገድ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል:: ደህንነት፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ መከላከያና አጠቃላይ መንግሥታዊ ተቋማት ደግሞ፤ ይሄን ህልሙን እውን አድርገውለታል:: የኢኮኖሚና የፖለቲካ ራዕዩንና የበላይነቱን እውን ካደረጉለት ተቋማት አንዱ፤ እኔ ያለሁበት አየር ኃይል በመሆኑ፣ ይህንን ነገር የሚፃረሩ ጥያቄዎችን በተደጋጋሚ ማንሣቴ ዓይን ውስጥ እንድገባ አድርጎኛል::

**ግዮን፡- ከአየር ኃይል ይህንን መሰሉ ጭቆናን የማውገዝ ጥያቄ፤ በአንተ ብቻ ነበር የሚቀርበው?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** እኔ ብቻ አይደለሁም:: መቶ አለቃ ዳንኤል ግርማ፣ መቶ አለቃ ገዛኸኝ ድረስ በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል በመቃወም በተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ያቀርቡ ነበር:: እኔ ባነሣሁት የሕዝብ መብት ጥያቄ የተነሣ ለስድስት ወር ያህል ከማዕረግ እንድለይ ተደርጌያለሁ::

ከዚያ በኋላ በተለያዩ አልሸባብን የመደምሰስ ሚሽኖች ላይ ተሳትፌያለሁ:: በ2007 ዓ.ም አሸባሪውን አልሸባብን የማጥፋት ሚሽን ላይ የበኩሌን ተወጥቼ ስመለስ ነው 'አሸባሪ' ብለው የያዙኝና ያሰሩኝ::

**ግዮን፡- የት ነው የያዙህ?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ታኅሣሥ 17/2007 ዓ.ም ድሬዳዋ ሥራ ላይ ነበርሁ፤ በማግስቱ ቀደም ሲል የጠቀስኩልህን ሰዎች ጨምሮ፤ መቶ አለቃ ብሩክ አጥናፉና እኔ ወደ ባህር ዳር ሄደን፤ ወደ ከተማው እየገባን ነው የያዙን:: ከእነሱ ለይተው ወደ ጫካ ወስደው ራሴን እስክስት ድረስ ክፉኛ ደብድበውኛል:: ለሁለት ወራት ያህል የት እንደሆን የማላውቀው በጣም ቀዝቃዛ ቤት፣ የደህንነት ቢሮ አስረውኛል:: በጣም ከባድ ቦታ ነው::

**ግዮን፡- ደህንነት ቢሮ ሁለት ወር ከታሰርህ በኋላ ወዴት ተወሰድህ?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ሁለት ወር ከታሰርሁ በኋላ፤ ወደ መከላከያ ካምፕ ወሰዱኝ:: እዚያ አንዱ 'መርማሪ ነኝ' ብሎ መጀመሪያ ላይ ቃል ተቀበለኝ፣ መጨረሻ ሌላ መርማሪ ተለወጠና የመጀመሪያው ዳኛ ሆኖ፤ ጋዋን ለብሶ ተቀመጠ:: ታጠቅ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ይመስለኛል፤ በጣም አስቂኝ ገጠመኝ ነው:: በራሴ ላይ የደረሰ ባይሆን ኖሮ እኔም ለማመን ይከብደኝ ነበር:: መጀመሪያ 'መርማሪ ነኝ' ብሎ ቃል የተቀበለኝ

ሰው፣ በኋላ፣ 'ዳኛ ነኝ' ብሎ ሲቀርብ እስኪ አስበው::

ይህን ነገር እኔ ስናገረው ራሴ አፍራለሁ:: ሕዝብ ለታሪክነቱ እንዲረዳው ብዬ ነው እንጂ፣ እኔ በምንም መልኩ ቢሆን ሐቅን ተመርኩዤ ከመታገል ወደኋላ አልልም:: ምንም ዓይነት ፍርኃት የለብኝም፣ ብኖርም ባልኖርም የሚቀርብኝ ነገር የለም፣ ብዙ መከራዎችን ዐይቻለሁና:: በሰዓቱ ይሄን ድራማ ሲሠሩብኝ እኔ ቃል ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆንኩም::

**ግዮን፡- ምን ነበር የሚሉህ?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** አንድ የጦር አውሮፕላን፣ ኤርትራ በገባች በሳምንቱ ነበር እኛ የተያዝነው፣ ከዚህ በመነሣት፣ 'አውሮፕላኗን ከአብራሪው ኤርትራ የላክሃት አንተ ነህ' የሚል ውንጀላ ነው ያቀረቡብኝ:: ይሄ መርማሪም፣ ዳኛም የሆነው ሰውዬ፣ ዐሥራ አራት ቀን ቀጠሮ በመከላከያ የጦር ፍ/ቤት ከሰጠብኝ በኋላ ነው ወደ አዲስ አበባ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ የመጣሁት:: ማዕከላዊ፣ በቀጥታ ጨለማ ቤት ውስጥ ነው ያስገቡኝ::

እኔን ሲመረምረኝ የነበረው፣ የፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉ ዳይሬክተር ኮማንደር ተክላይ ብቻ ነው:: ማንነቴን ተመርኩዞ ጸያፍ ስድብ ይሰድበኝ ነበር፣ 'ይቅርታ በል' ብሎኝ እምቢ ስለው ምራቁን ተፍቶብኛል:: የመነጋገሪያ ማይክ ወርውሮ መቶኛል:: በተደጋጋሚ፣ ብዙ ጫናዎች ያደርግብኝ ነበር:: መጨረሻ ላይ ሌላ አንድ ጽጋቡ የሚባል መርማሪ ቃል ጽፎ አስፈርሞኛል:: ከቤተሰብም ሆነ ከማንም ሰው ጋር አልገናኘም ነበር::

**ግዮን፡- በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶብህ ወደ ቂሊንጦ የወረድህበትና አጠቃላይ የፍትሕ ሥርዓቱ ምን ይመስላል?**



***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ክሱ፣ ቀደም ብዬ በጠቀስሁት መንገድ፣ 'ከግንቦት ሠባት አመራሮች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣ ለኩብለላ ተዘጋጅቷል' የሚል ነው፣ በመከላከያ ሕግ፣ አንድ የጦር አባል፣ ሃያ አንድ ቀን በራሱ ፈቃድ ከሥራው የቀረ ከሆነ ነው በኩብለላ የሚያስጠይቀው፣ እኔ ግን፣ ትናንት ሥራ ላይ ሆኜ ዛሬ ነው የተያዝኩት ማለት ይቻላል:: ሦስተኛ፡- መንግሥት ለራሳችን ያስታጠቀን ሽጉጥ አለ፣ እሱን 'ሽጣችሁታል' በሚል ነው ክስ የተመሰረተው::

የፍርድ ሂደቱ በጣም ያሳዝናል:: ሰሞኑን 'የፍትሕ ሳምንት ይከበራል' ሲባል እየሰማሁ ነው፣ እውነት ለመናገር፣ 'የፍትሕ የሙት ሳምንት' ከሆነ የሚከበረው እስማማለሁ:: በዚህች ሀገር ላይ 'ፍትሕ ጉድጓድ ውስጥ ተቀብሯል' ማለት ይቻላል:: ፍርድ ቤት የሚቀመጡት ዳኞች ሙያዊ ነፃነት የላቸውም፣ በተለይ ለፖለቲካ ነክ የሚመደቡት ዳኞች ራሳቸው ዳኛ መሆናቸው ያጠራጥራል:: ምንም ነገር ከሕግ አግባብ አይመለከቱም:: እኔ በሰዓቱ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ደርሶብኝ አቤቱታ ሳቀርብ ሊሰሙኝ ፈቃደኛ አልነበሩም:: 'ዳኛ ቅብ' የሆኑ የዳኛና የፍትሕን ስም የሚያጎድፉ ሰዎችን ችሎት አስቀምጠው አልቅሰን የወጣንበት ቦታ ፍርድ ቤት ነው::

**ግዮን፡- መጀመሪያ አብረውህ የተያዙት የአየር ኃይል አብራሪዎችም በክሱ ውስጥ ገብተው ነበር?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** መከራና ግፉን አብረን ነው የተቀበልነው:: የጠቀስኩልህን ሦስት ጓደኞቼን ጨምሮ፣ አራት ሰዎችና ሌሎች ሁለት ምንም የማያውቁ ሰዎች በአባሪነት በክሱ ተካትተዋል:: ሻለቃ አክሊሉ ግርማ የሚባል ከሀገር የወጣ ሰው፣ እሱን ለመበቀል ወንድሙን አሸባሪ አድርገው ሲከሱት፣ ወንድሜ የእኔ ሽጉጥ እሱ ጋር ስለነበር እሷን በማየት የሽብር ክስ ተመስርቶበታል፣ ተስፋዬ እሸቴ ይባላል::

ስድስታችን ላይም የሐሰት ምስክር ተፈልጎ ነው የተመሰከረብን:: እኔ ላይ ከመሰከሩት ሰዎች አንደኛው፣ 'ወደ ኤርትራ ሄዶ ግንቦት ሠባትን ሊቀላቀል ሲል ያዝሁት' ሲል፣ አንደኛው ደግሞ፣ 'ወደአውሮፓ ሊሄድ ሲል ሰማሁ' የሚል፣ እርስ በርሱ የሚጋጭ ምስክርነት ነው የሰጡት:: በዚህ ተከላከል ተባልሁ:: በፍርድ ቤቱ እምነት ስለሌለኝ፣ ሞትም ቢሆን፣ ዕድሜ ልክም ቢፈረድብኝ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚመጣውን ነገር ከመቀበል ውጪ አማራጭ ስላልነበረኝ፣ እኔም ሆንሁ ሌሎች ጓደኞቼ ክሱን መከላከል አልፈለግንም:: በዚህ የተነሣ በሐሰተኛ ምስክር ዐሥር፣ ዐሥር ዓመት ተፈርዶብናል::

**ግዮን፡- ብዙዎችን ያሳዘነውን የቂሊንጦ እሳት ቃጠሎን ወደአንተ የማላከኩንና ተጠያቂ የማድረጉን ጉዳይ፣ ዛሬ እውነታውን ከአንደበትህ የምንሰማበት ጊዜ ላይ እንገኛለንና ምን ትለናለህ?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** የቂሊንጦ እሳት ቃጠሎ የተነሣው በህወሓት ሤራ ነው:: ርካሽ የሆነና የተለመደ አውሬነታቸውን የሚያሳይ፣ ከዚህ በፊት ያደረጉት ነገር መሆኑ ይታወቃል:: 1998 ዓ.ም ላይ ሁላችሁም እንደምታውቁት የአዲስ አበባ ልጆችን በግፍ ጨፍጭፈዋል:: ቃሊቲ ዞን ስድስት ላይ ስታዲየም ሠርተውበታል:: ከዚያ ሥር እህትና ወንድሞቻችን ተቀብረው ይገኛሉ፣ ተጠያቂነት ቢኖር ያ ነገር እውን የሚሆን ይመስለኛል::

የሚገርመው እኔ ከዞን ወጥቼ፣ እነ አቶ በቀለ ገርባ ጋር ከነበሩ የፖለቲካ እስረኞች ጋር ወደ ከፍተኛ ጥበቃ የተዛወርሁት ቃጠሎው ከመከሰቱ ከአራት ወራት በፊት ነው:: ከፍተኛ ጥበቃ በነበርሁበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤት ስሄድ እንኳን በፒክ አፕ ታጅቤ ከአባሪዎች ጋር መገናኘት በማልችልበት ሁኔታ ነው::

በወቅቱ፣ የቂሊንጦን እሳት ቃጠሎ ያስነሣው፣ የታጋይ ልጅ ነው:: ቃል ሰጥቷል፣ ፈርሟል:: ሐቁ ይሄ ነው:: ዓለም አቀፍ ወንጀል ስለሆነና መንግሥትን ከተጠያቂነት ለማራቅ ሲባል፣ ሌላ ሰው መሥዋዕት ማድረግ ነበረባቸው:: በዚህ የተነሣ፣ ድራማውን እነሱ በሚፈልጉትና በሚጠሉት መንገድ ጻፉት፣ በተለይም የአማራ ልጆችን ሆን ብሎ ለማጥቃት:: እኔን የአደጋው ቡድን አደራጅ፣ ዶክተር ፍቅሩ ማሩን የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ በማድረግ፣ ለእኔ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር እንደሰጡ ተደርጎ ተከሰስን:: ሌሎች የጎንደርና የአዲስ አበባ ልጆች፣ ማነታቸው እየተጣራ፣ አማራ፣ ኦሮሞና ደቡብ ሆነው ሲገኙ በክሱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጎ የሐሰት ምስክር ቀርቦብናል::

**ግዮን፡- የቂሊንጦ ቃጠሎን ተከትሎ፣ እናንተ ከተወነጀላችሁ በኋላ፣ ምርመራው ዘግናኝ እንደነበር፣ አግባው ሰጠኝ የመጽሔታችን እንግዳ በነበረበት ወቅት ገልፆልናል:: አንተ ላይ የተደረገው ምን ነበር?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ሸዋ ሮቢት ተወስደን ዘግናኝ ድብደባ ተፈፅሞብናል:: እኔን ጣሪያ ላይ ሰቅለው ሲያሰቃዩኝ ከቆዩ በኋላ፣ 'ገመዱ ተበጠሰብን' በሚል ውሸት፣ መሬት ላይ ጥለው ወገቤን ለከፋ ጉዳት ዳርገውታል:: ዓይኔን በወታደር ጫማ ረግጠውኛል:: እግራችን ተላልጦ መሄድ እስከሚያቅተን ድረስ ገርፈውናል:: ደብድበውናል:: ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ነበር::

የሚገርመው ነገር፣ በእሳት ቃጠሎው ጊዜ እኔንና አቶ በቀለ ገርባን የመግደል ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር:: በሰዓቱ የልዩ ጥበቃና ደህንነት ሓላፊውን፣ ጠባቂ ወታደሮች፣ 'አትገባም' ብለው በመከልከላቸው ነው:: ይሄን ደግሞ በአደባባይ ህዘብ በተሰበሰበት ጋዜጠኞችና ታዛቢዎች ባሉበት፣ እሳቸው፣ 'በሩን ለመክፈት ነው የሄድሁት' ቢሉም፣ ለመግደል ሲመጡ ከወታደሮቹ ጋር አለመግባባት ተፈጥሮ ወታደሮቹ 'አናስገባም' በማለታቸው ተርፈናል::

ሸዋ ሮቢት ከወሰዱኝ በኋላ፣ መጀመሪያ ጫካ ውስጥ አስገብተው፣ 'እስር ቤት አቃጥለሃል፣ ሰው ገድለሃል፣ ይሄንን እመን' እያሉ ሊያስፈራሩኝ ሞክረው ነበር:: ከዚያ በኋላ ነው ድብደባ የተጀመረው:: የራሳቸውን ጥፋት፣ በእኛ ላይ ለማዞር፣ ሰብስበው በወሰዱን ወደ መቶ ሃምሳ የምንጠጋ ሰዎች ላይ ግፍ ተፈፅሞብናል:: በደረሰብኝ ድብደባ ዓይኔ በመጎዳቱ፣ ረዥም ጊዜ ማየት አልችልም ነበር፣ አሁንም በመነጽር እየታገዝኩ ነው የማየው::

**ግዮን፡- አሁን ጤናህ በምን ሁኔታ ላይ ነው ያለው?**


***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** ስንፈታ ያገኘሁት የሕዝብ ስሜትና ተቀባይነት፣ ብዙ መከራዎቼን አስረስቶኛል:: የሕይወት መሥዋዕትነት ብከፍልም አይቆጨኝም:: የሕዝቡን ስሜት በዚህ ደረጃ አገኛለሁ ብዬ አልጠበቅሁም:: ወገቤ ላይ ያለውን በሽታ እየታከምሁት ነው፣ ባህር ዳር ላይ ጀምሬያለሁ:: ዓይኔንም እንደዚሁ እየታከምሁ ነው:: ህዝብ በፍቅር እያሳከመኝ ነው::

**ግዮን፡- አፈታትህ እንዴት ነበር?**

***መቶ አለቃ ማስረሻ፡-*** እኔ የተፈታሁት እግዚአብሔር በፈቀደ ቀን ነው:: ሲቀጥል ግን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግፊትና ጥያቄ ነው ያስፈታኝ:: ምንም የፈረምሁበት ነገር የለም:: መጀመሪያ ላይ፣ ሁለትና ሦስት ጊዜ፣ ቂሊንጦ ድረስ ከመከላከያ መጥተው፣ 'እንፍታችሁ፣ ይቅርታ በሉ' ስንባል፣ እኛ እምቢ አልን:: ሌሎች እሺ ያሉትን ስድስት ሰዎችን ይዘው ወጥተዋል:: 'ሕዝብ ዋጋ እየከፈለ፣ እየሞተ ይቅርታ አልልም' በማለቴ ተስፋ የጣልሁበት ሕዝብ ነፃ አድርጎኛል:: ይሄ ሁሌም አብሮኝ የሚኖር ዕዳ አቋሜ ነው::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**





ከፍቅሩ ኪዳኔ

# የመስኮብ ዓለም ዋንጫ ውድድር

ጥንት ልጆች ሆነን ፒያሣ ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት የሚያመራው መንገድ ላይ የመስኮብ ማስታወቂያ ቢሮ ነበር:: ከውጭ ግድግዳው ላይ የፕሮፓጋንዳ ፎቶዎች ይለጠፉ ስለነበር በዚያ በኩል ስናልፍ የነ ሌኒን ስታሊን ጺም ማየታችን አይቀርም:: የኮሚኒስቱ አገር የሶቪየት ሕብረት ወይም ራሺያ ቢባም ለኛ ለተራው ኢትዮጵያዊ መስኮን ሆኖ ቀርቷል::

በግሩም ሁኔታ የዓለም ዋንጫ የእግር ኳስ ውድድርን 9.2 ቢሊየን ዶላር በማፍሰስ በማዘጋጀትም በሁሉም የተደነቀችው መስኮብ በቭላድሚር ፑቲን ቁጥጥር ስር ያለች አገር ናት:: ዕድሜ ለቴሌቭዥን ኩባንያዎች ግጥምያዎቹን ለማሰራጨት በሚከፍሉት ኪራይና ማስታወቂያ በማስተላለፍ የሚገኘው ገቢ በጣም ከፍ ያለ ነው:: ፊፋ ለ32ቱ ተወዳዳሪዎች የሚያከፋፍለው 334 ሚሊዮን ዩሮ ነው:: ለውድድሩ የታጨት ቡድኖች ለዝግጅታቸው 1.25 ሚሊዮን ዩሮ ይሰጣቸዋል:: ከዚያም በአንደኛው ዙር ውስጥ ተሸንፎ ለሚሰናበተው 6.7 ሚሊዮን ዩሮ ይደርሰዋል:: ቀጥሎም ለፍፃሜ ሩብ የደረሱት 13.4 ሚሊዮን ዩሮ ያገኛሉ:: ከፍፃሜ ግማሽ የደረሱት አራት ቡድኖች ድርሻቸው እንደሚከተለው ነው:: አራተኛ የሆነው 18 ሚሊዮን ዩሮ፤ ሶስተኛው 20 ሚሊዮን ዩሮ፤ ሁለተኛው 23 ሚሊዮን ዩሮ፤ አንደኛው 32 ሚሊየን ዩሮ ይከፋፈላሉ::

በተጨማሪም በዓለም ዋንጫ ውድድር ተጫዋች ያሰለፉ ክለቦች በሙሉ በቀን 7305 ዩሮ በፊፋ ይከፈላቸዋል:: በዚህ መሠረት ማንቼስተር ሲቲ 4.4 ሚሊዮን ዩሮ፤ ሪያል ማድሪድ 4.3 ሚሊዮን ዩሮ፤ ቼልሲ 4.0 ሚሊዮን ዩሮ ገቢ አስመዝግበዋል:: የዓለም ዋንጫን ያሸነፈው የፈረንሳይ ቡድን ተጫዋቾች 9.6 ሚሊዮን ዩሮ እንደሚከፋፈሉ ታውቋል:: እያንዳንዱ ተጫዋች ቢያንስ 40 ሺ ዩሮ ይደርሰዋል:: ተጫዋቾቹ በጣም ሀብታም ስለሆኑ ድርሻቸውን ለበጎ አድራጎት ድርጅትና ላሰለጠኑዋቸው የቀበሌ ክለቦች እንደሚሰጡ አስታውቀዋል:: ፌደሬሽኑም ከወጪ ያተረፈውን ለአማተር ክለቦችና ለፉትቦል አካዳሚዎች ይመድባል:: ፈረንሳይ ካሰለፈቻቸው 23 ተጫዋቾች ውስጥ አስራ አራቱ ከአፍሪካ ናቸው:: በዚህም የተነሳ የተነሳ የአፍሪካ ቡድን ነው በማለት የዘር ጥላቻ የሚያሳዩ አልጠፉም::

ለጥቁር ጥቁር ብራዚል፣ ቤልገርክ፣ እንግሊዝ፣ ኮሎምቢያ፣ ስዊድን፣ ዴንማርክ ቡድኖችም ውስጥም አሉ:: ፈረንሳይ ያሰለፈቻቸው ጥቁሮች በሙሉ ከድሃ አፍሪካዊ ቤተሰብ የተወለዱ፤ ከፓሪስ ከተማ ውጭ ባሉት የመንደር ክለቦች ውስጥ ታንፀው ያደጉ፤ እዚሁ የተወለዱ ፈረንሳዮች ናቸው:: በዚህም ምክንያት የፈረንሳይ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ኤማኑኤል ማክሮን እነኚህን የብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ያፈሩትን ክለቦች ፕሬዝዳንቶች ጋብዘው ወደ መስኮብ ይዘዋቸው ከመሄዳቸው ሌላ ወጣቶቹን ተጫዋቾች ቤተ መንግስት ጋብዘው አስተናግደዋል:: ከእነርሱም መካከል የ13 ዓመቱ ወጣት ኢትዮጵያዊ ብሩክ ሲሳይ ይገኛል:: መስኮብ ከነበሩት አሰልጣኞች ያለ አፍሪካዊያኖቹ በስተቀር (የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝ እንዳይሰማ) ሌሎቹ ከ20 የማያንሱ ረዳቶች ነበሯቸው:: ለምሳሌ የቤልገርኩ አሰልጣኝ ማርቲኔዝ ሰላሣ ረዳት፤ ፈረንሳይ ሃያ ረዳት ነበራቸው:: የዓለም ዋንጫን በተጫዋችነትና በአሰልጣኝነት ያገኙ እስካሁን ሁለት ነበሩ:: ማሪዮ ዛጋሎ ከብራዚል እና ፍራንዝ ቤከንባዎር ከጀርመን:: አሁን ዲዲዬ ዴሻ ከፈንረንሳይ ተደምሯል::

በፍፃሜው ጨዋታ የተካፈለችው ክሮሺያ በአጨዋወት ቴክኒክዋ ተመስግናለች:: ያገሪቱ የሚኒስትሮች ካቢኔ ከጠ/ሚኒስትሩ አንስቶ ሁሉም በዓለም ዋንጫ ውድድር ሰሞን የሚሰባሰቡት የቡድኑን ሹራብ ለብሰው ነበር:: ያገሪቱም ፕሬዝዳንት ስታዲየም የሚመጡት የቡድኑን ጥብቆ አጥልቀው ነበር:: በመስኮብ ዝግጅት ሁሉም የተደነቀው አስራ ሁለቱም ስታዲየሞች እስከ መጨረሻው ቀን ጢቅ ብሎ በመሞላቱና ምንም ዓይነት አደጋ ባለ መድረሱ ነው:: ሕዝቡም በጣም ጨዋ ሆኖ ነው እንግዶቹን ያስተናገደው:: የስታዲየም መግቢያ ቲኬት ዋጋ ከ1450 ዶላር አንስቶ 1100፣ 875፣ 750፣ 550 እና 420 ዶላር ነው የተሸጠው::

በጠቅላላው የዓለም ዋንጫ ውድድር ለመከታተል የመጡት ሁሉ በአንድ ወር ውስጥ 1.3 ቢሊዮን ዶላር መርጨታቸው ተረጋግጧል:: ወጪው ለሆቴል፣ ለምግብ፣ ለትራንስፖርት፣ ሽቀጣሽቀጥና ቢራ መሸመቺያ ነበር:: ከጥንት ጀምሮ ባልና ሚስት የሚያኮራርፈው ወጪ ይሄ ነው::

አምስቱም የአፍሪካ ቡድኖች ምንም እንኳ በመጀመሪያ ዙር ቢወጡም ጥሩ ተጫውተዋል:: በመጨረሻ ደቂቃ ዕድለ ቢስ በመሆን ባንዳንድ ስህተት የተነሳ ቢረቱም እስከዚህ የሚያሳፍር አይደለም:: ከነርሱ የወጡ የዓለም ሻምፒዮኖቹ እነ ጀርመን፣ ስፔን፣ አርጀንቲና አሉ አይደል? ይልቁንም የግብፅ ፓርላማ ቡድናቸው በሳውዲ አረቢያ ስለተሸነፈ ትልቅ ውርደት ተሰምቷቸው ምክንያቱን የሚያጣራ ኮሚቴ አቋቁመዋል:: ግብፅ ከማን አንሼ በሚል ስሜት ኳታር እ.ኤ.አ በ2022 የዓለም ዋንጫ ስለምታዘጋጅ እኛም በ2030 ለማዘጋጀት እጩ ሆነን እንቀርባለን ብላለች:: የሳውዲ አራቢያ አልጋ ወራሽ ደግሞ የዓለም የክለቦች ዋንጫ ለማዘጋጀት ከፊፋ ጋር እየተደራደረ ነው:: ዳሩ ግን የአውሮፓ ክለቦች በሃሳቡ አልተስማሙም:: ለማንኛውም የኳታርን ዝግጅት ለማሰናከል ጠላቶቿም ወደ ኋላ አይሉም:: እስራኤልም ተቃራኒ ሆና ተሰልፋለች:: ፉትቦልና ፖለቲካ ሁሌም እንደተጠቃቀቡ ነው:: የሐይቲ ሕዝብ የብራዚል ቡድን ደጋፊ መሆኑን የሚያውቀው መንግስት የቤንዚን ዋጋ ጭማሪውን ብራዚልና ቤልገርክ የተጫወቱለት አወጀ:: ዒላማው ብራዚል ካሸነፈ ሕዝቡ ጭማሬውን በሰላም ይቀበላል ነበር:: ነገር ግን ብራዚል ስለተሸነፈ ሕዝቡ ከተማውን በንዴት አቃጠለው:: የሚኒስትሮቹም ካቢኔ ተሰናበተ:: በቻይና ደግሞ በዓለም ዋንጫ ውድድር ላይ 330 ሺ በኢንተርኔት ቁማር በመጫወት አንድ ቢሊየን ዩሮ ከእጅ ወደ እጅ ተዛውሯል:: 540 የሚሆኑትም ቁማርተኞች ተይዘዋል::

በመጨረሻም አፍሪካ ውስጥ ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰማ የለም እንጂ ወጣቶቹን ከልጅነታቸው እስከ ጉርምስና ዕድሜያቸው ድረስ በፈለጉት ስፖርት ዓይነት ትምህርት አግኝተው እንዲያድጉ ዕድል ካልተሰጣቸው ጭራሽ መሻሻል አይኖርም:: የትምህርት ቤቶች ስፖርት ውድድርና ፌደሬሽን ዕድሜያቸው ከ17 እና 20 በታች ለሆኑት የሚያዘጋጁት ካልተጠናከረ ጥሩ ጥሩ ስፖርተኞች ለማፍራት አይቻልም:: የኢትዮጵያና የአፍሪካ መከራው የሰፈር ልጆች የሚጫወቱበት ቦታ የለም:: የቀራቸው ባቡር መንገድ ብዙ ነው:: ታዲያ የትኛው ሜዳ ላይ ተለማምዶ ነው ለዓለም ዋንጫ የሚዘጋጁት ::

ዓብይ ያውቃል! የፍፃሜውን ግጥሚያ ለማየት ግን የጋቦኑ መሪ አሊ ቦንጎ፤ የጊኒ ኢኳቶሪያል ም/ፕሬዝዳንት ቴዎዶረን ንጌማ ኦቢያንግ፤ የሳዎቶሜ ኢ ፕሪንቺፔ፣ ጠ/ሚኒስትር ፓትሪስ ትሮቮአን የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ኦማር አልበሽር በመንግስቶቻቸው ወጪ መጥተው ነበር:: ኬኒያ ግን የመጣው ይምጣ በማለት 20 የፓርላማ አባሎች ሙሉ ወጪያቸውን መንግስት ችሎ የዓለም ዋንጫን ዝግጅት እንዲመለከቱ መጥተው ፀሀይ ሲሞቁ ከርመው ተመልሰዋል:: በመቀለድማ አፍሪካን ማን ይስተካከላል



አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ

# በመደመር ዘመን የመቀነስ ፖለቲካ -2-

***ባለፈው ሳምንት ዕትም፣ "በመደመር ዘመን የመቀነስ ፖለቲካ" በሚል ርዕስ፤ የተወሰኑ ነጥቦች መነሣታቸው ይታወሳል፡፡ በዚህ የመቋጫ ጽሑፍም ወሳኝ የሆኑ ነጥቦች በዝርዝር ተዳስሰዋል፡፡***

## ለውጡን የመፈረጅ - የሴራ መላምት

ጠ/ሚ ዐቢይ ወደመንበረ ሥልጣን መምጣታቸውን ተከትሎ የተቻላቸውን ሁሉ ካደረጉት የትህነግ ደጋፊዎች፤ ለቁጥር የሚታክቱ የሤራ መላምቶች በስፋት እየተሰነዘሩ ነው:: ከማህበራዊ ሚዲያው ጀምሮ ከአይጋ ፎረም እስከ ትግራይ ኦንላየን እጅግ አስገራሚ የሆኑ የሴራ መላምት (conspiracy theory) ጋጋታ ማዝነባቸውን አላቆሙም:: ከጋሽ አበራ ሞላ እስከ ገጣሚ ሜሮን ጌትነት፤ ከኮሜዲያን ክበበው ገዳ እስከግጥምን በጃዝ ምሽቶች ያሉት በቀለም አብዮት አራማጅነት፤ በአይጋ ፎረም ጸሐፊ መፈረጃቸው ዓይነተኛ ማሳያ ነው::

"የቀለም አብዮት መደመር ህዝበኝነት" በሚል በሰላም ወርቅ ሁሉ አገር የቀረበው የፍረጃ ፕሮፓጋንዳ፤ የመደመር ጉዞው (ለውጡ) በብዙ የቀለም አብዮት ሠራዊት ተሳትፎ፣ በረዥምም ጊዜ ጥናት፤ በተለይም በሲአይኤ በተቀነባበረ አብዮት ስለመሆኑ በስፋት ያትትና፣ "ወደድነውም ጠላነውም፤ ማወቅ ያለብን እውነታ፣ ጋሼ አበራ ሞላ ገና ከመጀመርያው አዲስ አበባን አፀዳለሁ ብሎ፤ ከውጭ መጥቶ፤ ወጣቶችን እየሰበሰበ ፅዳት ሠርተዋል ብሎ ብር መክፈል ሲጀምር መጥረጊያ ብቻ ይዞ አልመጣም:: በአንዳንድ ሀገሮች ኮሜዲያን የቀለም አብዮቱን መሣሪያ አድርገው ሲጠቀሙባቸው እናያለን:: በኛም ሀገር አብዛኛዎቹ የሞያ ሰዎች ሲሆኑ፤ እንደ ክበበው ገዳና መስከረም የተባሉ በግላጭ ዋናውን የአብዮቱ ኮር ሐሳብ በማስረፅ የራሳቸው ሚና ነበራቸው:: ሌሎቹ፣ አሜሪካ ደርሰው ክትባቱን ወስደው ከተመለሱ በኋላ ጨዋታ የጨመሩ ሦስት ኮሜዲያንንም ብዙዎቻችን የታዘብናቸው ይመስለኛል" ይላል:: በመቀጠልም፣ "ከአርቱ ሳንወጣ ፊልሞች፣ ግጥሞች፣ መነባንቦችና በጥቂቱም ቢሆን የስእል ሥራዎች፤ የቀለም አብዮት ማስፈፀሚያ መሣሪያ ሆነው በሌላው ዓለም ዐይተናል፤ እኛም ሀገር እንዲሁ:: ለዚህም በቅርብ ዓመታት በርካታ የዚህ ቅኝት ያላቸው ፊልሞች ዐይተናል፤ ቁጥርና አድማጭ ተሳታፊ እያበዛ የመጣው የግጥም ምሽትና ግጥምን በጃዝ ...ወዘተ መድረኮች መብዛታቸውን ሁላችንም ታዝበናል:: ብዙም የማይደፈሩ የፖለቲካ ቅኝት ያላቸውን ነገሮች ሲነግሩን ስቀናል፤ አጨብጭበናልም:: ከዓመታት በፊት ሜሮን ጌትነት አሜሪካ ደርሳ የተመለሰች ጊዜ፤ በአንድ የግጥም መድረክ ያቀረበችውን ግጥም አስታወሳችሁ?" በማለትም የሀገሪቱ የኪነ ጥበብ ሥራዎች በሙሉ ለቀለም አብዮቱ መዋላቸውን ያወሳል:: ክሱ ግን በዚህ የሚያበቃ አልሆነም:: በተለይ ፈረንጆቹ፣ "ታላቁ ህፀፅ = grand fallacy" እንደሚሉት ዓይነት ፍረጃ ወደታች ወርዶ የመንግሥት ሚዲያውም ሆነ በፓርቲው ንብረትነት የሚታወቁት ሚዲያዎች ሳይቀሩ የቀለም አብዮት አራማጅ ስለመሆናቸው እንዲህ ይላል:: "እነ ዶ/ር ዐቢይን ወደሥልጣን ያመጣው የአዲሱ አብዮት ሚዲያ ለረጅም ጊዜ ታስቦበት በስፋት የተሠራበት ነው:: ይህ ሲባል የመንግሥትን ሚዲያ ጨምሮ በሀገር ውስጥ ያሉ ሚዲያዎችም ለቀለም አብዮቱ ጉዞ መሳለጥ የበኩላቸውን በመወጣት ረገድ ብዙም እንዳልሰነፉ ከዚህ በፊት በነበሩት ጽሑፎቼ የገለፅኹት ስለሆነ ለዛሬ ብዙ አልልም:: 'ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት' ለኔ በሚዛናዊነትና በሀገር ግንባታ ተወዳዳሪ ያጣ ሚዲያ የነበረ ሲሆን፤ የአብዮቱ ጊዜ እየደረሰ ሲሄድ፣ ለኔና ለአንዳንድ የተቋሙ ጋዜጠኞችም ጭምር በሚገርም ሁኔታ ልክ እንደ መሪ ቃሉ በደቂቃዎች ፍጥነት የዚህ አብዮት ማከናወኛ መሣርያ ሆኖ እየቀጠለ የሚገኝ መሆኑ ነው:: ሌሎች ከመንግሥት ሚዲያ እየለቀቁ ለዚህ መሣርያ የመሆናቸውን ነገርም በተግባር እያየነው የከረምን ይመስለኛል:: እዚህ ላይ ሳልጠቅሰው የማላልፈው የአለምነህ ዋሴ ጉዳይ ነው:: ከሚሠራበት ተቋም የለቀቀበትና ወደ ውጭ ሀገር ወጥቶ ግልፅ የሚባል የቀለም አብዮት የማራመድ ሥራ ሲሠራ ሳይ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ በራሱ የጊዜ ሰሌዳ ይንቀሳቀስ የነበረ መሆኑ ነው የገባኝ" በማለት በቀለም አብዮቱ ያልተሳተፈ ሚዲያ እንደሌለ ያትታል:: የዚህ ዓይነቱ ፍረጃ በተለይ ከቀድሞው ጠ/ሚኒስትር አንሥቶ እስከተራው ካድሬ ሳይቀር ተቃዋሚዎችን ለማሸማቀቅ ሲጠቀሙበት የቆየ ነው:: ይሄኛውን ግን የተለየ የሚያደርገው የሀገሪቱን ጠ/ሚኒስትር፣ የቀለም አብዮት ያመጣቸው አድርጎ መፈረጁ ነው:: ይህ ዓይነቱ የጅምላ ፍረጃ፤ ከምንም በላይ የትህነግ ደጋፊዎች ያሉበትን ቀቢፀ ተስፋ ከማሳየት የዘለለ ትርጉም አይኖረውም:: ነገር ግን የቆሰለ አውሬ የሚያደርገውን ዓይነት ያልተጠበቀ እርምጃ ቢወሰድ ሊከተል የሚችለውን ቀውስ በመገንዘብ በመንግሥት በኩል ተገቢውን ማብራሪያ ከትህነግ፤ አልያም ከዚህ ሐሳብ በስተጀርባ ያሉትን ሰዎች መጠየቁ ተገቢ ነው:: ይህን የምለው የተጀመረው የይቅርታና የመደመር ዘመን ለውጥ፣ ሙሉ በሙሉ የቀለም አብዮት ተደርጎ መቅረቡ፤ በሂደት ለለውጡ ምንም ዓይነት ፍላጎትም ሆነ አዎንታዊ አመለካከት የሌላቸው ሊወስዱት ላሰቡት እርምጃ፤ ይህንኑ ውንጀላ እንደሁነኛ ምክንያት ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ዕድል በመኖሩ ነው::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ የመረጃ መረብ ደህንነት ዋና ሓላፊ፣ ሜ/ጄኔራል ተ/ብርሃን ወ/አረጋይ፤ ከድምፂ ወያነ ራዲዮ ጋር በነበራቸው ሰፊ ቃለ መጠይቅ በሀገሪቱ በታየው ለውጥ ደስተኛ አለመሆናቸውን በይፋ ከመግለፃቸውም በላይ፣ "በሥልጣን ላይ የወጣው ኃይል ከኢህአዴግ ፕሮግራም ጋር የሚገናኝ ትንሽ የኢህአዴግ ሽታ እንኳን የለውም:: ለእኔ ይህ የጠላት ኃይል ነው:: እንደጠላት ኃይል እንውሰደው" ማለታቸውን ማስታወሱ ይገባል:: በተመሳሳይ "የጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ ንጉሥ የመሆን ፍላጎት ከልብ ነው እንዴ?" በሚል ርዕስ ከፍትሕ ይንገሥ በአይጋ ፎረም የቀረበው ሌላኛው መጣጥፍ ደግሞ፣ "ከድርጅታቸው ይልቅ የራሳቸውን ሰብዕና (Personality Cult) ገንብተው እርሳቸው እንዳሉት በረዥም ጊዜ ንጉሥ ለመሆን የዳዱ ይመስላል:: ህዝቡም በጉዳዩ ላይ የመደናገር ስሜት ውስጥ ያለ ይመስላል" በማለት ለሕዝቡ ተቆርቋሪ በመምሰል የቀረበው ፕሮፓጋንዳ ይቀጥልና፣ "የጠቅላይ ሚንስትሩን ንጉሥ የመሆን ህልም የሚያሳየው ቁም ነገር ደግሞ ለመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሓላፊዎች ሹመት የሰጡበት ►

ሁኔታ ነው:: እኝህ ሰው ልክ እንደንጉሣዉያን አገዛዞች ሁሉ ሥልጣናቸውን ያለስጋት ለማስጠበቅና ለማስቀጠል በማሰብ ይመስላል ዋነኛ ተቋማት ናቸው ተብለው በሚገመቱ ቁልፍ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች ለርሳቸው ቅርብ ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን የኦህዴድ የሥራ ሓላፊዎች መድበዋል" በማለትም የለውጥ አራማጁ ፍላጎት በሂደት ንጉሥ መሆን ነው የሚልን መከራከሪያ አቅርቧል::

በትግራይ ኦን ላይየን ሦስተኛ ዲግሪ እንዳላቸው በተነገረላቸው ሞገስ አብርሃም "Neo-liberal Imperialism Creating a Fragile Ethiopian State" በሚል ርዕስ የቀረበ ተከታታይ ጽሑፍ በኒዮሊበራል ኢምፔሪያሊዝም እና በኢሳይያስ አፈ ወርቂ መሣሪያነት ኢትዮጵያ ደካማና ወደመፈራረስ የተቃረበች ሀገር እንድትሆን በደመቀ፣ በገዱ እና በጓደኞቻቸው እየተሠራ መሆኑን በስፋት በማተት፤ መለስ የቀየሰው የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት በማንኛውም የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ኃይል ሊቀለበስ እንደማይችል ይዝታል::

"ኢትዮጵያ በመበተን አፋፍ ላይ?" በሚል ርዕስ ገብረ ሥላሴ ኣርኣያ በአይጋ ፎረም ላይ "'ኢትዮጵያን ካልበተንናት፤ ለኤርትራ ህልውናም ሆነ ዘላቂ ሰላም ትልቅ ፈተና ሆና ትቀጥላለች' የሚለው የኢሳይያስ አፈ ወርቂ መንግሥት ህልም እየተሳካ ይመስላል፤ ያውም ኢትዮጵያውያንን ተጠቅሞ" በማለት የጠ/ሚኒስትሩን ሠላም የማምጣት ሐሳብ ኢትዮጵያን ለመበታተን የተወጠነ በማስመሰል ውድቅ አድርገዋል::

## የመቀነስ ፖለቲካ-የተንሸዋረሩ የመፍትሔ ሐሳቦች

አይጋ ፎረም በበኩሉ፤ አዲሱ አመራር፣ "የኦህዴድ ዝቅጠት የወለደው አዲሱ ኃይል፤ ቄሮ አደራጅቶ ወደአመፅ በማስገባት፣ 'የኦሮሞ ተወላጅ ሥልጣን እስካልያዘ ድረስ ሰላም በዚህ ሀገር አይኖርም' ብሎ በአመፅና በተጠላለፈ ኔትዎርክ ወደሥልጣን የመጣ ኃይል ነው" በማለት፤ "መደመር ለሀገራዊ መግባባት መተካት አይችልም" በሚል ርዕስ በአባዲ አባይ ባቀረበው ጽሑፍ፣ "አሁን የወጣቱን መንፈስ፣ የቀለም አብዮት በሚመስሉ መፎክሮች እያንቀሳቀሰ ያለው ኃይል፤ በ1997 ዓ.ም. ቅንጅት የተባለው ኃይል ፈጥሮት የነበረውን መንፈስ በመፍጠር ሀገር ማፍረስ ካልሆነ በስተቀር፤ አዲስ የተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚመራበት በጋራ የሚያምንበት፣ Synergy Create የሚያደርግበት፣ Collective Decision and Shared Knowledge (የህብረት ውሳኔ ሆነ የጋራ እውቀት) የለውም:: በአጠቃላይ አሁን ያለው አመራር የኢህአዴግ ብልሽት የወለደው በመሆኑ ውልደቱ እና እድገቱ የተዛባ ኃይል ነው" በማለት ካጣጣለ በኂላ፤ "ይህ አካሄድ አንድነትን ከመፍጠር ይልቅ ሀገሪቷን እንደሚበታትናት አውቀን በጊዜው ሃይ ሊባል ይገባል" ሲል ለውጡን ማስቆም እንደሚገባ ይጠይቃል::

በትግራይ ኦንላይን የኢትዮ-ኤርትራ ሠላማዊ ግንኙነት ከተጀመረ ወዲህ፤ "Egypt Induced Riots and Instability Have Changed the Political Order of Ethiopia - What is next for Egypt?" በሚል ርዕስ፣ በኤርሚያስ ኃይሉ በቀረበ ሰፊ ሐተታ፤ ልክ በርዕሱ ላይ እንደተመለከተው፤ "ግብፅ በኢትዮጵያ ረብሻና አለመረጋጋት እንዲፈጠር በማድረግ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሥርዓት ለውጣለች፤ ቀጣዩ እርምጃዋስ ምን ይሆን?" ሲል ይጠይቃል:: በተለይ ይህ መጣጥፍ፣ "ኢትዮጵያ የታላቁ ሕዳሴን ግንባታ መጀመሯን ተከትሎ፤ ግብፅ የኢትዮጵያን ውስጣዊ ድክመት በሚገባ በማጥናት፣ ታላቅ ኢትዮጵያን የማዳከሚያ ስልት (Grand Ethiopian Destabilization Strategy) በመንደፍ ሀገሪቷን በግብፅ ተላላኪዎች እንድትሞላ አድርገዋል:: ቀጣዩ ግባቸውም የግድቡን ግንባታ ማስቆም ነው:: ይህን ጥያቄ አልቀበል ቢሉ ግብፅ በተላላኪዎቿ በኩል ብጥብጥ ታስነሣለች" እያለ ይቀጥላል:: የሚገርመው ይህ ለውጥ እንዲመጣ በጸሐፊው ገለፃ መሰረት፤ ግብፅ በፕሬዚዳንት ኢሳይያስ፣ በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ በዳውድ ኢብሳ እና በኢሳት፣ በኦኤምኤን፣ በቢኤንኤን እና በመሳሰሉ ሚዲያዎች መጠቀሟን ያወሳል:: በዚህም በኢትዮጵያ የትህነግ አመራሮችን በማግለል የግብፅን መንግሥት የሚደግፍ አሰላለፍ መፍጠሩን በሰፊው በማውሳት በአጭሩ፤ "በርካቶች ከቤታቸው ወጥተው በቀሩበት፣ ቁጥራቸው ያልታወቁ አካላቸውን በገበሩበት፣ ሺዎች በስቃይና እንግልት ውስጥ አልፈው ያመጡትን የለውጥ ጅምር፤ የግብፅ መንግሥት ኢትዮጵያን ለማዳከም የወሰደው እርምጃ ነው" በማለት፤ "ይህንኑ አካሄድ ለመቀልበስም ለጠ/ሚኒስትሩ የምመክራቸው ማናቸውንም የለውጥ እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት፣ ከትህነግ (TPLF) ጋር ሠላም ማውረድ ያለባቸው መሆኑን ነው" በማለት ሐተታውን ይቀጥላል::

የመቀሌ ዩንቨርስቲ መምህሩና የአረናው አመራር አብርሃ ደስታ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የበለጠ አወዛጋቢነቱ እንደቀጠለ ሲሆን፤ "ወቅታዊው የኢትዮጵያ ፖለቲካ በህወሓት ሰበብ ተጋሩን ማዳከም ላይ ያለመ ነው:: በ'መደመር' ስም ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ ተሰብኳል:: አንድነት ሳይሆን መለያየት ተሰብኳል:: ጅብ ገለመሌ እየተባለ የተጋሩን ሞራል ለመንካት ተሞክሯል:: ተጋሩን ያገለለ ስምምነት ሊፈረም ነው:: እንዲጠቃ የተፈለገው ህወሓት ሳይሆን ትግራይ ነው:: ከሰኔ 16 በኂላ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች አንድነትን የሚያጠናክሩ ሳይሆን የሚከፋፍሉ ናቸው:: በዚህ አካሄድ ሰላም ሊሰፍን አይችልም:: በኦሮምያ ክልል አለመረጋጋት ሊኖር ይችላል:: በአማራ እና ትግራይ ክልሎች መካከል ግጭት ሊከሰት ይችላል:: ስለዚህ ተጋሩ በተቻለ መጠን ሀገራችሁ ግቡ" እስከ ማለት ደርሷል::

የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፣ "የህዝብን የለውጥ ፍላጎት ማንም አያቆመውም!" በሚል ርዕስ በቅርቡ ይፋ አድርጎት በነበረው ሳምንታዊ የመንግሥት የአቋም መግለጫ፤ "የህዝብን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ የተጀመረው ፈጣን ለውጥ ተጨባጭ ስኬቶችን ማስመዝገብ በመቻሉ አሁን ላይ ለውጡን ማንም ሊያቆመው በማይችለው ደረጃ ላይ ደርሷል:: ባለፉት ጥቂት ወራት መንግሥት ሀገራዊና ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ እየወሰዳቸው ባሉ እርምጃዎች ፈጣንና ተጨባጭ ውጤቶች በመመዝገብ ላይ ናቸው" በማለት፤ ለውጡ በህዝብ ጥያቄ መምጣቱን ያትታል:: ነገር ግን ለወትሮ "መንግሥት ያለውን ሁሉ እመኑ" እያሉ ፕሮፓጋንዳን በመንዛት የሚታወቁትና በመካሄድ ላይ ያለውን ለውጥ በፅኑ የሚቃወሙት የትህነግ ደጋፊዎች ለውጡን ከቀለም አብዮት እስከግብጽ መንግሥት፤ ከሲአይኤ እስከ ፕ/ት ኢሳይያስ በተከናወነ ኢትዮጵያን የመበታተን ሴራ ስለመሆኑ ይፈርጃሉ::

መንግሥት ስለለውጡ እንዲህ ሲል ያወሳል:: "በርካታ የሕግ ታራሚዎች በይቅርታ ከእስር ተለቀዋል፤ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ተጀምሯል፤ በትጥቅ ትግል ላይ የተሰማሩ ኃይሎችም ሰላማዊ የትግል መስመርን ተቀላቅለዋል፤ በውጭ ሀገር የነበሩ ሚዲያዎች በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ወደሀገር ቤት መመለስ ጀምረዋል፤ የዳያስፖራውም የፖለቲካ አተያይ መቀየር ጀምሯል፤ ከኤርትራ ጋር የነበረው ሞት አልባ ጦርነትም መቋጫ በማግኘት ላይ ነው::"

ይሁን እንጂ የትህነግ ደጋፊዎች ሙሉ በሙሉ ለውጡ ትህነግን ያገለለና ሆን ብሎ ትግራይን ለመጉዳት እንደተደረገ አድርገው ብቻ መሳሉን መርጠዋል:: ለዚህም ትግራይን ከመገንጠል ጨምሮ መፈንቅለ መንግሥት እንዲካሄድ ጥሪ እያደረጉ ነው:: መንግሥት በበኩሉ ለውጡን የሚቃወሙትን በተመለከተ እንዲህ ብሏል:: "እየተካሄደ ያለው ሀገራዊ ለውጥ ቀድሞ ለፈጸሙት በደልና ጥፋት ተጠያቂነትን ያስከትልብናል ወይም ቀጣይ ሕገ ወጥ የሆነውን የጥቅም ማጋበሻ መንገድ ይዘጋብናል የሚል ስጋት የፈጠረባቸው አካላት እንዳሉ መገንዘብ ተችሏል:: በመሆኑም እነዚህ ቡድኖች የህዝብን የለውጥ ፍላጎት ለማደናቀፍ እስከታችኛው እርከን በዘረጓቸው የጥፋት መረቦቻቸው በመጠቀም፤ በረቀቀና ውስብስብ በሆነ መንገድ የለውጥ ሂደቱን አቅጣጫ ለማስቀየር ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው::" ሲል ይወቅሳል:: በርግጥ በእነዚህ በጭፍን የለውጡ ተቃዋሚዎች ዙሪያ እየተወሳ ስላለው የመቀነስ እና ለውጡን በውጭ ኃይሎች የመጣ መፈንቅለ መንግሥት አድርጎ ማውሳት፤ ምን አልባት ወደፊት በትህነግ ሊወሰድ የሚችለውን እርምጃ ጠቋሚ ሊሆን መቻሉ፤ ከዚህ ቀደም ጋዜጠኞችንም ሆነ የእምነት አባቶችን ሳይቀር በግፍ ለማሰር ሲወጠን ይወሰዱ የነበሩ ስም የማጥፋት ፕሮፓጋናዳዎችንና ዶክመንተሪዎችን ማስታወሱ በቂ ነው:: የሆነው ሆኖ፣ ከዚህ ሁሉ በለውጡ እርምጃ ላይ ከሚቃጡ የጭፍን ተቃውሞዎች በተለየ፤ እንደ ክብሮም አድሐኖም ያሉት፣ በትግርኛ የሚጻፉትን መስመር የሳቱ ሐሳቦች ጭምር ወደ አማርኛ በመመለስ፤ ሕዝብን ከሕዝብ ለመለያየት የሚደረገውን ሙከራ ለማስቀየር እያደረጉ ያሉት ጥረት በተስፋ ሰጪነቱ ሊወሳ የሚገባው ነው::

ከኤርትራ ጋር ሠላማዊ ግንኙነት በተጀመረበት በዚህ ሰዓት ስለመገንጠል ማውራት የጤነኝነት ሐሳብ አይደለም:: በሌላም በኩል በአውስትራልያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ትርፉ ኪዳነማርያም፣ "ለውጡ በትግራይም ይመጣል:: ለውጡ በህወሓት ውስጥም ይመጣል:: የትግራይ ሕዝብ እየተናገረ ነው:: ለውጥ ያስፈልጋል:: እጁን መሰብሰብ ያለበት ኃይልም እጁን እንዲሰበስብ ይደረጋል የሚል ጥብቅ እምነት ነው ያለኝ::" ያሉት ነገር እውን የሚሆን ከሆነም ምን ሊከሰት እንደሚችል ወደፊት የሚታይ ይሆናል:: እስከዚያው ግን፣ "ጆና ጎልድበርግ" እንዳለው፤ መረጃ በሚመስል ፕሮፓጋንዳ ሕዝቡን በማሳሳት የቅነሳ እና ለውጡን ለማስቆም የኃይል እርምጃ መምረጡ የሚኖረው ጊዜያዊና የረዥም ጊዜ ውጤቱም የከፋ መሆኑን በመገንዘብ አሰላለፍን ማሳመር የተሻለው መንገድ ነው:: ከምንም በላይ ለውጥ የማይለውጥ ብቸኛው ሕግ መሆኑን በመረዳት ጊዜው ካለፈበት የፍረጃና ሌላውን የማጥላላት ፕሮፓጋንዳ ታቅቦ ለተሻለ ሀገር ዘመን ተሻጋሪ ሐሳብ ማቅረቡ የውዴታ ሀገራዊ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያሻል::



ብሩክ መኮንን

# የትግል አጋሮቼም ገደል ይግቡ

ከዛሬ 27 ዓመት በፊት በዚህ ሳምንት የሊቢያ አረብ ጀምሐሪያ ሪፐብሊክ ሕዝባዊ ኮንግረስ 17ኛውን ሕዝባዊ ጠቅላላ ጉባኤ በሲርቲ በማካሄድ ላይ ነበር::

የሊቢያው መሪ ኮሎኔል መአመር ሞሐመድ አቡማናየር ጋዳፊ ጠቅላላ ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት በመምራት ላይ ነበሩ:: ተሰበሳቢዎቹ ምንም ቢሰለቹ ለቀናት የቀጠለው ጉባኤ መቼ እንደሚጠናቀቅ አያውቁም::

ጋዳፊ የአሜሪካና የአውሮፓ ሀገራትን መሪዎች እየተሳደቡ የሊቢያ አብዮት ከማንም ጋር የማይደራደሩበትንና በእሳቸው የተነደፈውን ርዕዮተ ዓለም ለተሰበሳቢው በማስተማር ላይ ናቸው::

ቀናትን የፈጀው ጠቅላላ ጉባኤ በመላው ሊቢያ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ በቀጥታ እየተላለፈ ነው:: መአመር ጋዳፊ ከአጠገባቸው ካለው ጥቁር ሰሌዳ ላይ ጠመኔ ይዘው የአፍሪካን ካርታ እያሳዩ ስለ አፍሪካ አህጉር የፖለቲካ ሁኔታ መተንተናቸውን ቀጥለዋል:: በመሃሉ ጠረጴዛው ላይ ከተደረደሩት ወርቃማ ፔርሙዞች ከአንዱ ትኩስ ቡና አስቀድተው ከጠጡ በኋላ፤

“ይህንን ጠቅላላ ጉባኤ ሳላመሰግነው አላልፍም፤ ከዛሬ 20 ቀን በፊት ምሥራቅ አፍሪካ ላይ ትልቅ የፖለቲካ ድል ተመዝግቧል:: መቼም ለማለት የፈለግሁት ይገባችኋል:: ስለ መንግሥታት አወዳደቅ ልነግራችሁ ነው::

“የኢትዮጵያው መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ፀረ-አሜሪካ፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም፣ ፀረ-ቻይናዊ ነበር::

“ከእኛም ጋር ተሰልፎ ነበር፤ አብዮታዊም ነበር፤ ጥሩም ይሠራ ነበር፤ በመጨረሻ ግን ሕዝቡንና ሀገሩን ለማፍረስ ከጽዮናውያንና ከአሜሪካውያን እርዳታ ፈለገ::

“የኤርትራውያንንና የህወሓቶችንም ትግል ማሸነፍ አለብኝ አለ:: እነዚህን ሕዝቦች ማጥፋት አለብኝ ብሎ ተነሣ::

“እነዚህ ሕዝቦች የአንተ ሕዝቦች ናቸው ብንለውም አልሰማንም:: ‘ጦርነቱ መቀጠል አለበት፤ በአሁኑ ወቅት የእስራኤል ፓይለቶች አሉኝ፤ ክላስተር ቦንብም ሰጥተውኛል’ አለ::

“እኔም በበኩሌ በቀይ ባህር ሦስት ወታደራዊ ሰፈሮች ሰጥቸዋለሁ:: ‘ይህ ለእኔ የመጨረሻው ድል ነው:: እስራኤል ከጎኔ እስካለች ድረስ፤ አሜሪካም ከእኔ ጋር ከመሆኗም በላይ ደስተኛ ናት፤ እኔም ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም አቋም አይኖረኝም’ አለ:: የሌኒንን ምስል አነሣ:: ከእንግዲህ ኮሚኒስት አለመሆኑን ለማሳየት ነው ይሄን ያደረገው::

“‘የትግል አጋሮቼም ገደል ይግቡ’ አለ:: ይህንን ሲል ሊቢያንም፣ ሌሎችንም ጭምር ማለቱ ነው፤ አበቃ:: ከዚያ በኋላማ ጥጋቡን ማን ይቻለው? ‘ከአሜሪካና ከእስራኤል የጠነከረ ምን ወዳጅ ይገኛል?’ አለ:: እኛም ተው አልነው፤ ነገርነው:: እኛ ከኤርትራውያንና ከኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ አመፁን ያቀጣጠሉትን ወገኖች እንደግፋለን አልነው::”

ተሰብሳቢው ለደቂቃዎች ያለመቋረጥ አጨበጨበ::

“ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆማችንን ነገርነው፤ አንተ ደግሞ ከአሜሪካና ከእስራኤል ጋር ነህ:: ማን እንደሚያሸንፍ እንተያያለን አልነው::

“አሁን የታላቁን የኢትዮጵያ አብዮት እየመራ አዲስ አበባ ያለውን መለስን እና የኤርትራን መሪ ኢሳይያስን እንዲሁም ሌሎችን መሪዎች በሙሉ ጠርተን ያደርግነው ውይይት ለሕዝብ በቴሌቪዥን እንዲተላለፍ እፈልጋለሁ::

“መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከእስራኤልና ከአሜሪካ ጋራ ተሰልፎ እኛን ተወን:: የራሱም ሕዝብ በጠላትነት ተሰለፈበት፤ በተዋጊ አውሮፕላን፣ በተፈነጣጣሪ ፈንጂና በመርዝ ጋዝ ተጠቀሞ ግን ተዋጋ:: አውሮፕላኖቹ የሕዝቡን እውነትና እምነት ሊገድሉ አይችሉም:: ይህ የምለው እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለጋችሁ ፊልሙን ማየት ትችላላችሁ::”

ወዲያው በአዳራሹ ውስጥ መአመር ጋዳፊ ከኢትዮጵያ አማጽያንና ከኤርትራ አማጽያን መሪዎች ጋር ያደረጉትን ውይይት የሚያሳይ የቪዲዮ ፊልም ለጉባኤው ተሳታፊዎች መታየት ጀመረ::

መአመር ጋዳፊ ቀጠሉ::

“ፈጣሪ ይመስገን፤ ታላቁ አብዮት አሸነፈ፤ በውጭ ኃይሎች የሚታገዝ በሙሉ መጨረሻው ይህ ነው::

“ወንድሞቼ፣ ይህ ወቅት በአፍሪካና በኢትዮጵያ የአዲስ ታሪክ ምዕራፍ ነው:: ከአሁን ወዲያ፣ ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር፤ የአረቦች ሀገር መሆኗን ማመናችንን ልትረዱ ይገባል፤ እኛ አረቦች እስራኤልን ፈጽሞ አንቀበልም:: እስራኤላውያን ሰሎሞንን ይጠቅሳሉ፤ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነቢያችን ንጉሣችን ነው ይላሉ:: ምኒልክ ከዚያ ወገን ደም አለኝ ይላል:: ይህ ሰው ሰሎሞናዊ የዘር ግንድ ያገኘና የኢትዮጵያን ንጉሣዊ ቤተሰብ የመሠረተ ነው:: የኢትዮጵያን ትውልድ የሚጠብቅ ይህ ቤተሰብ ነው:: በዚህም ምኒልክ በአረቦችና በእስራኤል መካከል ያለውን ደመኝነት የኢትዮጵያና የአረቦች ደመኝነት አደረገው::

“ከጥቂት ንጉሣዊ ቤተሰቦች አባላትና ከቁጥር ከማይገቡት ሻንቅሎች በቀር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አረባዊ ነው:: ኢትዮጵያውያንም ሁሉም አረቦች ናቸው::

“ኢትዮጵያ የእኛ ሀገር ናት፤ ሕዝቡም የእኛ ሕዝብ ነው:: እነዚህ ሕዝቦች ምንጫቸው አረብ ነው፤ ማንም መሳቅ የሚፈልግ ከትከት ብሎ መሳቅ ይችላል:: ያመነም ይመን፤ ኢትዮጵያ የአረብ ናት” ብለው ኮሌኔል መአመድ ጋዳፊ የአፍሪካ ካርታ ወደሚታይበት ጥቁር ሰሌዳ ሄደው ቆሙ::

“ወንድሞች ከዚህ ወቅት ጀምሮ የአረቦች ካርታና ሀገር ይሄ ክልል ነው፤” የጉባኤው ተሳታፊ ለደቂቃዎች የማያቋርጥ ጭብጨባ::

ጋዳፊ በያዙት ጠመኔ፤ ጅቡቲን፣ ሶማልያን፣ ሱዳንን፣ ኢትዮጵያን፣ ቻድን፣ ኒጀርን፣ ኤርትራን፣ እስከ ሴኔጋል ድረስ ያለውን የካርታውን ክፍል በጠመኔ አቀለሙት:: “ይህንን ካርታ በዚህ መልክ መቀየር አለብን:: ተመልከቱ፤ ይቺ ኢትዮጵያ የአረብ ነች፤ ደግሜ ልንገራችሁ፣ ኢትዮጵያ የአረብ ነች፤” ንግግራቸው እንደገና ለደቂቃዎች ባልተቋረጠ ጭብጨባ ተቋረጠ::

ኮሎኔል ጋዳፊ በስሜት ተሞልተው፣ “አንድ የአረብ ሕዝብ! አንድ የአረብ ሠራዊት!” ሲሉ መፈክር አሰሙ:: ተሰበሳቢው በሙሉ ከመቀመጫው ተነሥቶ፤ ከታላቁ የሊቢያ አረብ ጀመሃርያ ወንድም አብዮታዊ መሪ ከመአመር ጋዳፊ ጋር መፈክሩን አብረው ያወርድ ጀመር::

ጋዳፊ አሁንም በስሜት እንደተዋጡ፣ “ዐሥራ ሰባተኛው ሕዝባዊ ጠቅላላ ጉባኤ፤ በኢትዮጵያ የተካሄደው ኃያልና ሕዝባዊ አብዮት ባስመዘገበው ድል ዳግም በተሣካ ሁኔታ በመጠናቀቁ ጠቅላላ ሕዝባዊ ጉባኤውን ለማመስገን እወዳለሁ” አሉ::

ለደቂቃዎች የዘለቀ ጭብጨባ አዳራሹ ያናውጠው ጀመር::

ይህ የሆነው የኢህአዴግ ጦር አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ከሃያ ቀናት፤ ሻዕቢያ ደግሞ መላዋን ኤርትራን ከተቆጣጠረ ከሃያ ሦስት ቀን በኋላ፤ ሰኔ 10 ቀን፣ 1983 ዓ.ም. ነበር::

“የትግል አጋሮቼ ገደል ይግቡ” አሉ የተባሉት የቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፤ በዚምባብዌ በስደት ሃያ ሰባተኛ ዓመታቸውን እያገባደዱ ነው::

ከዓመታት በኋላ ራሳቸው መአመር ጋዳፊ በጠላትነት ከፈረጇቸው ከአሜሪካና ከእንግሊዝ ጋር አብረው መሥራት ጀምረው ነበር:: ከዐሥር ዓመት በፊት መላውን የአረብ ዓለም ያናወጠው የአረብ ስፕሪንግ፤ ከምስራቅ ሊቢያ ተነሥቶ ለአርባ ዓመታት አፍሪካውያን ጎረቤቶቻቸው፤ እንዲሁም መካከለኛው ምስራቅ ድረስ እየተሻገሩ በሚሰነዝሩአቸው ፀብና ፍጹም በሆነ ጣልቃ ገብነት ይታወቁ የነበሩት ሙአመር ሞሀመድ አቡማናየር ጋዳፊ፤ ከተወሰኑ ደጋፊዎቻቸውና ከግል ጠባቂዎቻቸው ጋር በተሸሸጉበት የትውልድ ከተማቸው ሲርት ውስጥ፤ በሊቢያ አማፅያን ተያየዘው በ73 ዓመታቸው ተገድለዋል::

እኛም፣ የዛሬ 27 ዓመት፤ ሙአመር ጋዳፊ “አንድ የአረብ ሠራዊት” ለመመስረት ከነበራቸው ዓላማ ውስጥ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ለማካተት ወስነው፤ ለታላቁ የሊቢያ አረብ ጀምሃሪያ አብዮታዊ ሕዝባዊ ኮንግረስ ጠቅላላ ጉባኤ ያደረጉትን ንግግር ለታሪክ ትውስታ ወደኋላ ተመልሰን እንዲህ ዘከርነው::

# ስደተኞችን በዕንባ የሚቀበል መሪ



በፎቶው የምታዩት የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ (Justin Trudeau) ይባላል:: ይህ ሰው ከ25 ሺህ በላይ ቦምብ እንደዝናብ የሚርከፈከፍባቸውን የሶርያ ሕፃናት፤ አውሮፕላን ልኮ ወደ ሀገሩ እጁን ዘርግቶና ተቀብሎ በማስገባት በካናዳ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ሰጥቷቸዋል።

በሀገረ ካናዳ የሚገኙ ከ500 የሚበልጡ ዶክተሮች፣ የጋራ ፊርማ በማሰባሰብ፤ "ደመወዛችን ይቀነስ" በማለት ሐሳባቸውን ገልጸዋል።

# በሳቅ ምክንያት ለሕልፈተ ሕይወት የተዳረጉ ግለሰቦች

1. **አሌክስ ሚሼል**፡- እ.ኤ.አ በ1975 በአንዱ ዕለት አመሻሽ ላይ "Kungfu Kapers" የተባለውን ፊልም እያየ ከፊልሙ አንዱ ትዕይንት ያስቀውና ከ30 ደቂቃ በላይ በሳቅ ፍርፍር እያለ ሕይወቱ አለፈ::
2. **ቶማይነሲን ኡም**፡- እ.ኤ.አ በ2003 የከባድ መኪና ሹፌር የሆነው ይኸው ግለሰብ ካለማቋረጥ ለ2 ደቂቃ ከሳቀ በኋላ ትንሽ ልረፍ ብሎ ጋደም እንዳለ እስከመጨረሻው አሸልቧል::
3. **ኦሌ ቤንዜን**፡- እ.ኤ.አ በ1988 የጆሮ ሐኪም የነበረው ይህ ሰው፤ "A Fish Called Wanda" የተሰኘውን ታዋቂ የኮሜዲ ዘውግ ያለው ፊልም እያየ እጅግ ይስቃል:: በዚህም ምክንያት በደቂቃ ከ250-500 ልቡ በመምታቱ ሕይወቱ አልፏል::
4. **ክሪሲፐስ**፡- በ3ኛው መ/ክ/ዘመን የነበረው ይህ የግሪክ ፈላስፋ አህያው በአቅራቢያዋ ካለው ወራጅ ያገኘችውን እንቁራሪት ስታንከባልለው ያይና በሳቅ ፍርስ ይላል:: ከደቂቃዎች በኋላም ሕይወቱ አልፏል::

# የሶርያ ሕፃናት ሰቆቃ



በዚህ ፎቶ ላይ የምታዩት የአራት ዓመት ሕፃን ብቻውን ከሶርያ በረሃ ወደዮርዳኖስ በመሄድ ላይ ሳለ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ሠራተኞች ሲያገኙት የተነሣ ፎቶ ነው

ያንጠለጠለው ፌስታል ውስጥ የተገኘው ብቸኛ ነገር በጦርነት የሞቱት የእናቱ እና የእህቱ ልብስ ብቻ ነበር::

# አባባሎች

ስኬት ብዙ አባቶች ሲኖሩት ውድቀት ግን ወላጅ አልባ ነው።
ስኬት እና እረፍት አብረው አይሄዱም።
ብዙ አዳምጥ ጥቂት ተናገር፤
ረጃጅም ጢሞች አእምሮን ሊተኩ አይችሉም።
በወደቀ ሰው አትሳቅ፤ ከፊትህ ያለው መንገድ አዳላጭ ነውና።
የዛፍ ፍሬውን፣ የሰው ተግባሩን ተመልከት፤
በጦርነት ጊዜ ሕግ አይሠራም።
በጠብ ጊዜ፣ ክፍሉን ለቀህ ውጣ፤
ለመሥራት ጊዜ ከሌለህ፤ ደጋግመህ ለመሥራት ጊዜ ሊኖርህ ይገባል።
እባብ ያየ በልጥ በረየ፤
ሰላም የሚቆየው ወታደር እስኪመጣ፤ ወታደርም የሚቆየው ሰላም እስኪመጣ ነው።
ወደ ባህር ዳርቻው እየቀዘፍህ ወደ አምላክህም ጸልይ።
ሰነፎች በሌሎች ትክሻ መኖር ይፈልጋሉ።
ገንዘብ ለማግኘት እንጂ፣ ለማጥፋት ደቂቃ አይወስድም።
የአንዲት ቅጠል መውደቅ ለጓደኞቿ የሹክሹክታ ያህል ነው።
መስታወትን የሚያደቀውም፣ ብረትን ቅርፅ የሚሰጠውም፤ ያው መዶሻ ነው።

# ስለ ሩሲያ

- ሩሲያ በቆዳ ስፋት ከዓለም ትልቋ ሀገር ናት፤ ስፋቷም 17 ሚሊዮን ስኩዌር ኪ.ሜ ሲሆን የምድርን አንድ ዘጠነኛ ይሸፍናል። (ቢ.ቢ.ሲ)
- ሩሲያ በዓለም ላይ ረዥሙ የባቡር መስመር ይገኝባታል፤ ትራንስ - ሳይቤሪያን የተባለው ይህ የባቡር መስመር መላ ሀገሪቷን ያገናኛል፤ አጠቃላይ ርቀቱም 9,200 ኪ.ሜ ሲሆን፣ አንዱ ባቡር ሳይቆም ርቀቱን ለመሸፈን 152 ሰዓት እና 27 ደቂቃ ይፈጅበታል። (ዘ ቴሌግራፍ)
- ሩሲያ በአውሮፓና በእስያ ምድር ያረፈች ሀገር ናት። አንድ አራተኛ ግዛቷ በአውሮፓ ሲገኝ፤ ሦስት አራተኛው ግን በእስያ ያረፈ ነው። ሊሰመርበት የሚገባው ግን 22 ከመቶ የሚሆነው ህዝብ የሚኖረው በእስያ ባለው ክፍል ነው። (ወርልድ አትላስ)
- ሞስኮ ከሌሎች የሩሲያ ከተሞች ጋር ስትነፃፀር የብዙ ቢሊየነሮች መኖሪያ ናት። ከዚህም አንፃር የ73 ቢሊየነሮች መኖሪያ ስትሆን፤ ደረጃዋም 82 ቢሊየነሮችን ከያዘችው ከኒዮርክ እና 75 ቢሊየነሮች ካሏት ከሆንግ ኮንግ ቀጥሎ ነው። (ፎርብስ)
- ሩሲያውያን ከቤላሩስ ከሞልዶቫ እና ከሊቱኒያ ቀጥለው በአራተኛ ደረጃ የሚገኙ አልኮል ጠጭዎች ናቸው። በዚህም ሳቢያ በራሽያ ውስጥ ከአምስት ወንድ ሰዎች ሞት ውስጥ የአንዱ ሞት ከአልኮል ጋር የተያያዘ መሆኑ እንደ ምክንያት ይቀርባል። (ዘ ቴሌግራፍ)
- እስከ 2011 ዓ.ም. ድረስ የአልኮል ይዘቱ ከ10 በመቶ በታች የሆነ አልኮል እንደ ምግብ ይቆጠር ነበር። (ቢ.ቢ.ሲ)
- ሩሲያ ከ14 ሀገራት ጋር ድንበር ትዋሰናለች። እነዚህም ሀገራት ኖርዌይ፣ ፊላንድ፣ ኢስቶንያ፣ ላቲቪያ፣ ሊቱንያ፣ ፖላንድ፣ ቤላሩስ፣ ቻይና፣ ዩክሬን፣ ጆርጂያ፣ አዘርባጃን፣ ካዛኪስታን፣ ሞንጎልያ እና ሰሜን ኮርያ ናቸው። ይህንን ያህል አዋሳኝ ያለው ሌላ ሀገር የለም። (ዘ ቴሌግራፍ)

የሩሲያ የስልክ መደወያ ኮድ 007 ነው። (ካንትሪ ኮድ)

# 18,000 ዶላር የበላችው አይጥ



ህንድ ውስጥ በሚገኘውና ባለቤትነቱ የህንድ መንግሥት በሆነው ባንክ የሚሠሩ የባንክ ቴክኒሽያኖች ለተወሰኑ ቀናት መሥራት ያቆመውን የባንኩን ኤቲኤም (ATM) ማሽን ለምን እንደማይሠራ ሲፈትሹት የአይጥ ሽታ ይደርሳቸዋል::

የኤቲኤም (ATM) ማሽኑን ሲከፍቱትም፣ በውስጡ ያገኙት 18,000 ዶላር የሚያወጣ የህንድ ሩፒ ከጥቅም ውጪ ሆኖ ነው:: ሩፒውን የበላችውን አይጥም ሞታ አግኝተዋታል::

ባለቤትነቱ የህንድ መንግሥት የሆነው ይህ ባንክ፤ የህንድ ትልቁ ባንክ ሲሆን፣ በሀገሪቱ ውስጥ ከ50,000 በላይ ኤቲኤም (ATM) ማሽን አለው::

በኤቲኤሙ (ATM) ውስጥ ከነበረው 2.5 ሚሊዮን ሩፒ (42,685 ዶላር) 1.7 ሚሊዮን ሩፒ (25 022 ዶላር) ያህሉ ሳይበላሽ ተገኝቷል:: 1.2 ሚሊዮን ሩፒ (17,662 ዶላር) የሚሆነው ግን ከጥቅም ውጪ ሆኗል::

1.2 ሚሊዮን ሩፒ (17 662 ዶላር) የሚያወጣው ግን ከጥቅም ውጪ ሆኗል::

ጉዋሃቲ በተባለች ከተማ የተፈጠረውን ይህንን ትዕይንት በካሜራው ካስቀረው ምስል እንደታየው ግራጫ እና ሐምራዊ ቀለም ያላቸው የ500 እና የ2,000 ሩፒ ኖቶች በብዛት ታይተዋል::

# ዳህላክ ላይ ልሥራ ቤቴን



መስፍን ጌታቸው

ፈጣሪ የአንድ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት አካል እሆን ዘንድ ሲመርጠኝ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሃያ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለተኛ ቤታችን ወደሆነችው የኤርትራ ዋና ከተማ አስመራ ከተማ ያደረገው የመጀመሪያ በረራ ላይ ተሳታፊ የመሆን ዕድሉን አግኝቼ ነበር::

በእለቱ፣ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ እንድንደርስ የተነገረን ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ ቢሆንም፤ መንገደኛው ግን ገና ከማለዳው ጀምሮ ነበር በሁለቱ ሀገራት ሰንደቅ ዓላማዎች አምሮና ተውቦ ከስፍራው የደረሰው::

በአጋጣሚ ይሁን ወይም ደግሞ ሆን ተብሎ ባይገባኝም፤ ይህ በረራ የመጀመሪያ እንደሆነው ሁሉ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በማስፋፊያ ፕሮግራሙ ባሠራው አዲስ ተርሚናል የተስተናገድን የመጀመሪያዎቹ መንገደኞች ሆነናል::

ሰዎች፣ አየር መንገድ ደርሰው ሰላምታ ሲለዋወጡ፤ ፊታቸው ላይ የሚታየው የደስታ ስሜት በጣም የሚገርም ነበር:: እርስ በርስ ከተገናኙ በኋላ፣ "ቀጥሎ ደግሞ ማን ይመጣ ይሆን?" በሚል ጉጉት ተከታዩን መንገደኛ ለማየት ጊዜው ደርሶ ብቅ ሲልም፣ "እንዴ አንተም አለህ እንዴ! እንኳን ደስ ያለህ" በመባባል ይደረግ የነበረው መተቃቀፍና መሳሳም ትናንት በጠላትነት እናያት ወደነበረችው ኤርትራ ሳይሆን ወደመንግሥተ ሰማያት የምንጓዝ ነበር የሚመስለው::

ስንሳፈርም የዚህ ታሪካዊ ጉዞ ተሳታፊዎች መሆናችንን የሚገልፅ ቲ-ሸርት፣ እንዲሁም ከተቀመጥን በኋላ እጅግ የሚያምር የጽጌረዳ አበባ ታደለን:: ብዙም ሳይቆይ የ"እንኳን ደስ ያላችሁ" ሻምፓኝ በበረራ አስተናጋጆቹ ተከፍቶልን በደስታ ዋንጫችንን አነሣን::

አውሮፕላኑ ተነሥቶ የተፈቀደለት ከፍታ ላይ ከደረሰ በኋላ ማንም የተቀመጠ ሰው አልነበረም:: ሁሉም ተነሥቶ አስመራ ሊጠብቀው ስለሚችለው ነገር፣ "እገሌን አውቀዋለሁ ወይም ደግሞ አላውቀውም" ሳይል ካገኘው ሰው ጋር ሁሉ ያወራል::

ብዙም ሳይቆይ፣ ኋላ አካባቢ ተቀምጠው የነበሩ መንገደኞች አነስተኛ በሆነች የእጅ ቴፕ ለስለስ ያለ የትግርኛ ዘፈን ከፍተው መጨፈር ሲጀምሩ፤ መንገደኛው በጠቅላላ ግልብጥ ብሎ የአውሮፕላኑ ባላንስ እስኪታወክ ድረስ አካባቢውን አጥለቀለቀው::

የበረራ አስተናጋጆቹ፣ ተሳፋሪውን ለማረጋጋት ቢሞክሩም የሚሰማቸው ጠፋ:: ምግብና መጠጥ እንደልብ ተዘዋውሮ ማቅረብ የማይታሰብ ሆነ:: ከትንሿ ቴፕ የሚወጣው ሙዚቃ አልሰማ በማለቱም፣ ዜማ አዋቂ መንገደኞች ዘፈን እያወረዱ ጭፈራው ቀለጠ::

"ጉሮ ወሸባዬ፣ ጉሮ ወሸባዬ፤ ዐቢይ ድል አርጎ ሲገባ፤ ኢሱ ድል አርጎ ሲገባ" በሚል የደስታ ዜማ አውሮፕላኑ ተንቀጠቀጠ፤ በስፍራው የነበሩ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ጋዜጠኞች በዚያች ጠባብ ቦታ ትዕይንቱን ቀርፀው ዜናውን ለዓለም ህዝብ ለማድረስ ስቃያቸውን አዩ::

ከብዙ የማረጋጋት ሙከራ በኋላ፣ ዋና አብራሪው "እንኳን ደስ አላችሁ! ከሃያ ዓመታት በኋላ፣ የኢትዮጵያን የአየር ክልል በመጨረስ የኤርትራን ድንበር ተሻግረናል" በማለት ሲናገር የተፈጠረው ደስታና እልልታ፤ ቃላት ፈፅሞ ሊገልፁት የሚችሉት ዓይነት አይደለም::

ወዲያው ሰው፣ "አስመራ" ከአየር ላይ ምን እንደምትመስል ለማየት፣ ወደ አውሮፕላኑ መስኮቶች ተንደረደረ:: አጋጣሚው የፈጠረውን መረጋጋት በመጠቀም፣ የበረራ አስተናጋጆቹ የ"እንኳን ደስ ያላችሁ" ኬክ፤ መንገደኛው መካከል አምጥተው በመቁረስ ለተሳፋሪው አደሉ::

ከብዙ ልመናና ተማፅኖ በኋላ፣ አውሮፕላኑ ሲያርፍ የሚፈጠረውን መንገጫገጭ ለመከላከል፤ ሁሉም ሰው ቦታውን ይዞ፣ የመቀመጫ ቀበቶውን እንዲታጠቅ ቢደረግም፤ ገና አውሮፕላኑ መሬት ከመርገጡ፣ ተሳፋሪው እያፏጨና እያጨበጨበ፣ ቀበቶውን ፈቶ መነሣት ጀመረ::

ይህ ድርጊት፣ ከበረራ ደህንነት ሕግጋት ጋር የሚጋጭ በመሆኑ፤ የበረራ አስተናጋጆች ሳይወዱ በግድ ተነሥተው መንገደኛውን ለማስቀመጥና ቀበቶውን እንዲታጠቅ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም፤ የሚሰማቸው ጠፍቶ አውሮፕላኑ የተፈቀደለት ማቆሚያ ጋር ደርሶ ሞተሮቹን አጠፋ::

ስንወርድ፣ የአየር ማረፊያው ግቢ በሰው ጎርፍ ተጥለቅልቆ ጠበቀን:: የአስመራ ቆነጃጅት ከሚያጠግብ የሞቀ ፈገግታ ጋር ለሁላችንም አበባ ሰጥተው በፍቅር ተቀበሉን:: እናቶችና ትልልቅ ሴቶች እየዘፈኑና እየጨፈሩ ወደ አውሮፕላኑ ሲመጡ እኛም "ጉሮ ወሸባዬ" እያልን በደስታ ተቀላቀልናቸው::

አውሮፕላን ማረፊያው ድብልቅልቁ ወጣ:: የነሱ የትግርኛ ዘፈንና የኛ "ጉሮ ወሸባዬ" ዜማው በጣም የተራራቀ ቢሆንም፤ ከሁሉም ሰው ልብ ውስጥ ፈስሶ የሚርከፈከፈው ፍቅር በጥበብ አዋዶ አስናናውለለ

ጭፈራው ከልክ በላይ ደራ:: ባንዲራዎች ከጥግ እስከ ጥግ በስሜት ተውለበለቡ:: የሁሉም ሰው ዓይኖች የደስታ እንባ አነቡ፤ እጆች ደግመው ደጋግመው ተጨባበጡ:: ጋዜጠኞች በሰው መካከል እየተሹለከለኩ ኢንተርቪው ለማድረግ ስቃያቸውን አዩ::

ሁላችንም በተደረገልን ደማቅ አቀባበል ተደስተን ቪዛና ሻንጣ ለመረከብ ወደ ተርሚናሉ ስናመራ በር ላይ የኢቲቪውን ጋዜጠኛ አዲስ አለምን አንድ ፈረንጅ አስቁሞ፣ ኢንተርቪው እያደረገ ሳየው በጣም ደስ አለኝ::

አዲስ ዓለምን የማያውቀው ሰው ያለ አይመስለኝም:: የረዥም ጊዜ ወዳጄ የሆነው ይህ ጋዜጠኛ፣ ባለቤቱና ሁለት ሴት ልጆቹ ተባረውበት ለሃያ ዓመታት በናፍቆትና በስቀቀን ሲማቅቅ የኖረ ሰው ነው:: ይሄን አሳዛኝ ታሪኩን የሚያሳይ ዘገባ ኢቲቪ ሠርቶ አየር ላይ አውሎታል:: ብዙዎቹም በማህበራዊ ሚዲያ ተቀባብለው ከሱና ከቤተሰቦቹ ጋር አብረው አንብተዋል::

አዲስ ዓለምን ሳየው ያለ ልክ የተደሰትሁት ለዚህ ነው:: ሁኔታው ትዕግሥት አሳጥቶኝ ኢንተርቪውን አቋርጦ እንዲያናግረኝ በማሰብ ብቀርበውም፣ "ትንሽ ጠብቀኝ" በሚል አቆየኝ::

ኢንተርቪውን እንደጨረሰ በደስታ ተጠመጠምሁበት:: አንገት ለአንገት እንደተያያዝን ተሳስመን ሳንጨርስ፣ "ልጆችህን አገኘሃቸው?" ብዬ ስጠይቀው የሰጠኝ መልስ ክፉኛ አስደነገጠኝ:: ልጆቹና ባለቤቱ መጥተው በናፍቆት ውጪ እየጠበቁት ነው:: እሱ ግን አንዴ እንኳን ወጥቶ ሰላም ሳይላቸው፤ በፅናት ሥራውን እየሠራ ነው::

እኔ ይሄንን ፈፅሞ ማመን አልችልም:: የሃያ ዓመት ናፍቆትና ያ ሁሉ እንባና ሰቀቀን እንዴት ነው ተችሎ ሥራ የሚሠራው? እንዴትስ ነው እጅ ጨብጦ እንደበት ጥያቄ ሊያፈልቅ የሚችለው? የሃያ ዓመት ናፍቆትና መድኃኒቶችህ ከሁለት መቶ ሜትር በማይበልጥ ርቀት ላይ ቆመው በስስት እየጠበቁህ፤ ማን ነህ ላፍታ እንኳን ወጣ ብለህ ዓይናቸውን ሳታይ ሥራህን በእርጋታ መሥራት የምትችለው? ማን ነው እሱ ከካሜራ ባለሙያ ጋር ተግባብቶ ሰው ሁሉ ወጥቶ እስኪያልቅ ድረስ ቆሞ ቃለ መጠይቅ ማድረግ የሚችለው?

ማንም የሚችል አይመስለኝም:: እኔ በበኩሌ አልችልም:: እሱ ግን ችሎታል:: መቻል ብቻ ሳይሆን እስከመጨረሻ ድረስ በፅናት በመቆምም የሥራን ክቡርነትና የርሱን ጀግንነት አሳይቶናል:: ለዚህም ታላቅ ክብርና አድናቆት ይገባዋል::

ቪዛችንን ተቀብለን ስንወጣ፣ ከኛ ቀድመው ከወጡ ሰዎች መካከል አንድም ሰው በስፍራው አልነበረም:: ሄደው ነው እንዳይባል፣ የሁሉም ▶



ዳህላክ ደሴት

ሰው ሻንጣ አንድ ጥግ ላይ ተከምሮአል::

እኔና ጓደኞቼ፣ ምክንያቱ የገባን በጣም ዘግይቶ፤ ከግቢ ውጪ የሚደመጠውን ከፍተኛ ሁካታና ጭፈራ ስንሰማ ነው::

ጊዜ ሳናጠፋ ጭፈራውን ወደሰማንበት ቦታ ስንሄድ ሀገር ተደባልቆአል:: የአስመራ ህዝብ በነቂስ በመውጣት በር ላይ ጭፈራውን አቅልጦታል:: የኛም መንገደኞች ነጭ ላብ እስኪወጣቸው ድረስ ይቀውጡት ይዘዋል::

ውስጥ ያለቀ የመሰለን አቀባበል፣ ውጪ በብዙ እጥፍ አድጎ ቀጥሎአል:: ከየአቅጣጫው የፈንዲሻ መዓት ይዘንባል:: ከየት እንደመጣ ያላየኸው ሰው በፍቅር ተወርውሮ አንገትህ ላይ ይጠመጠማል:: “እንኳን ለዚህ ቀን አበቃን፤ እንኳን ሳንሞት ይሄን ታሪክ ለማየት ታደልን” እያለ ፍፁም አንጀት በሚበላ ወንድማዊ ፍቅር፤ እያነባ በጥልቅ ስሜት ይስምሃል:: አንተም ባየኸው ድንቅ ተአምር ልብህ እየተነካ፣ አፀፋውን በደስታ ትመልሳለህ:: ወንዱም ሴቱም፤ አዛውንት አሮጊቱም በእንዲህ አይነት ስሜት እየተንሰፈሰፈ ሲስምህ፤ እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ ህልም እንጂ እውነት አይመስልህም::

ትንሽ ፋታ ያገኘነው፤ የአካባቢ ጎረምሶች፣ “በቃ…በቃ እንግዶቹ ርቧቸዋል” በሚል ሰውን በብዙ ትግልና ግብግብ ተረዳድተው ሲመልሱት ነበር:: እኛ ግን አልራበንም:: ደሞስ ያን ሁሉ በላያችን ላይ የሚዘንብ ፍቅር እየተመገብን እንዴት ሊርበን ይችላል?

ከዚህ በኋላ፣ ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ግቢ ተመልሰን ስንገባ፤ ሁሉም ሰው፣ በር ላይ ሲዘንብ ያየው የፍቅር ዶፍ ከመመለሱ በፊት፤ አባርቶ ይጠብቀው ይመስል በትግስት ማጣት እየተቁነጠነጠ ነበር የወጣው::

ሻንጣችንን ተቀብለን ለታክሲና ለሆቴል የምንከፍለው ገንዘብ ለመዘርዘር ስንሰለፍ፤ ብዙዎቹ ቆመው የሚጠብቁበት፣ ትዕግስት አጥተው “ከናንተ እንበደራለን” በሚል ጥለውን ወጡ::

ገንዘቡን ዘርዝረን ስንወጣ ግን፣ የሚዘንበው የፍቅር ዶፍ አላባራም:: እንዲያውም ኃይሉን አስተባብሮ፣ ጉልበቱን ጨምሮ ነው የጠበቀን:: የመነዘርነው ገንዘብም ዋጋ አልነበረውም::

ማን ሻንጣችንን እንደተቀበለን፣ ማን እየመራ ወደመኪና እንደወሰደን አናውቅም:: የአስመራ ህዝብ በሙሉ፣ መኪኖቹን አግተልትሎ እንግዶቹን ለመቀበል ስለወጣ፤ የኛን ግሩፕ የማናውቃቸው ሰዎች በሁለት መኪና በመጫን ይዘውን ወደ ከተማ መሄድ ጀመሩ::

ከተማ ሲገባ ደግሞ፣ እንደገና ሌላ ደስታ፣ አየር መንገድ ያልመጣው ህዝብ፤ አስፋልት ዳርና ዳር ቆሞ በሆይታና በእልልታ ሲቀበለን፤ እኛም በአስተናጋጆቻችን ፊታውራሪነት የመኪና ጥሩንባ ከልክ በላይ እየሰማንና አንገታችንን አውጥተን “ኡ ኡ” እያልን የአስመራን ከተማ ሦስት አራቴ ተመላልሰን ዞረን ወደ ሆቴላችን አቀናን::

ምሳችንን የበላነው ከኢትዮጵያ ተፈናቅለው የሄዱ ባልና ሚስት በከፈቱት ታዋቂ ሬስቶራንት ውስጥ ነው::

ኤርትራ ምግብ የሌለ፤ ህዝቡም ደህና ነገር በልቶ የማያውቅ የሚመስለን ሁሉ በጣም ተሸውደናል:: ሁላችንም የተስማማንበት አንድ ሐቅ ቢኖር፣ በሕይወታችን ከበላናቸው ክትፎዎች እጅግ ጣፋጩን የበላነው በዚህ ቤት ነው::

እንጀራው ላይ ምን ጨምረው እንዲያ እንዳሳመሩትና እንዳለሰለሱት እግዜር ይወቀው:: የቀረበልን ትኩስ አይብ ብቻውን ቢበሉት ቢውሉ አይጠገብም:: በዚያ ላይ ጣዕሙ ለረዥም ጊዜ ከአፍ አይጠፋም:: ለጋ ቅቤ እንደጉድ እየፈሰሰ ክትፎውን፣ ጎረድ ጎረዱን፣ ጥብሱን፣ ቀይ ወጡን ያለ ሃሳብ ልኩን አሳየነው:: ሁላችንም ብዙ በመብላታችን እራት አላስፈለገንም ነበር::

በእርግጥ፣ ይሄን ጣፋጭ ምሳ ያበላችን ሴት፤ ስለፍቅር ብዙ ዋጋ የከፈለችና ከጉራጌ ምድር የበቀለች ኢትዮጵያዊ ሴት ነበረች::

ከምሳ በኋላ መሎቲ ቢራችንን በአስመራ አረቄ እያወራረድን በሞቀ ፍቅርና ጨዋታ ራሳችንን ዘና እያረግን አልፎ አልፎም በኃዘን፣ በደስታና በፀፀት እያነባን ቆየን::

ሁሉም ሰው የሚያያችሁ በትልቅ ፍቅርና ስስት ነው:: ፍቅሩ ሳታስቡት እናንተም ላይ ተጋብቶ ትሳሳላችሁ:: የሚጠሩን “ወንድሜና እህቴ” እያሉ ነበር:: ከዚህ ውጪ ሌላ ስም አልነበረንም:: የኛን እግር ተከትሎ ከፍተኛ ዝናብ መዝነቡም ትንግርት ሆኖባቸዋል:: ሁሉም በአግራሞት አፋቸውን በመያዝ፣ “ለረዥም ጊዜ በሐሩር ስንቃጠል ኖረን፣ ድንገት ደርሳችሁ አረጣጠባችሁን እኮ” እያሉ እግረ ለምለም መሆናችንን ደጋግመው ይነግሩን ነበር::

ከዚህ በኋላ፣ ሌላ ቤት ተዘጋጅቶ የሚጠብቀን ሁለተኛ ምሳ እንዳለ ተነግሮን ሂሳብ ስንጠይቅ፤ ሁሉም ሰው በአንድ ላይ ሳቀብን:: እንዲህ ዓይነት ድፍረት በአስመራ ምድር የሚታሰብ ባለመሆኑ ብንለምን የሚሰማን አጣን::

በመጨረሻም፣ በፍቅር ተነሥተንና ክብ ሠርተን እጅ ለእጅ በመያያዝ ስለ ሁለቱ ሀገሮች ሰላም፤ ስለፍቅርና ወንድማማችነት ፀልየንና ተመራርቀን ወጣን::

በየሄድንበት ቦታ ሁሉ፣ ከዚህ የበለጠ ፍቅር እየተቀበልን በደስታና በሆታ እየተጫወትን አመሸን::

ማታ ላይ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ያዘጋጀው የእራት ግብዣ ቢኖርም፤ ህዝቡ ግልብጥ ብሎ በመውጣቱና ቦታ በማጣታችን፤ አዳራሹን በርቀት ተሳልመን ተመለስንና በፍቅር ስንጫጫስ አድረን ከሌሊቱ ዐሥር ሰዓት ላይ ሆቴላችን በመግባት ጎናችንን አሳረፍን::

ጠዋት ላይ የነቃነው ተቀስቅሰን ነበር:: በማግስቱ ምፅዋ ለመሄድ አስበን ስለነበር፤ ይሄን ያወቁት ትናንት ሲያዝናኑን ውለው ያደሩት ወጣቶች ነበሩ መኪናቸውን ነዳጅ ሞልተው መጥተው የቀሰቀሱን::

የሆቴላችንን ክፍያ ቀድመው ከፍለውታል:: መከራከር የሚያመጣው ዋጋ ስለሌለ ተከራክረን “ደስታቸውን ለምን እናደፈርስባቸዋለን?” በሚል ዝም ብለን ጉዞአችንን ወደ ምፅዋ ቀጠልን::

ምፅዋ ስንደርስ ግን በጣም ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ተሰማን:: ማንም ኢትዮጵያዊ ቀይ ባህር ፊት ሲቀርብ ሊሰማው የሚችለው አይነት ስሜት:: ያ ሁሉ ደም የፈሰሰለት፣ ያ ሁሉ የወገን ነፍስ የተገበረለት፤ ዛሬ ግን ምንም ዋጋ የሌለው ሆኖ በሰፊው በረሃ ላይ የተንጣለለ ውሃ… ቀይ ባህር…

ኤርትራን ከረገጥንበት ጊዜ አንስቶ ሁለት ጊዜ ብቻ የሐዘን ስሜት ተሰምቶኛል:: አንዱ ቀይ ባህርን ሳይ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፣ እንዲያ በፍቅር አንቀባረው መሬት እንዳይነካን እየተጠነቀቁ ሲያስተናግዱን የነበሩትን ልጆች፤ ኢትዮጵያ መጥተው በተራችን ልናስተናግዳቸው አለመቻላችንን ማወቂ ነበር::

ልጆቹ የማይመጡት፣ ከኤርትራ መውጣት የማይችሉ ብሔራዊ ወታደሮች በመሆናቸው ነው:: 99% ያህሉ የኤርትራ ወጣት በተጠንቀቅ ላይ የሚገኝ ብሔራዊ ወታደር ነው:: ስለዚህ የትም ንቅንቅ ማለት አይችልም::

ታዲያ ይህ አያሳዝንም:: ሦስት ቀን ሙሉ ምግብ ሳይቀምሱ፣ ቤታቸው ሳይገቡና እንቅልፍ ሳያምራቸው፤ የሀገራችንን ባንዲራ ለብሰው ሲያስተናግዱን የቆዩ ወንድሞቻችንን በተራችን ለማስተናገድ እድል አለማግኘታችን በርግጥም በጣም ያሳዝናል::




# ይፋ የሆነው ምስጢርና አሳዛኙ የኢ/ር ስመኘው አሟሟት

የሕዳሴ ግድብ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ስመኘው በቀለ፤ ሐሙስ፣ ሐምሌ 19 ቀን፣ ጠዋት በመስቀል አደባባይ መኪናቸው ውስጥ እንዳሉ ሞተው ተገኝተዋል:: መላ ኢትዮጵያውያንን ያሳዘነውና ያስደነገጠው ይህ ጉዳይ ከጅምሩ የኢንጅነሩን አሟሟት በተመለከተ፤ በህብረተሰቡ ዘንድ የተለያዩ መላ ምቶች እንዲሰዘነሩ አድርጓል::

የሕዳሴው ግድብ ፕሮጀክት ይፋ ከሆነበት መጋቢት 20/2004 ዓ.ም ጀምሮ፤ የዚህ ታላቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ በመሆን፤ ሙያዊ አገልግሎት እየሰጡ የነበሩት ኢንጂነር ስመኘው በቀለ ግድቡን አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያት በሚሰጧቸው መግለጫዎችና ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ግድቡ የሚጎርፈውን ሕዝብ ያለ መታከት በመቀበል፣ በማስጎብኘትና ሙያዊ ትንታኔ በመስጠት በአጭር ጊዜ ውስጥ በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ዕውቅና ለማግኘት መቻላቸው ይታወቃል::

የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር የአቶ መለስ ዜናዊ መግለጫ፣ የህዳሴው ግድብ በአምስት ዓመት ውስጥ ውሉ እንደሚጠናቀቅ በመግለጽ፤ በፍላጎትም ሆነ በተጽዕኖ በተለይ የመንግሥት ሠራተኛው ከሕብረተሰቡ ከፍተኛ ገንዘብ እንዲሰባሰብ አድርገው ነበር:: በጊዜ ሂደት እንደታየው ግን በስድስተኛው ዓመት ላይ ብንገኝም፤ አጥጋቢ ሥራ እንደተሠራ ለማወቅ ተችሏል:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን እንደገለፁት ከሆነ፣ የህዳሴው ግድብ በሚቀጥሉት ዐሥር ዓመታት መጠናቀቁ አጠራጣሪ ናው::

በሕዳሴው ግድብ ተቋም ውስጥ ሆነው የግንባታው መጠን፣ "ሃምሳ ፐርሰንት ደረሰ፤ ስልሳ ፐርሰንት ገባ" እያሉ ሲገልፁ የነበሩት የመንግሥት ሓላፊዎች፤ ሕዝቡን ተስፋ በመስጠት ምንም ባልተሠራበት ሁኔታ በሐሰት መረጃ ገንዘብ ሲሰበስቡ መኖራቸውን ያረጋገጠውና የተደበቀውን እውነታ ያጋለጠው የጠ/ሚኒስትሩ መግለጫ በተሰማበት ማግሥት ሞተው የተገኙት የኢንጂነር ስመኘው ጉዳይ በርግጥም አጠያያቂ ገፅታ እንዳለው ለማየት ይቻላል::

ኢንጂነሩ፣ የግድቡ ዋና ሥራ አስኪያጅ የመሆናቸውን ያህል በርካታ ምስጢሮች ሊያውቁ እንደሚችል አያጠራጥርም:: ታይቶ በማይታወቅ መልኩ፣ ከሀገሪቱ ቱባ ቱጃሮች ጀምሮ ዝቅተኛ ገቢ እስካላቸው ዜጎች ድረስ የተሰበሰበው ገንዘብ፤ "ባለፉት ስድስት ዓመታት በትክክል ለታለመለት ዓላማ ውሎ ነበር ወይ? በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ ውስጡን እንደሚሰማው የህወሐት የበላይነት የሰፈነበት ያለፈው አመራር፤ ይህን የህዝብ ገንዘብ፣ ለግል ጥቅሙ አውሎታል?" የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት ከእኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ኢንጂነር መሆኑ ባያጠያይቅም፤ ሁሉም ነገር ምስጢር ሊሆን በሚችል መልኩ ኢንጂነር ስመኘው በቀለ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል::

ኢንጅነር ስመኘው በቀለ፣ "መኪናቸው ውስጥ ሞተው ተገኙ" የሚለው ዜና፤ "እንዴት ሞቱ? ተገድለው ቢሆንስ?" የሚሉ ጥያቄዎችን ማጫሩ አይቀርም:: ሐሙስ ጠዋት፣ መስቀል አደባባይ፤ የሰሌዳ ቁጥር Et ኮድ 3-29722 አዲስ አበባ፣ ላንድ ክሩዘር (V8) መኪናቸው ውስጥ የተገኘው አስከሬናቸው እንደሚያሳየው ከሆነ፤ ኢንጂነሩ ባርኔጣቸውን እንዳደረጉ ቀላ ያለ ጃኬት ለብሰው፣ ወደ ቀኝ ዘንበል ብለው የተገኙ ሲሆን፤ ፖሊሶች ለምርመራ አስከሬናቸውን በሚያወጡበት ጊዜ በግራ ጆሮአቸው ደም ሲፈስ ታይቷል::

በሥራ ገበታቸው ላይ ባላቸው መልካም ባህርይ፣ አብረዋቸው በሚሠሩ ሠራተኞች በሙሉ በእጅጉ ተወዳጅና ተግባቢ የሆኑት ኢንጅነር ስመኘው በቀለ፤ በማህበራዊ ሕይወታቸውም በኩል ከሰው ተግባቢ በደስታና በኃዘን ተካፋይ መሆናቸውን በቅርብ በሚያውቋቸው ይመሰክሩላቸዋል:: ኢንጂነሩ የሕዳሴው ግድብ ፕሮጀክት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ከተሾሙ በኋላ፤ በመላ ሀገሪቱ ከፍተኛ እውቅና ያገኙ ቢሆኑም፣ የትም ቦታ ሲንቀሳቀሱ ያለ አጃቢ በነፃነት ነው፤ መኪናም ቢሆን በብዛት ራሳቸው ናቸው የሚያሽከረክሩት::

"እኔ የፖለቲካ ሹመኛ አይደለሁም፤ የሚጠላኝ ወይም የምፈራው ሰው የለም" በማለት ለጓደኞቻቸው እንደልባቸው በመላ ሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱበትን ምክንያት የተናገሩት ኢንጅነር ስመኘው፤ በርግጥም የህዝብ ፍቅርና አክብሮት ያገኙ ታላቅ ሙያተኛ ነበሩ:: ይህ እውነት ባለበት ሁኔታ፣ ጠ/ሚኒስትሩ በጠዋት ለዚያውም በአደባባይ መኪናቸው ውስጥ እንዴት ሞተው ሊገኙ ቻሉ? የዓባይ ግድብ በሚቀጥሉት ዐሥር ዓመታት ውስጥ እንደማይጠናቀቅ እርግጠኛ በተሆነበት ማግሥት እንዴት ሞታቸው ተሰማ? የሚለው የብዙኃኑ ሕብረተሰብ ጥያቄ ነው::

የኢንጂነር ስመኘው ሞት በተሰማበት ቅጽበት፤ ብዛት ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ወደ መስቀል አደባባይ መጉረፉን ተከትሎ፣ የፌደራል ፖሊስ አባላት ከፍተኛ ጥበቃ በማድረጋቸው፣ ጋዜጠኞቹ የኢንጂነሩ መኪና ወደቆመበት ቦታ እንዳያልፉ የተከለከለ ሲሆን፤ ፖሊስም በጉዳዩ ላይ በቂ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም:: ሆኖም በግልፅ መታዘብ እንደተቻለው፣ በቀኝ በኩል ያለው የመኪናው የኋላ በር ተሰብሯል:: የኢንጂነሩ አስከሬን ውስጡ ያለበት መኪና ሙሉ ለሙሉ ዝግ በመሆኑ አስከሬኑን ለማውጣት በፖሊስ የተወሰደ ዕርምጃ ሊሆን እንደሚችል ተብሎ ተገምቷል::

አስከሬኑ ወጥቶ በጥቁር ፕላስቲክ ተሸፍኖ ወደጳውሎስ ሆስፒታል ለምርመራ ከመጓዙ በፊት በአካባቢው የነበሩ የኢንጂነሩ ቤተሰቦች "እባካችሁ እንየው" እያሉ በማልቀሳቸው ለአፍታም ቢሆን አስከሬኑን እንዲመለከቱት ተደርጓል:: በፖሊስ አምቡላንስ ታጅቦ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የተወሰደውን የኢንጂነሩን የአስከሬን ምርመራ ተከትሎ "ያገኛችሁትን የምርመራ ውጤት ንገሩን" የሚል ጥያቄ የሀገር ውስጥና የውጭ ሚዲያ ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም፤ መጽሔታችን ለኅትመት እስከ ገባችበት ሐሙስ ከሰዓት ድረስ አንዳችም መረጃ ማግኘት አልተቻለም::

ኢንጅነር ስመኘው በቀለ በሲቪል ምህንድስና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በዲግሪ የተመረቁ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ላይ አስተዋጽኦዋቸው ከፍተኛ እንደሆነ የሚነገርላቸው ኢንጂነር ስመኘው፤ ባለፉት ሠባት ዓመታት የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሠርተዋል:: መስከረም 3 ቀን፣ 1957 ዓ.ም በጎንደር፣ ማክሰኚት ነው የተወለዱት:: በኢትዮጵያ ኃይል ኮርፖሬሽንና በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ከ1978 -1991 ዓ.ም ድረስ የኮተቤ ማሰልጠኛ መምህር፤ ከ1991-1992 ዓ.ም በዋና መ/ቤት የኢንጂነሪንግ ዲፓርትመንት ሓላፊ፤ ከ1992-1993 ዓ.ም የጊቤ አንድ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ካውንተር ፓርት ኢንጂነር፤ ከ1997-2002 የጊቤ ሁለት ኃይል ማመንጫ ኮርድኔተርና ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል::

ኢንጂነር ስመኘው በቀለ ከመሞታቸው አንድ ቀን በፊት ከቢቢሲ አማርኛ ጋር ቃለ መጠይቅ ያደረጉ ሲሆን፣ ሕይወታቸው ባለፈበት ሐሙስ ዕለት ምሽት፤ ወደ ህዳሴው ግድብ የመመለስ ዕቅድ እንደነበራቸው ታውቋል:: ኢንጂነር ስመኘው በቀለ፣ የሦስት ልጆች (የሁለት ወንዶችና የአንዲት ሴት) አባት ነበሩ::

በመጨረሻም፤ የኢንጂነር ስመኘው በቀለን ሞት በተለያዩ ሚዲያዎች ሰምቶ ወደመስቀል አደባባይ የተጓዘው ህዝብ የኢንጂነሩ አሟሟት ከፀረ ለውጥ ኃይሎች ጋር ተያያዥነት ሊኖረው ይችላል በሚል የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድና በጉዳዩ ላይ ግልፅ የሆነ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በአደባባዩ ተቃውሞአቸውን ከማሰማት ባሻገር፤ በEBC (በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን) ዋና መ/ቤት በመገኘት መልእክታቸውን አሰምተዋል::

# የአንዷለም አራጌ አዲስ መጽሐፍ በቅርብ ቀን




## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ፣ የሕግ ባለሙያ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ስለመጽሐፉ ምን አሉ!



እኔ እና አንዱዓለም አራጌ በጥቅሉ ካሳለፍነው የስድስት ዓመት ተኩል እስር በግምት ስምንት ወራቱን አንድ ላይ ነበር ያሳለፍነው፡፡ ቀሪውን ጊዜ ተለያይተን ነበር የታሰርነው ፡፡ እነዚያ ስምንት ወራትም ሆኑ ሌሎቹ የእስራት ዓመታት የስራ ጊዜ ነበሩ ብል ማጋነን አይሆንብኝ፡፡ ታስረንም ሥራ አልፈታንም፡፡ አንብበናል፣ ፅፈናል፣ በቀሪው ጊዜ

እስክንድር ነጋ
(እውቅ ጋዜጠኛ እና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች)



በኤሌክትሪክ መብራት መገልገል እንደ ቅንጦት ከሚታይባቸው እና ከጭንቁርቁሶቹ የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከተሞች መካከል አንዷ በሆነችው ክምር ድንጋይ እትብቱን የቀበረው፣ በዛኒ-ጋባ ጎጆ የተወለደው፣ ከከብቶች ጋ ልጅነቱን የቀጨው… የዚህ መጽሐፍ ደራሲ፣ አፍላ የጉርምስና ዕድሜ አንደርድሮ ከሚነክርበት ከተማሪ-አብዮተኛነት አስከ ጎልማሳነቱ ያቀነቀነው የነፃነት ጥያቄ ይቸነከር ዘንዳ ወደ መስቀያው ደጋግሞ አስገፍትሮታል፤ ሥርዓት-ወለድ ስቅየቶችን

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ
(የመለስ አምልኮ እና የፈራ ይመለስ መጽሐፍ ደራሲ)



ይህ አንዱአለም የጻፈው የግጥም መድብል ቡና እየተጎነጨ ቆሎ እየቆረጠመ በምቹ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብሎ የከተበው ሳይሆን ቃልቲ ወህኒ ቤት ለብዙ ጊዜ የሰቆቃ ቤቱ ሆኖ ከሰው ሁሉ እርቆ በብርድ እየተቆራመተ በቀን ሀሩር እየነደደ ጠባቂው አየኝ አላየኝ እያለ በጭንቀት ላይ ሆኖ እነዚህ ከሁለት መቶ በላይ

ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም
ዕውቅ ዓለም አቀፍ የሕግ ባለሙያ፣ ፖለቲከኛና የአሰብ የማናት? ደራሲ



ያሳለፍነው ግማሽ ምዕት ዓመት የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰብአዊ ክብሩና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ የታገለበት ዘመን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሰብአዊ መብቶቹ ባለቤት ለመሆን እስከ አሁን አልታደለም፡፡ እኔም በተፈጠርኩበት በዚህ ዘመን ለራሴ፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት

እግዚአብሄር ይስጥልኝ
አንዱ-ዓለም አራጌ ዋለ

## በሁሉም መጽሐፍ መደብር በቅርብ ቀን ያገኙታል!